**የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ**
**መደበኛ እትም**

# “ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ...”
# በእጦት ያሉ ወገኖቻችን ማገልገል


አዘጋጅ፡ ጆናታን ዱፊ

**ዘላለም አስረስ እንደተረጎመው**


ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡ በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡


በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ

## 3ኛ ሩብ ዓመት

## ከሰኔ *22* - መስከረም *16/ 2012* ዓ.ም.

# ማውጫ

**አርዕስት ቀን ገጽ**

1.የእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ...... ከሰኔ 22 - 28...............6

2.የተሻለ ዓለም ለማምጣት

የሚያስችል ንድፍ.......ከሰኔ 29-ሐምሌ 5---------.......15

3.ሰንበት፡ የነፃነት ቀን.. ከሐምሌ 6-12............................24

4.ምኅረት እና ፍትሕ በመዝሙረ ዳዊት

እና በመጽሐፈ ምሳሌ.... ከሐምሌ 13-19..........................34

5.የነቢያት ልቅሶ.. ከሐምሌ 20-26.................................43

6.ፈጣሪን ማምለክ.. ሐምሌ 27 - ነሐሴ 3..........................53

7.የሱስ እና በእዕጦት ያለው ሰብዓዊ ወገን..ከነሐሴ 4–10..........62

8.ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት.. ከነሐሴ 11–17........................71

9.አገልግሎት በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን..ከነሐሴ 18–24........80

10.ወንጌልን መኖር.. ከነሐሴ 25-ጳግሜ 1............................89

11.በዳግም ምጽአቱ ተስፋ መኖር. ከጳግሜ 2 - መስከረም 2.......99

12.ምህረትን መውደድ.. ከመስከረም 3-9........................108

13.አገልጋዮች ያቀፈ ማኅበረሰብ.. ከመስከረም 10-16............118

# ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ . . .

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች “የዘላለም ወንጌል” (ራእ. 14፡6) የሆነውን የምሥራች ቃል ለዓለም ሁሉ እንድንሰብክ ተጠርተናል። ይህን በማድረግ የሱስ ደቀ መዛሙርትን ስለ ማፍራትና ስለ ማጥመቅ የተናገረውን ቃል መታዘዛችንን እናሳያለን “ ‘ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ’ ” (ማቴ. 28:20)። የተጎዱን፣ የተጨቆኑን፣ ድኾችን፣ የተራቡንና፣ የታሰሩን ማገልገል ጌታ እንድናደርግ ካዘዘን መሃል ይወሳሉ።

ለነገሩ የሱስ የደጉን ሳምራዊ ተምሳሌታዊ ታሪክ (ሉቃ. 10፡30-36) ከተናገረ በኋላ “ ‘አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ’ ” (ሉቃ. 10:37) አልነበር ያለው? ደግሞም “እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ፣ ሕዝቡን አንዱን ከሌላው ይለያል” (ማቴ. 25፡32) ብሎ የወደፊቱን ያሳየው የሱስ ራሱ--የተራቡትን፣ የታመሙትን፣ የታረዙትንና የታሰሩትን መርዳት አስፈላጊ እንደሆነ ተናግሮአል። “ ‘እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው’ ” (ማቴ. 25፡40)።

በሌላ አነጋገር ስለ ደኅንነት ታላላቅ እውነቶች ማለትም--ስለ ቤተ መቅደሱ፣ ሙታን ስለሚገኙበት ሁኔታ እና ስለ ሕጉ ዘላለማዊነት በይፋ ከማወጅ ጎን ለጎን ሌሎችን በሚያስፈልጓቸው ሁሉ ልናገለግል የተገባ ነው። ወደ ሰዎች ለመድረስ፤ ስለ ሰዎች ከመሥራት የላቀ ምን የተሻለ መንገድ አለ? “የሱስ የተጠቀመበትን ዘዴ መተግበር ብቻውን ወደ ሰዎች ለመድረስ የሚያስችል እውነተኛ ስኬት ያጎናጽፋል። አዳኙ ለሰብዓዊው ፍጡር በጎ መመኘቱን በሚገልጥ ሁናቴ ከሰዎች ተቀላቀለ። ለእነርሱ ያለውን ርኅራኄ ካሳያቸውና በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ካገለገላቸው በኋላ መተማመናውን አገኘ። በመጨረሻም ‘ተከተሉኝ’ ሲል ጥሪ አቀረበላቸው”—The Ministry of Healing, p. 143.

እግዚአብሔር ለድኾችና ለተጨቆኑ ያለውን የተለየ መቆርቆር የሚገልጹ 2,103 ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገኙ አንድ አኃዝ ያመለክታል። ስለ ተለያዩ የእምነት መገለጫዎች፣ ስለ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎችና በአጠቃላይ ስለ ክርስትና አኗኗር ዘይቤ ከቀረቡ ማጣቀሻዎች ይልቅ በእጦት የሚገኙ ወገኖችን ስለ ማገልገል የተሰጠው መልእክት በእጅጉ ይገዝፋል። በዙሪያችን ያለውን ህመምና ሥቃይ ለማስታገስ የተለየ ትኩረት ሰጥተን ልንቀሳቀስ ይገባል። ይህን ማድረጋችን በወንጌል ሥራችን ላይ እክል አይፈጥርም። እንደውም በተቃራኒው ወንጌልን በብርቱ ኃይል ለማሰራጨት ያስችለናል።

እርግጥ ነው ስለ ሌሎች በጎ በማሰብ እነርሱን ለመርዳት መንሳቀስ መልካም ነገር ነው። “ፍትሕን” ማድረግ (ሚክ.6፡8) ትክክልና መልካም በመሆኑ ብቻ እናደርገዋለን። ፍትሕ እያደረግን፣ ሌሎች ለገጠሟቸው አፋጣኝ ምላሽ ለሚሹና ጊዜያዊ እጦቶች እርዳታ እያደረግን “እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን” (1ጴጥ. 3፡ 15) ይኸውም ወደ ክርስቶስ ዘላለማዊ ህይወት ተስፋ ማመላከት የተሻለ አይሆንም?

የሱስ ደዌን ፈወሰ፣ ዐይነ ሥውሩን አበራ፣ ለምጻሙን አነጻ ከዚያም አልፎ የሞተውን አስነሳ። ሆኖም እነዚህ ታምራት ያደረገላቸው ወገኖች በሙሉ በጎልማሳነታቸው ወይም በእርጅና ዘመናቸው ሞተው የለ? የሱስም ለአፋጣኙም ሆነ ለዘላቂው ችግራቸው የቱንም ያህል ቢያገለግላቸውም--ከዚያ የላቀውን ግን አድርጎአል። እርግጥ ነው በጉዳት ይገኙ የነበሩ ወገኖችን ካገለገለ በኋላ *ተከተሉኝ* ይላቸው ነበር። በተመሳሳይ እኛም በጉስቁልና የሚኙ ወንድም እህቶችን እያገለገልን *ተከተሉት* የምንልበት ትክክለኛ ምክንያት ይኸው ነው።

በዚህ ዓለም ላይ ፍትሕና ርኅራኄ እንዲሰፍን ካለን መሻት አኳያ አምላካዊውን መንግሥት (ሉቃ. 4፡18-19) እየተለማመድን መሆናችን አያጠያይቅም። ቢያንስ ታማኝ በመሆንና የቀናውን አካሄድ በመከተል እየሰበክነው እንገኛለን። ድኾችንና የተጨቆኑትን ስንንከባከብ እግዚአብሔርን እያከበርንና እርሱን እያመለክን መሆኑ እሙን ነው (ኢሳ. 58፡6-10)። ነገር ግን የተጎዱትን፣ በሥቃይ ያሉትንና ልባቸው የተሰበረውን ከማገልገል ስንሰናከል እርሱን በተሳሳተ መንገድ እንወክላለን (ምሳ. 14፡ 31)።

በዙሪያችን የሚገኙትን በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖች ለማገልገል ስላለብን ኃላፊነት የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል በዚህ ሩብ ዓመት የሰንበት ትምህርት ጥናታችን እንመለከታለን።

"'በነፃ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ'" (ማቴ. 10፡8)።

የዚህን ሩብ ዓመት የሰንበት ትምህርት ጥናት ያዘጋጁልን ጆናታን ዱፊ ከጎርጎሮሳውያኑ ቀመር ከ2012 ዓ.ም. አንስቶ የአለማቀፉ አድቬንቲስት ልማትና ተራድኦ ተቋም (ADRA) ፕሬዚደንት ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። ተቋሙን በ2008 አውስትራሊያ ላይ ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ ሰፊ ተሞክሮ ባካበቱበት በጤና ማጎልበቻና ማኅበረሰብ አቀፍ ጤና አጠባበቅ እድገት ዘርፍ በደቡብ ፓሲፊክ ዲቪዥን የአድቬንቲስት ጤና ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል።

# 1ኛ ትምህርት

ከሰኔ 22 - 28

# የእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ

ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** ዘፍ. 1–3፣ ሐዋ. 17:28፣ መዝ. 148፣ መዝ. 24:1፣ ዘፍ. 4:1–9፣ ማቴ. 22:37–39፣ ራእ. 14:7።

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-** “ድኾችን የሚያስጨንቅ ፈጣሪያቸውን ይንቃል፤ ለተቸገሩ የሚራራ ሁሉ ግን አምላክን ያከብራል” (ምሳ. 14፡31)።

ብዙ ተጨንቀውና ተጠብበው ከእንጨት ወይም ከብረት አንድ የሆነ የሥነ ጥበብ ወይም የዕደ ጥበብ የፈጠራ ሥራ ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ለአንድ ሰው ሲያበረክቱ--ግለሰቡ ሰባብሮት ወይም የትም ጥሎት ተመልከተው ያውቃሉ? እንዲያ ከሆነ--ይህን ዓለም ፈጥሮ ለሰብዓዊ ፍጡራን የሰጠው አምላክ በኃጢአት ስብራት ሲያደርሱበት የተሰማውን ስሜት በጭላንጭልም ቢሆን ይረዳሉ እንደ ማለት ነው።

ይህች ዓለም በብዙ ጥንቃቄ መፈጠሯንና እያንዳንዱ የፍጥረት ሥራ “መልካም” እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እግዚአብሔር ስለ ፍጥረቱ የተሰማውን ስሜት አስመልክቶ ዘፍ. 1 እና 2 ጉልህ ምልከታ ይሰጠናል። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሰዎች ጋር በገጠመው ፍጥጫ፤ የሰውን ውድቀትና የአምላካዊውን ልብ ስብራት ታሪክ ከዘፍ. 3 አንስቶ ከቀረበው ምንባብ ዐውድ እናገኛለን።

ምንም እንኳ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት የዘለቀ ኃጢአት፣ ብጥብጥ፣ ኢፍትሐዊነትና ዐመጻ በምድር ላይ ቢሰፍንም፤ እግዚአብሔር ግን በሚያስደንቅ መልኩ ይህችን ዓለም ከመውደድ ወደ ኋላ አላለም። ይበልጥ የሚያስደንቀው ደግሞ ይህችን ዓለም ለመዋጀትና ዳግም ለመፍጠር የሚያስችለውን ዕቅድ ሲያወጣ፤ እንደ አማኝ ግዙፎቹ ዕቅዶች ይሰምሩ ዘንድ የምንጫወተውን ሚና ሰጥቶናል። የእርሱ ጸጋ ተቀባዮች መሆናችን እርግጥ እንደመሆኑ፤ በዚህ በተቀበልነው ጸጋ ከጌታ ጋር ተባባሪዎች ሆነን የምንሠራው ሥራ ተሰጥቶናል።

## እሑድ ሰኔ 23

# በፍጥረት ውስጥ በውልብታ የምንመለከተው፣ እግዚአብሔር

ይህ ዓለምና በውስጡ የያዘው ህይወት፣ የገዛ ህይወታችንና በህይወታችን የምናደርገው ነገር፣ በዙሪያችን ያለ የእያንዳንዱ ሰው ህይወትና ከሰዎች ጋር የምንፈጥረው መስተጋብር፣ ራሷ ህይወትና ምርጥ ህይወት ልንኖር የምንችልበት መንገድ--ሁሉ ጅማሬ እግዚአብሔር ነው "'የምንኖረውና የምንንቀሳቀሰው፣ ያለነውም በእርሱ ነውና" (ሐዋ. 17፡28)።

የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አፈጣጠር ታሪክ በዘፍ. 1፡26-31 ይመልከቱ። ታሪኩ ስለ እግዚአብሔር አምላክ ምን ዓይነት ጠቃሚ ማብራሪያዎችን ይዞአል? የሰዎችን ታሪክ አስመልክቶስ ምን ዓይነት አስፈላጊ ነገሮችን ይነግረናል?

በተፈጥሮ ውስጥ በቂ ጊዜ በማሳለፍ፣ ወደ ፍጥረቱ በማማተርና በፍጥረቱ ውስጥ የአምላካዊውን ባህሪ በጨረፍታ በመመልከት ስለ እግዚአብሔር ብዙ መማር እንደምንችል በተደጋጋሚ ሲነገር ይደመጣል። ደግሞም እኛ ራሳችን እግዚአብሔርን ያስተዋልንበትን መንገድ በመመርመር እርሱ ዓለምን እንዴት እንደ ፈጠረ በውልብታም ቢሆን መመልከት እንችላለን። ለምሳሌ እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ ከሆነ፤ በፍጥረቱ ውስጥ ሕግና ሥርዓት እንደምናገኝ መጠበቅ ይኖርብናል። ወይም እግዚአብሔር የፈጠራ ሥራ አምላክ እንደሆነ የምናምን ከሆነ እርሱ በፈጠረው ዓለም ውስጥ አስደናቂ የፈጠራ ሥራዎችን በማግኘታችን ልንደነቅ አይገባም።

በተመሳሳይ እግዚአብሔር የግንኙነት አምላክ እንደሆነ እናምናለን። አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ግንኙነት እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን በአንድ ያስተሳሰረበት ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ እናገኘዋለን። እርሱ እያንዳንዱ የዚህ ዓለም ፍጥረት ከተቀረው ጋር ግንኙነት እንዲኖረው አድርጎ ፈጥሮአል። እንስሳትን የዝምድና ኅብር እንዲኖራቸው አድርጎ ፈጥሮአል። ሰብዓዊ ፍጡሮችን ከራሱ ከፈጣሪ ጋር፣ እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከተቀሩት ፍጥረታት ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው አድርጎ ፈጠረ።

ስለ እግዚአብሔር ያለን እሳቤ በብዙ መልኩ ውሱንና የተገደበ ቢሆንም፤ ከእርሱ ጸባይ መመልከት የምንችለው ነገር ዓለም እንዴት መሆን እንዳለባት ዳግም እንድናጤን ሊገፋፋን ይገባል።

***ምድር ግልጽ ሆኖ የሚታይ የኃጢአት ውድመት ቢደርስባትም፤ ይህች ዓለም ዛሬም የአምላካዊው ባህሪ ነጸብራቅ መሆኗን እንዲያስተውሉ እንዴት ትረዳዎታለች?***

## ሰኞ ሰኔ 24

## ፍጹም የሆነው ዓለም

ማንም ቢሆን በጥንቱ የኤደን ትዝታ በቀላሉ ሊቆዝም ይችላል። እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን መኖሪያ አድርጎ በፈጠረላቸው የአትክልት ስፍራ በቀረቡ መግለጫዎች ውስጥ በልባችን የናፍቆት ስሜት እንዲያጭር የሚያደርጉ ነገሮች አሉ። ዓለም እንዴት እንደሚሠራ ለመረዳት ቢያዳግተንም እንኳ በተሞክሮው ውስጥ ማለፍ እንዳለብን ግን ይሰማናል። ውስጣችን ሊኖር የሚችለው የእርካታ ስሜትና ምሉዕነት “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ” በሚል እርሱ የተሰማውን ስሜት የሚጋራ ይመስላል። እግዚአብሔር የሠራው ነገር ውበትን ሊሠራ ከሚችል ብቃት ጋር በአንድ አጣምሮ የያዘ ነበር። በቅርጽም ሆነ በግብር አስደናቂ ውበት የተላበሰ ንድፍ ነበር። በህይወትና ቀለማት የፈካ ብቻ ሳይሆን ህይወት እንድታብብ የሚያስችለውን ማንኛውንም አስፈላጊ ግብዓት አሟልቶ የያዘ ነበር። እግዚአብሔር በጥቂት ፋታ የመንፈስ መነሳሳት እንዲፈጠር እያደረገ መልካም የሆነውን የዚህን ዓለም የፍጥረት ሥራ መሥራቱ ብዙም የሚደንቅ አይሆንም።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ እግዚአብሔርም “መልካም እንደሆነ አየ” በሚል በተደጋጋሚ ስለ ቀረቡት መግለጫዎች ፍቺ ምን ያስባሉ? ዘፍ. 1:4፣ 10-12፣ 18፣ 25፣ 31።

---

---

ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ሰው ሙሉ ለሙሉ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ቢሆንም አምላካዊው ቃል እንደ ኢዮ. 38-41 እና መዝ. 148 ባሉ በፍጥረት ሥራ ሐሴት በሚያደርጉ ምስጋናዎችና ውዳሴዎች የተሞላ ነው። እነዚህ ነገሮች ምድር በመጀመሪያ እንደ ተፈጠረች ማለትም ኃጢአት ሳታውቅ ብቻ የነበረውን ሁናቴ በጨረፍታ በመመልከት በኃላፊ ጊዜ አለመጻፋቸውን ማስታወስ የግድ ይሆናል። ይልቁንም ዛሬም በዓለማችን በተጨባጭ በሚስተዋለው መልካምነት ላይ

ሐሴት እናደርግ ዘንድ በኃላፊ ሳይሆን በአሁን ጊዜ ተጽፈዋል።

ዙሪያችንን የከበቡንን ኢምንት የሚመስሉ አስገራሚ ነገሮች እያደነቅንና በእግዚአብሔር እየተመካን ምስጋና እናቀርብለት ዘንድ የሱስ ከዓለም ስለሚጠብቀን አምላካዊ ቸርነትና ጥንቃቄ በምሳሌ ነግሮናል (ማቴ. 6፡26፣ 28-30)። ዐይኖቻችንን ከፍተን አስደናቂውን የፍጥረት ሥራ ብንመለከት፤ ከፈጣሪያችን የተበረከተልን ገራሚ ስጦታ ተቀባዮች መሆናችንን በእውነት ማየት እንችላለን። በአስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ልንሆን ብንችል እንኳ ምላሻችን ለስጦታ ሰጪው ምስጋና ማቅረብና ራስን በትህትና ማስገዛት ሊሆን ይገባል።

ይህ ዛሬ በጨረፍታ የምንመለከተውና የተሞክሮአችን አካል የሆነው የምድር ውበት፣ ደስታና መልካምነት በአንድ ወቅት በሙላት የዓለም አካል እንደነበረ ሁሉ፣ አንድ ቀን እንደገና ገቢራዊ እንደሚሆን በአምላካዊው የፍጥረት ሥራ ሐሴት የምናደርግና ዳግም ምጽአቱን የምንጠባበቅ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ልንገነዘብ ይገባል።

***ከተፈጥሮ ጋር ካሎት ቁርኝትና ተሞክሮ አኳያ በተለይ ስለ አስገራሚው የፍጥረት ሥራ የትኛውን ያደንቃሉ? በዕለት ከዕለት ህይወትዎ በአስገራሚው ተፈጥሮ አማካኝነት ጌታን በተሻለ ማወቅ የሚችሉት እንዴት ነው?***

## ማክሰኞ ሰኔ 25

## የምድር መጋቢዎች

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የኤደን አትክልት ስፍራ እና አዲስ የተፈጠረችው ምድር ህይወት እንዲያብብባቸው--በተለይም ሰብዓዊ ፍጡራን ሐሴት ያደርጉባቸው ዘንድ በብዙ የተትረፈረፉ ነገሮች የተሞሉ ነበሩ። ደግሞም እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ ወንድ እና ሴት ፍጥረቶቹ እንዲሁም ከእነርሱ በኋላ የምንመጣው እኛ ጭምር በፍጥረቱ የምንጫወተውን ሚና ሰጠን። በፍጥነት ይፋ ሆኖ መታየት እንደ ቻለው--አዳምና ሔዋን በዚህ አዲስ ምድር ላይ የተለየ ማዕረግ ተሰጣቸው።

አዳም በመጀመሪያ የተሰጠው ሥራ እንስሳትንና አዕዋፋትን መሰየም ነበር (ዘፍ. 2፡19)። በመቀጠል ከራሱ ከእግዚአብሔር በበረከት መልክ የቀረበለት ሌላ ሚና ተሰጠው "እግዚአብሔርም 'ብዙ ተባዙ፤ ምድርን ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባሕርን ዓሦች፣ የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ሁሉ ግዟቸው' ብሎ ባረካቸው" (ዘፍ. 1፡28)።

የሚከተሉትን ሁለት ጥቅሶች ማለትም ዘፍ. 1፥28 እና 2፥15 ያስተያዩ። ሰብዓዊውን የሥራ ኃላፊነት በአንድ ወይም በሁለት ዓረፍተ ነገሮች እንዴት ማስቀመጥ ይችላሉ?

---

---

ዘፍ. 1፥28--በአብዛኛው የክርስትና ታሪክ ተፈጥሮን እስከ ማውደም የደረሰ የመበዝበዣ ፈቃድ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሎአል። በእርግጥ ምድር የተፈጠረችው ለሰው ህይወት፣ ጥቅምና ደስታ ሲባል ቢሆንም--ለሰው የተሰጠው ኃላፊነት “እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት” ነው (ዘፍ. 2፥15)።

ስለ መጋቢነት ስንነጋገር በቅድሚያ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ገንዘብ ቢሆንም፤ ነገር ግን በመጋቢነት ዙሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው የመጀመሪያ ትእዛዝ እግዚአብሔር ፈጥሮ በአደራ የሰጠንን ምድር ስለ መጠበቅና ስለ መንከባከብ ይናገራል። ለአዳምና ሔዋን የተሰጠው ትእዛዝ ምድር የልጆቻቸውና የቀጣዮቹ ትውልዶች የጋራ መኖሪያ እንደምትሆን አስቀድሞ የተመለከተ ነበር። ለምድር በነበረው የቀደመ ዕቅድ መሰረት ይህች አዲስ የተፈጠረች ዓለም ለመላው ሰብዓዊ ፍጡራን--የህይወት፣ የመልካምነትና የውበት ምንጭ ሆና የምትቀጥል ሲሆን፤ አዳምና ሔዋን ምድርን በመንከባከብና በመጠበቅ ረገድ የላቀ ሚና ይኖራቸው ነበር።

ምድር ዛሬም የጌታ ናት (መዝ. 24፥1)፤ እኛም እግዚአብሔር በሰጠን ነገሮች ሁሉ መጋቢ እንድንሆን ተጠርተናል። ምናልባት በዚህ በወደቀ ዓለም እንደ መጋቢ የእኛ ኃላፊነት እንደውም የላቀ ነው ብለን መደምደም እንችላለን።

***በዚህ በወደቀ ዓለም የምድር መጋቢ መሆን ለእርስዎ ምን ትርጉም አለው? ይህን ኃላፊነት መገንዘብዎ በየዕለት ሕይወትዎ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ ይኖረዋል?***

## ረቡዕ ሰኔ 26

## የተበላሸው ዓለም

እግዚአብሔር በምድር ላይ ለማንም ሳይሰጥ ለአዳምና ሔዋን ብቻ የቸረው ነገር ቢኖር የመምረጥ ነፃነት ነው። ከእጸዋት፣ ከዛፎችና ከእንስሳት በተቃራኒ እነርሱ መምረጥ የሚችሉ ሰብዓዊ ፍጡራን ነበሩ። ለሰብዓዊው የመምረጥ ነፃነት ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው እግዚአብሔር እርሱ የፈጠራቸው ሰዎች ራሱኑ ላለመታዘዝ መምረጥ

እስኪችሉ የሚፈቅድ ነፃነት ሰጣቸው። ከሰብዓዊ ፍጡሮቹ ጋር ፍቅርንና የመምረጥ ነፃነትን መሰረት ያደረገ ከፍ ያለ ግንኙነት እንዲኖረው ያቀደው አምላክ በዚህ ድርጊቱ መላውን የፍጥረት ሥራውን አደጋ ላይ ጣለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ልዩ ሰብዓዊ ፍጥረቶቹን ተጠቅሞ መልካምና ፍጹም የሆነችውን ዓለም ምስቅልቅሏን ለማውጣት በጽኑ የሚሻ አውዳሚ ነበር (እዚህ ላይ መላእክት የመምረጥ ነፃነት ባለቤት መሆናቸውን ልብ ይሏል)። እባብን ተጠቅሞ የተናገረው ዲያብሎስ ፍጹምና ምሉዕ በሆነው የእግዚአብሔር ስጦታ ላይ ጥያቄ አቀረበ። እግዚአብሔር ከሰጣቸው በላይ መመኘታቸው፣ አምላካዊውን በጎነት መጠራጠራቸውና በራሳቸው ላይ መታመናቸው ዋንኞቹ ፈተናዎች ነበሩ።

በእግዚአብሔር የተነደፈውና ለፍጥረት ወሳኝ የነበረው ግንኙነት በዚያ ምርጫ እና ድርጊት ተበጠሰ። ከፈጣሪያቸው ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ሆነው የተነደፉት አዳምና ሔዋን ከእንግዲህ ከእርሱ ጋር ሐሴት ማድረጋቸው አከተመ (ዘፍ. 3፡ 8-10)። እነዚህ ሁለት ሰብዓዊ ፍጡሮች እርቃናቸውን መሆናቸውንና ሐፍረት እንደ ተሰማቸው በድንገት አስተዋሉ። በሁለቱ መካከል የነበረውም ግንኙነት እንደማይጠገን ሆኖ ተለወጠ። ከተቀረው የምድር ፍጥረታት ጋር የነበራቸውም ግንኙነት እንዲሁ ውጥረት የሰፈነበትና የተበላሸ ሆነ።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 3፡16-19። ጥቅሶቹ በሰብዓዊ ፍጡራንና በተፈጥሮ መካከል ስለ ተለወጠው የግንኙነት ሁኔታ ምን ይነግሩናል?

---

---

በተጨባጭ በተከሰተው ኃጢአት መንስኤ ህይወት በድንገት ለአዳም፣ ለሔዋንና ለተቀረው ፍጥረት በሙሉ አስቸጋሪ ሆነች። በተለይ ሰብዓዊውን ፍጡርና የእርስ በርስ ግንኙነቱን የጎዳው የኃጢአት ውጤት በገሃድ የሚታይ ነው። ከፈጠረን አምላክ ጋር በጣም እንድንራራቅ አደረገን። ቤተሰቦቻችን በብዙ መንገድ የዚህ ችግር ገፈት ቀማሽ ናቸው፤ ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነትም ባብዛኛው በተግዳሮት የተሞላ ነው። ከምንኖርባት ዓለምና ከተፈጥሮ ጋር ያለን ግንኙነትም እንዲሁ ትግል የበዛበት ነው። ፈርጀ ብዙዎቹ የህይወታችን ገጽታዎችም ሆኑ ዓለማችን በኃጢአት ምክንያት የተከሰተውን ብልሽት ያሳያሉ።

ዓለም የዛሬውን ገጽታ እንድትይዝ ሆኖ በእግዚአብሔር አልተፈጠረችም። በዘፍ. 3 የምናነበው "እርግማን" ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ምድራችንን ዳግም ለመፍጠርና በኃጢአት የተሰበረውን ግንኙነት ለመጠገን የሰጠውን ተስፋ ጭምር ነው። ኃጢአት በህይወታችን ሊኖረው ከሚችል ውጤት ጋር መታገላችንን እየቀጠልን፤ የቀደመችውን ዓለም መልካምነት እንድንጠብቅና እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ያለውን ዕቅድ በህይወታችን በተግባር እንድናሳይ ተጠርተናል።

## ሐሙስ ሰኔ 27

# ድርና ማግ የሆነው ሰብዓዊ ቤተሰብ

ኃጢአት ከገባ በኋላ ምድርን ምስቅልቅሏን ለማውጣት ብዙ ጊዜ አለወሰደበትም። በቅናት መጦዝ፣ በስህተት ማስተዋልና በቁጣ መንደድ የመጀመሪያው ግድያ በወንድማማቾች መካከል እንዲፈጸም መንስኤ ሆነ። ቃየን ስለ ሠራው ኃጢአት እግዚአብሔር በጠየቀው ጊዜ የሰጠው ምላሽ ምጸታዊ ነበር "' አላውቅም፤ እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?' " (ዘፍ. 4:9)። እግዚአብሔር በመጀመሪያ በጠየቀው ጥያቄ ውስጥ "አዎ፣ በትክክል የወንድምህ ጠባቂ ነህ የሚል ሃሳብ በተዘዋዋሪ ይዞአል።

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ምሳ. 22፡2። በዚህ ቀላል በሚመስል ዐረፍተ ነገር ውስጥ በተዘዋዋሪ የምናገኘው ሀሳብ ምንድን ነው? ከባልንጀሮቻችን ሰብዓዊ ፍጡራን ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ግንኙነት ምን ይነግረናል?

---

---

እያንዳንዱ የምንገናኘው ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠሩ ፍጥረታት መካከል አንዱ እንደ መሆኑ፤ የቱንም ያህል ደካማና የተፍረከረከ ቢሆንም ሁላችንንም ከእግዚአብሔር ፍጥረት ጋር በአንድ የሚያስተሳስረን የእርስ በርስ መገናኛ ዘዴ አካል ነው። "እኛ ሁላችን በሰብዓዊው ድርና ማግ በአንድነት ተሸምነናል። በሰብዓዊ ፍጡራን መካከል የሚከሰት ማንኛውም ክፋት በሁሉም ላይ አስጊ አደጋ ያስከትላል።"—Ellen G. White, The Ministry of Healing, p. 345. ወደድንም ጠላንም በዚህ በጋራ በሚያስተሳስረን ገመድ የተነሳ በፈጣሪም ሆነ በሰው ፊት እግዚአብሔር የሰጠን ኃላፊነት አለብን (ማቴ. 22፡37-39)።

እግዚአብሔር ፈጣሪያችን መሆኑን የሚናገረው መልእክት በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ተደጋግሞ ሲቀርብ እንመለከታለን። ለምሳሌ ሰንበትን እንድናስታውስና

(ዘፀ. 20፡11) በመጨረሻው ዘመን ለእግዚአብሔር እንድንሰግድ (ራእ. 14፡7) ጥሪ የቀረበበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው። እንዲሁም በዕጦት ላሉ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግና በችግራቸው መድረስ ተቀዳሚ አጽንኦት የተሰጠው ተግባር ነው።

---

---

እኛ ሁላችን በጋራ በሚያስተሳስረን የቀደመው ጅማሮአችን ይኸውም በእግዚአብሔር ተሳሰረናል። "ደኾችን የሚያስጨንቅ እግዚአብረሔርን ይንቃል" (ምሳ. 14፡31)።

እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ አምልኮአችንን እና አገልግሎታችንን ጨምሮ መላውን ህይወታችንን በባለቤትነት ለመጠየቅ ባለ መብት ነው። አንዳንዴ ፈታኝና ምቾት የሚነሳ ሊሆን ቢችልም፤ በእርግጥም የወንድማችን "ጠባቂ" ነን።

**እንደ ፈጣሪ፤ እግዚአብሔር ያለው ባለመብትነት በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ተደጋጋሚ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ የቀረበው ለምን ይመስሎታል? ይህ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ይህ ሐቅ ከሌሎች ጋር በሚኖረን አግባብ ላይ ተጽእኖ የሚኖረው ለምንድን ነው?**

## አርብ ሰኔ 28

ተጨማሪ ሃሳብ፡ Read Ellen G. White, , "The Creation," pp. 44–51, in Patriarchs and Prophets.

" 'እግዚአብሔር ፍቅር ነው' ተፈጥሮውም፣ ሕጉም ፍቅር ነው። 'ከፍ ከፍ ያለውና ልእልና ያለው እርሱ፣

ስሙም ቅዱስ የሆነው፣ ለዘላለም የሚኖረው' 'መንገዱ ዘላለማዊ ነው' 'በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ፣ ከመዞር የተነሳ የሚያርፍ ጥላም የለም'. . .

"አምላካዊው የመፍጠር ኃይል ውስጥ የታየው እያንዳንዱ ማንነት የዘላለማዊ ፍቅሩ መገለጫ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ለፍጥረታቱ ሁሉ ፍጹም የሆነ በረከት ያጎናጽፋል።" (የኃይማኖትና አባቶችና ነቢያት ገጽ 22።)

"ሰዎች ታማኝ መጋቢ ሆነው የጌታን ንብረት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ቢያውሉ ኖሮ ዳቦ የሚጠይቁ የልቅሶ ድምጾች ባልተሰሙ፣ በድኸነት የተጨበጡና የታረዙም ባልኖሩ ነበር። ሰብዓዊውን ፍጡር በእጦት ሥቃይ ውስጥ የዘፈቀው የሰዎች

ታማኝ አለመሆን ነው... ሰዎችን መጋቢዎቹ አድርጎ የሾመው እግዚአብሔር አምላክ በሰብዓዊው ሥቃይ፣ ጉስቁልና እና እርቃን መወንጀል አይችልም። ጌታ ለሁሉም በቂ የሆነ ቸርነት አድርጎአል።"—Ellen G. White, Welfare Ministry, p. 16.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ከላይ የቀረበውን የኤለን ኋይት መግለጫ በጥንቃቄ ይመልከቱ። ለመሆኑ ምን እያለች ነው? በዙሪያችን አብልጦ ተንሰራፍቶ ለምንመለከተው ድኽነት ውሎ አድሮ ኃላፊነቱ የማን ነው ትላለች? አባባሉ ታማኝ መጋቢነት በእጅጉ አስፈላጊ ስለመሆኑ ምን ይነግረናል?**

**2.በኃጢአት ምክንያት በደረሰ በሺ የሚቆጠሩ ዓመታት ብልሽት በኋላ የፍጥረትን መልካምነት ለመመልከት ምን ያህል ይቻለናል? በእግዚአብሔር ፈጣሪነት የምናምን ሕዝቦች እንደመሆናችን ሌሎች የእርሱን የፍጥረት ሥራ መልካምነት መመልከት እንዲችሉ ምን ማድረግ እንችላለን?**

**3.መጋቢነት የተሰኘውን ቃል እንዴት ያስተውሉታል? የዚህ ሣምንት ትምህርታችን መጋቢ የተሰኘውን ቃል ፍቺ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንዲመለከቱ እረድቶታል? በተለይ በዚህ ማዕረግ በእግዚአብሔር ከመጠራታችን አኳያ?**

**4.ይህ ሰው "በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረና በእርሱ የተወደደ ነው" የሚል ጽሑፍ በእያንዳንዱ የምንገናኘው ሰው ላይ የምንመለከት ቢሆን ኖሮ፤ ይህ አባባል በሌሎች ላይ ባለን አመለካከትና ቀረቤታ ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ሊያመጣ ይችል ነበር?**

*ማጠቃለያ፡ እግዚአብሔር መልካምና የተሟላ ዓለም ከፈጠረ በኋላ የፍጥረት ሥራውን "እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት" በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው ሾመ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለእኛ ያቀደውን ነገር ኃጢአት ቢያበላሸውም ዛሬም እንደ መጋቢ መልካም ለሆነው የፍጥረት ሥራ እና ለባልንጀራችን በጎነት የምንጫወተው ሚና አለን።*

# 2ኛ ትምህርት

**ከሰኔ 29 - ሐምሌ 5**

# የተሻለ ዓለም ለማምጣት የሚያስችል ንድፍ

ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** *ዘፀ.* 3:7፣ *ማቴ.* 22:37–40፣ *ዘፀ.* 22:21–23፣ *ዘዳ.* 14:22–29፣ 26:1–11፣ *ዘሌዋ.* 25:9–23።

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-** " 'ወገንህን አትበቀል፤ ወይም ምቀኛ አትሁንበት፤ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ' " (ዘሌዋ. 19:18)።

እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን በምኅረት ከተሞላ ማንነቱ ጋር በዓይነቱ ልዩ የሆነውን የግንኙነት መስመር እንደ ጠበቁ የቆዩ ሕዝቦች ነበሩት። የእነ ሔኖክ፣ ኖህ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና ሌሎች ወገኖች ታሪክ እግዚአብሔር ከሰብዓዊው ፍጡር ጋር የነበረውን የተበላሸ ግንኙነት ዳግም ለመመስረት የነበረውን መናፈቅ ያሳያል። ነገር ግን በግንኙነቱ መስመር መታደስ የቱሩፋቱ ተጠቃሚዎች እነዚህ ጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው ብቻ እንዳልነበሩ መመልከት እንችላለን። ይልቁንም እነዚህ ወገኖች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መስርተው በእርሱ ሲባረኩ--ይህን በረከት ለሌሎች ማስተላለፍ የግዙፉ ዕቅድ አካል ነበር። "' ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ ደግሞም እባርክሃለሁ፤ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎች በረከት ትሆናለህ. . . በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ' " (ዘፍ. 12:2-3)። እርሱ ሲባረክ ለሌሎችም በረከት መሆን ይችላል።

ይህ በረከት በእስራኤል ሕዝብ አማካይነት መምጣት የነበረበት ሲሆን፤ ውሎ አድሮ መሲህም ከዚያው ሕዝብ መምጣቱ የታወቀ ነበር። እስራኤላውያን እንደ ሕዝብ ከተመሰረቱ በኋላ እግዚአብሔር የሚሠራው በጣት ከሚቆጠሩ ግለሰቦች ጋር ሳይሆን ከመላው ሕዝብ ጋር ሆነ። ይህን ተከትሎ እነዚህ በእግዚአብሔር የተባረኩ ሕዝቦች ለሌሎችም በረከት ይሆኑ ዘንድ የሚተዳደሩባቸውን ሕጎች፣ ደንቦችና የሚያከብሯቸውን በዓላትና ወግ ልማዶች ሰጣቸው። ይህ መርኅ ዛሬም የሚሠራ ለመሆኑ አፋችንን ሞልተን መናገር እንችላለን።

# እሑድ ሰኔ 30

# የሚሰማው አምላክ

“ ‘በግብፅ አገር የሚኖሩትን የሕዝቤን መከራ አይቻለሁ፤ ከአሠሪዎቻቸው ጭካኔ የተነሳ የሚያሰሙትንም ጩኸት ሰምቻለሁ፤ ሥቃያቸውንም ተረድቼአለሁ’ ” (ዘፀ. 3፡7)።

እየተቀዛቀዘ ሳይሆን እየጋመ ይሄድ ለነበረ ጭካኔ የተሞላበት የባርነት ዘመን--አራት መቶ ዓመት መጠበቅ እጅግ ረጅም ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ ተመልሶ ከግብፅ እንደሚያወጣቸውና ወደ ለምለሚቱ ምድር እንደሚመራቸው የተስፋ ቃል ሰጥቶአቸው የነበረ ቢሆንም፤ ትውልድ ሄዶ ትውልድ ቢተካም የጨቋኞቹን ጣዖት አምላኪ ጌቶቻቸውን ሐብትና ክብር እንዲገነቡ ተተዉ። እግዚአብሔርም ጸጥ ያለ መሰለ።

ከዚያም እግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ ራሱን ገለጠ። ጭው ባለ ምድረ በዳ--በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ ለአንድ ትሁት ኮብላይ ልዑል እና የበጎች እረኛ ጌታ ራሱን ገለጠ። እግዚአብሔር በወቅቱ ዳተኛ ለነበረው ሙሴ የሚሠራውን ሥራ ሰጠው። እስራኤላውያን ወደ ነበሩበት ግብፅ ተመልሶ በመሄድ እግዚአብሔር ጭቆናቸውን ማየቱንና መስማቱን የሚገልጥ መልእክት መላክ ለሙሴ የተሰጠው የመጀመሪያው ክፍል ኃላፊነት ነበር። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር በእርግጥ ለሕዝቡ እንደሚጠነቀቅ ያሳየ ክስተት ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ሕዝቡ የሚገኙበትን ሁናቴ ለመለወጥ ጌታ አንድ አስደናቂ ለውጥ ማድረግ ነበረበት።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 3፡16-17። እግዚአብሔር በዓይነቱ ልዩ የሆነውን ይህን እቅድ ለእነዚህ ሕዝቦች አውጥቶ መሥራት እንዲጀምር ያስፈለገው ለምንድን ነው? ከዚህ አምላካዊ መግለጫ ይበልጥ ትኩረትዎን የሳበው የትኛው ክፍል ነው?

---

---

ሆኖም እግዚአብሔር በዚህ አልቆመም። የእግዚአብሔር እቅድ ሕዝቡ የተሻለ ምድር ባለቤት ሆኖ እንዲወጣ ብቻ ሳይሆን ከግብፅ ባዶ እጁን፣ በድኽነት እንዳይወጣም ጭምር ነበር። እነዚህ ወገኖች ላለፉት አራት መቶ ዓመታት ለግብፅ ሕዝብና መንግሥት ብልጽግና ይሄ ነው የማይባል ከፍተኛ የኤኮኖሚ አስተዋእጾ አበርክተዋል። ፈርኦን ሕዝቡን በቀላሉ እንደማይለቅ እግዚአብሔር አስቀድሞ ተመልክቶ የነበረ ቢሆንም፤ እስራኤላውያን ለዘመናት ለሠሩት ከባድ ሥራ ተመጣጣኝ ማካካሻ ይዘው እንደሚወጡ እግዚአብሔር ለሙሴ አረጋግጦለት ነበር። “ይህ ሕዝብ በግብፃውያን ዘንድ የመወደድን

ጸጋ እንዲያገኝ ስለማደርግ በምትወጡበት ጊዜ ባዶ እጃችሁን አትሄዱም” (ዘፀ. 3፡21)። እስራኤላውያን አስከፊውን የጭቆና ገፈት ከቀመሱባቸው ዘመናት በኋላ እግዚአብሔር ከእነዚህ የቀድሞ ባሮች ጋር በዓይነቱ አዲስ የሆነ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ዕድሉን ተጠቀመበት። ሕዝቡ ከተለመደው የአኗኗር ዘይቤ ወጥቶ በተለየ መንገድ እንዲኖርና በዘላቂነት ራሱን ችሎ የሚያድግ ማኅበረሰብ ለመመስረት የአምላካዊው ፍላጎት ነበር። ይህ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ማኅበረሰብ ለአጎራባች ሕዝቦችና መንግሥታት ሞዴል በመሆን ልክ እንደ አብርሃም እነርሱም ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት በረከት መላውን ዓለም ይባርክ ዘንድ አምላካዊው ዕቅድ ነበር።

***እግዚአብሔር አምላክ በዓለም ያሉ ሕዝቦችን ሥቃይና መከራ የሚመለከትና ልቅሶአቸውን የሚሰማ አምላክ መሆኑን መገንዘብዎ ለእርስዎ ምን ዓይነት ትርጉም አለው? ታሪኩ ስለ እግዚአብሔር ምን ይነግሮታል? ይህን ጥቅስ በድጋሚ ይመልከቱ--ዘፀ. 4፡31።***

## ሰኞ — ሐምሌ 1

# ዐሥርቱ ትእዛዛት

***ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 22፡37-40፤ ዘፀ. 20፡1-17። ዐሥርቱን ትእዛዛትን ሲያነቡ የሱስ ስለ እነዚህ ትእዛዛት የሰጠው የማጠቃለያ ሃሳብ ይበልጥ እንዲያስተውሉአቸው የሚረዳዎ እንዴት ነው?***

---

---

ዐሥርቱ ትእዛዛት ልክ እንደ ሕገ መንግሥት ይነበባሉ። እነዚህ መግለጫዎች መሰረት ስላደረጉበት ነገር አጠር ያለ መግቢያ--ማለትም እግዚአብሔር ሕዝቡን የመታደጉ እውነታ እና አገሪቱ የተመሰረተችባቸውን ዐበይት መርኆዎች ሰነዱ በዝርዝር ያቀርባል። እዚህ ላይ ፍቅር ለእግዚአብሔር እና ፍቅር ለሰው በሚል መርኅ ሰብዓዊ ፍጡራን ምርጥ በሆነ ፍቅር አምላካቸውንም ሆነ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ የቀረቡ ልዩ ትእዛዞች ነበሩ። ክርስትናን በቅርስነት የያዙ የአያሌ አገራት ሕጎች መሰረት ከእነዚህ መርኆዎች መመዘዛቸው ብዙም የሚገርም አይሆንም።

ከእነዚህ መግለጫዎች አብዛኞቹ አጠር ብለው ቢቀርቡም የተጽእኖአቸውን ወርድና ስፋት ዝቅ አድርገን መመልከት የለብንም። መግለጫዎቹ ማለትም ዐሥርቱ ትእዛዛት እንደ ሕይወት ሕግጋትነታቸው ያላቸውን ጠቅላይ ባህሪ መዘንጋት የለብንም። ለምሳሌ

“አትግደል” (ዘፀ. 20፡13) የሚለው አሥረኛው ትእዛዝ “ህይወትን የሚያሳጥር ማንኛውም ዓይነት ኢፍትሐዊነት... የተቸገረውን ወይም በሥቃይ ያለውን ችላ የሚል ራስ ወዳድነት” (የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገጽ 346) በሚል አጠር ያለ ፍቺ ቀርቦአል። በተመሳሳይ መስረቅ የሚከለክለው ሕግ (ዘፀ. 20፡15) “የባርነት ንግድ መፈጸምና ሰዎችን በጦርነት ወርሮ መያዝን ያወግዛል።” እንዲሁም “የሠራተኞችን ክፍያን መክፈል፤ የወሰድነውም ብድር ቢኖር በአግባቡ መመለስ እንዳለብን ይነግረናል።” በተጨማሪ “ለግል ጥቅም ሲባል የሌሎችን--አለማወቅ፣ ደካማነት ወይም እጦት ተገን በማድረግ” ማጭበርበር የለብንም።--(የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገጽ 346-347)።

መጥፎ ሰዎች እንዳልሆን በቀላሉ ለራሳችን መንገር እንችል ይሆናል። ለምሳሌ በአንድ ግድያ ወይም የስርቆት ወንጀል ላይ ተሳታፊዎች ባለመሆናችን ራሳችንን እንደ ጻድቅ እንቆጥር ይሆናል። ነገር ግን የሱስ ስለ ትእዛዛቱ ሲናገር ከትእዛዛቱ የተወሰኑት በመጠበቃቸው ብቻ ሕጉ ተከብሮአል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦአል። ይልቁንም አስተሳሰባችን፣ ተነሳሽነታችን--ከዚያም አልፎ ማድረግ እንዳለብን የምናውቀውን ነገር አለማድረጋችን በራሱ አምላካዊውን ሕግ ሊጥስ ይችላል (ማቴ. 5፡ 21-30)።

እያንዳንዱ የዐሥርቱ ትእዛዛት ሕጎች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በጽኑ ገቢራዊ ቢሆኑና ከሰዉ ህይወት ጋር ብርቱ ቁርኝት ቢኖራቸው ምን ሊፈጠር እንደሚችል በዐይነ ህሊናዎ ለመሳል ይሞክሩ። እያንዳንዱ ሰው ፍቅሩን በጋለ መንፈስ ለሰው እንዲሁም ለእግዚአብሔር የሚገልጽ፣ ለሌሎች እንክብካቤ የሚያደርግ፣ ንቁና ደስተኛ ማኅበረሰብ በሆነ ነበር።

***እጅግ የገዘፉትንና ለህይወታችን ጠቃሚ የሆኑትን የዐሥርቱን ትእዛዛት እንደምታዎች ችላ እያልን “ጠባብ” በሆነ እይታ ማንበብ የሚቀናን ለምንድን ነው? ጠባቡን የንባብ ስልት መከተል ቀላል የሆነው ለምንድን ነው?***

## ማክሰኞ ሐምሌ 2

## ባሮች፣ መበለቶች፣ አባት የሌላቸው ህፃናትና መጻተኞች

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ዘፀ. 23፡9። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው መልእክት ምንድን ነው?

ከባርነት ነፃ ለመውጣት አዲስ የነበሩት እስራኤላውያን--ጭቆና፣ ብዝበዛና እጅግ ዝቅ ተደርጎ መታየት ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ነፃነታውቸን ሲያከብሩ ከየት እንደመጡ፣ ዝቅ ተደርጎ መፈረጅ ምን ይመስል እንደነበርና እግዚአብሔር እነርሱን ነጻ ለማውጣት ያደረገውን በጎነት እንዳይረሱ ጌታን አሳስቦት ነበር። በመሆኑም እነዚህ ሕዝቦች ያለፉበትን ታሪክ "ከባርነት ምድር ከግብፅ እግዚአብሔር በኃያል ክንዱ አወጣን" (ዘፀ. 13፡14) ብለው ለልጅ ልጆቻቸው ይነግሩ ዘንድ እግዚአብሔር እንደ መታሰቢያ አድርጎ የፋሲካን በአል ሰጣቸው።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 22፡21-23። እስራኤላውያን በመሰረቱት አዲስ ማኅበረሰብ ውስጥ ድኾችንና መጻተኞችን እንዴት መመልከት እንዳለባቸው በባርነት ያለፉበት ትውስታ ምን ያህል ሊረዳቸው ይችላል?

---

---

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ተጨማሪ ጊዜያቶችን እንዲያሳልፍ በቀረበለት ጥሪ መሰረት ግዙፎቹን ዐሥርቱን ትእዛዛት እና ዝርዝር መመሪያዎችን ከእርሱ ተቀበለ። እግዚአብሔር የመገናኛ ድንኳኑን ስለ መገንባት መመሪያ ከመስጠቱ አስቀድሞ--አብዛኞቹ እስራኤላውያን ካለፉባቸው ተሞክሮዎች በተቃራኒ ባሮችን ተገቢ በሆነ መንገድ ስለመያዝ የሚናገሩ ሦስት ምዕራፍ ያሏቸውን ሕጎች ሰጥቶአቸው ነበር። እነዚህ ሕጎች ስለ ከባድ ወንጀሎች፣ ሐብት ስለ ማፍራት፣ ስለ የዕለቱ አኗኗር የሚናገሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ ሕጎቹን ተግብሮ ፍትሕን በማስፈኑ ረገድ--የፍርድ ሸንጎዎችን ለማቋቋም የሚያስችሉ መርኅዎችንም ያካተቱ ነበሩ (ዘፀ. ምዕ. 21 እስከ 23)።

በዚህ በዓይነቱ አዲስ የሆነ የእስራኤል ማኅበረሰብ፤ ለዜጎች መድረስ እንዲሁም ለመጻተኞችና ለአደጋ ተጋላጮች አለኝታ መሆን በጉልህ ከቀረቡት ሕጎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ከምንም ዓይነት ብዝበዛ የተጠበቁ ነበሩ። የሚበሉትን በተመለከተ ለስብእናቸው ተገቢውን ክብር በሰጠ መልኩ ከማንኛውም ሰው እርሻ ዙሪያ ቃርሚያ መልቀም የሚችሉበት መብት ጭምር ተችሮአቸው ነበር። እንዲህ ዓይነቱ "መጻተኞችን" የመንከባበከብ ተግባር በጥንቱ ዓለም የተለመደ አልነበረም። እንዴት ለሌሎች አለኝታ መሆን እንዳለብን የሚነግሩን በእጅጉ አስፈላጊ የግብረገብ መርኅዎች እነሆ ዛሬም በአንዳንዶች የተዘነጉ ይመስላሉ።

**በሌሎች ላይ በሚደርሱ ሥቃዮችና የፍትሕ መጓደሎች ይበልጥ እንዲራሩ የሚያደርግዎ ምን ዓይነት ትውስታ አሎት?**

**ረቡዕ** **ሐምሌ 3**

## የአሥራት አሥራት (ሁለተኛ አሥራት)

አያሌ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሥራት የሚሰጠውን ትእዛዝ በሙሉ ልባቸው አምነው በመቀበል አሥራታቸውን ይመልሳሉ። በሚልክ. 3፡10 በቀረበው ቀላል ቀመር መሰረት አማኞች ከገቢያቸው አንድ አሥረኛውን ይመልሳሉ። ወይም ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማሰራጨት የምትሠራውን ሥራ በመደገፍ በዚያ ላይ አክለው ይሰጣሉ። የምዕመኑን አሥራት አደራ የተቀበሉት ቤተ ክርስቲያኖች ስለ ገንዘቡ አጠቃቀም ጥብቅ መመሪያ ያላቸው ሲሆን፤ ለወንጌል አገልግሎት ቀጥተኛ ድጋፍ ቅድሚያ ይሰጣሉ።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘዳ. 14፡22-29። በቀረቡት መመሪያዎች መሰረት አሥራት የመመለስ ተቀዳሚው ዓላማ ምንድን ነው?

---

---

ከአሥር አንድ በመመለስ አሥራታችንን ስንከፍል የሚፈለግብንን እንዳሳካን አድርገን በማሰብ እንፈተናለን። ነገር ግን ለእስራኤላውያን የተሰጡት መመሪያዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ አሥር ከመቶው መነሻ ነጥብ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዘሌዋውያን ሕግና ደንቦች መሰረት ይኖሩ የነበሩ የጥንት እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ሥራ፣ ካህኑንና ቤተ መቅደሱን ለመደገፍ እንዲሁም ድኾችን ለመደገፍ ከዓመቱ ገቢያቸው ከእሩብ እስከ አንድ ሦስተኛ የሚሆነውን በመደበኛ ይሰጡ ነበር።

አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን፤ በተለይ መጻተኞችን፣ ወላጅ የሌላቸውን ህፃናትና ባሏ የሞተባትን መበለት ለመደገፍ ይውል የነበረውን ስጦታ እንደ ሁለተኛ አሥራት አድርገው ይገልጹታል። ሕዝቡ በሥራው ውጤትና በሰበሰበው ምርት ሞገስ ማግኘቱና ደስ መሰኘቱ እሙን ነው። እስራኤላውያን በተለይ በአዲሱ ምድራቸው እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ቃል ገብቶላቸው የነበረ ቢሆንም፤ እነርሱ ግን የተሰጣቸው በረከት ሁሌም በእጃቸው እንደሚሆን በማሰብ ዝቅ አድርገው ተመለከቱት።

በመደበኞቹ ዓመታት ከሰበሰቡት ምርት የተጠቀሰው መጠን ለቤተ መቅደሱ እንዲገባ ይደረግ ነበር። ሆኖም በየሦስት ዓመቱ ግን ያገኙትን በረከት ለገዛ ማኅበረሰባቸው የማጋራት ልዩ ትኩረት ይደረግ ነበረ። መከር የሚሰበሰብባቸው የፌሽታ ጊዜያቶች

በቀላሉ ችላ ሊባሉ ወይም ሊዘነጉ የሚችሉ ወገኖች ላይ ልዩ ትኩረት ይደረግ ነበር፡ “የአሥራት ዓመት የሆነውን የሦስተኛውን ዓመት ምርት አንድ ዐሥረኛ ለይተህ ካወጣህ በኋላ በየከተሞችህ ውስጥ በልተው እንዲጠግቡ ለሌዋዊው፣ ለመጻተኛው፣ አባት ለሌለውና ለመበለቲቱ ስጣቸው” (ዘዳ. 26፡12)።

እግዚአብሔር በሰጠው መመሪያ መሰረት እስራኤላውያን ከሚሰጡት ስጦታ ቢያንስ የተወሰነው ክፍል የገንዘብና ሌሎች ተጨባጭ ድጋፎች ለሚያስፈልጓቸው ወገኖች እንዲውል ይደረግ ነበር። አሁንም ቢሆን ይህ ችሮታ እግዚአብሔር ምን ያህል ለእነርሱ መሐሪና ጻድቅ እንደሆነ አድናቆታቸውን የሚገልጡበትን ትውስታ መሰረት ያደረገ ነበር።

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘዳ. 26፡1-11። ጌታ ምን እያላቸው ነው? በችግር ላሉ ስለ መስጠት አስመልክቶ ይህን ለየራሳችን መተግበር የምንችለው እንዴት ነው?**

## ሐሙስ ሐምሌ 4

## የኢዩቤልዩ ዓመት

የገዛ ራሳቸው መኖሪያ ቤት የሌላቸው፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመድረስ ይጠባበቁ የነበሩ እስራኤላውያን እንደ ሕዝብ አዲሱ ማኅበረሰባቸው በከነዓን የመቋቋሙን አስፈላጊነት እግዚአብሔር ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። በኢያሱ መሪነት እንደ የጎሳቸውና ቤተሰባቸው ምድሪቱን ሥርዓት ባለው አመዳደብ ይከፋፈሉ ዘንድ እግዚአብሔር ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ሠርቶ ነበር።

እንዲሁም ከመሬት ስሪት ጋር በተያያዘ ሐብት፣ ምቹ ሁናቴዎችና ብልጽግና በጥቂት ሰዎች እጅ ሊወድቅ እንደሚችልም እንዲሁ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮች፣ የጤና እክል፣ ደካማ ምርጫና ውሳኔ--እንዲሁም አንዳንዶች ለአጭር ጊዜ ጥቅም ወይም ለጊዜያዊ ችግር መፍቻ ብለው ይዞታቸውን ይሸጣሉ። ታዲያ ይህ እንደ ዋዛ የሚደረግ ውል ቤተሰቡን ለተከታታይ ትውልዶች ከርስት የመንቀል አደጋ ያስከትላል።

መሬት ፍጹም እንዳይሸጥ መደንገግ አምላካዊው መፍትሔ ነበር። ሆኖም መሬት እስከ ቀጣዩ “የኢዮቤልዩ ዓመት” ብቻ እንዲሸጥ ተወስኖ የነበረ ሲሆን፤ በዚህ ወቅት ተሸጦ የነበረ ርስት ወደ ቀድሞው ቤተሰብ ይመለስ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ርስቱን የሸጠ ግለሰብ በማንኛውም ጊዜ ይዞታውን ዋጅቶ ማስመለስ ወይም የቅርብ ዘመዱ መሬቱን ሊዋጅለት ይችል ነበር። “መሬት ለዘለቄታ አይሸጥ፤ ምክንያቱም ምድሪቱ

የእኔ ናት፤ እናንተም መጻተኞችና እንግዶች ናችሁ" (ዘሌዋ. 25፡23)።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘሌዋ. 25፡8-23)። እነዚህ መርኅዎች ጥቅም ላይ ቢውሉ ኖሮ ማኅበረሰቡ ከዛሬው ምን ያህል የተለየ ሊሆን ይችል ነበር ብለው ያስባሉ? በተለይ አንዱ ሌላውን አይጨቁን ከሚለው አባባል አኳያ?

"እግዚአብሔር እነዚህን ደንቦችና መተዳደሪያዎች የቀየሰው ማኅበራዊ እኩልነትን ለማስፈን ነው። የሰንበት ዓመትና ኢዮቤልዩ--በህዝቡ ማኅበራዊና ፖለቲካ ኢኮኖሚ የተፈጸሙ ልዩነቶችን ለማስወገድ የተቀየሱ ማስተካከያዎች ናቸው።" (የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገጽ 613 /አማርኛው ትርጉም/)

እነዚህ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የምጣኔ ሐብትና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምን ያህል ሙሉ ለሙሉ በሥራ ላይ መዋላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ምሑራን እርግጠኞች አይደሉም (2ዜና 36፡21)። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕጎች ሙሉ ለሙሉ ተከትለው ቢሆን ኖሮ ዓለም ምን ትመስል እንደ ነበር በውልብታም ቢሆን በእነዚህ መሳጭ ደንቦች ማየት እንችላለን። በተጨማሪ እግዚአብሔር ለድኾችና ዝቅ ተደርገው የሚታዩ ወገኖች ስላለው ስጋት አጽንኦት ይሰጣሉ። እንዲሁም ሚዛናዊነት በዓለማችን በተጨባጭ እንዲታይ ያለውን ጭንቀትም ያሳያል።

## አርብ ሐምሌ 5

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, *"The Law Given to Israel," pp. 303–314; "God's Care for the Poor," pp. 530–536, in Patriarchs and Prophets.*

"እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከተቀበሉና እንደ ፈቃዱ መመላለስ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ሙሴ እንዳዘዘው ድሖችን ከማሰብና ለእነርሱ የርኅራኄና የእንክብካቤ መንፈስ ከማሳየት የላቀ ነገር የለም። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ህዝቡን አብልጦ ለመባረክ ቃል ቢገባም፤ ነገር ግን ድህነትን ሙሉ ለሙሉ ሳያውቁ ይቀሩ ዘንድ

እቅዱ አልነበረም። በመሆኑም ከምድሪቱ ድሖች ፈጽሞ እንዲጠፉ እንደማይፈልግ ገልጾአል። ቸርነት፣ ለጋስነትና ድጋፍ የሚጠብቁ ወገኖች በሕዝቦቹ መካከል መኖራቸው ይቀጥላል። ያን ጊዜም እንደ ዛሬው በሰዎች ላይ መጥፎ ዕድል፣ ህመምና ድህነት ይደርስ ነበር። ሆኖም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተከትለው እስከኖሩ ድረስ በመካከላቸው ለማኞች ወይም ምግብ አጥቶ የሚቸገር አልነበረም።" (የኃይማኖት

አባቶችና ነቢያት ገጽ 609 /አማርኛው ትርጉም/)

*"እነዚህ ደንቦች የተቀየሱት ባለጸጋውን ከድኻው ባላነሰ ለመባረክ ነው። ስስትና ራስን ከፍ የማድረግ አባዜ እንዲታቀብ በማድረግ የደግነትን ታላቅ መንፈስ ይቀርጻሉ። በሁሉም መደቦች መካከል ቅን ልቦናና መተማመን እንዲፈጠር በማድረግ አገርን የሚያረጋጋ ማኅበራዊ ሥርዓት ያዳብራሉ። ሁላችንም የተሠራነው በታላቁ ሰብዓዊነት ድርና ማግ እንደመሆኑ ሌሎችን ለመጥቀምና ለማገሳት የምናደርገው ተግባር በረከት ሆኖ በላያችን ያንጸባረቃል።"* (የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገጽ 614 /አማርኛው ትርጉም/)

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

***1.ሙሴ እና የእስራኤል ሕዝቦች ስለሚመሰርቱት ማኅረሰብ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ንድፍ ውስጥ የእርስዎን ትኩረት የሳበው የትኛው ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ ነው? (በዚህ ሣምንት ትምህርቱ ከቀረበው ወይም እርስዎ በተጨማሪ ሲያነቡ ካገኙት)***

***2.እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጠው ሕጎች ውስጥ ትኩረቱ ለጉዳት ተጋላጭ ወገኖች ላይ የሆነው ለምን ይመስሎታል?***

***3.ዛሬ እነዚህን ሕጎች እንዴት ማስተዋልና ከራሳችን ጋር ማዛመድ እንችላለን? ከእነዚህ መካከል ከዛሬው የእኛ ሁኔታ ጋር ሊሠሩ የሚችሉትንና የማይችሉትን መምረጥ የምንችለው እንዴት ነው? እስራኤላውያን ማኅበረሰባውንና ህይወታቸውን በሥርዓት ከመሩባቸው ከእነዚህ በዝርዝር ከቀረቡ መመሪያዎች የምንማረው በጣም አስፈላጊ ነገር የትኛው ነው?***

*ማጠቃለያ፡ በምድረ ግብፅ በባርነት ሥቃይ ውስጥ የነበሩትን እስራኤላውያን የልቅሶ ድምጽ የሰማው እግዚአብሔር እነሆ ሊያድናቸው ጣልቃ ገባ። ምንም እንኳ እሰራኤላውያን የተረሱ፣ ከሌላው ሕዝብ በእኩል የማይታዩና ደካሞች ቢመስሉም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር በዓይነቱ ልዩ የሆነ የኪዳን ግንኙነት ለመመስረትና ለሁሉም በረከት የሚሆን አዲስ ማኅበረሰብ ለመፍጠር አብሮአቸው መሥራት ተመኘ።*

# 3ኛ ትምህርት

**ከሐምሌ 6-12**

# ሰንበት፣ የነፃነት ቀን

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘፀ. 16:16–18፣ ዘፀ. 20:8–11፣ ዘዳ. 5:12–15፣ ማቴ. 12:9–13፣ ዘሌዋ. 25:1–7።*

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-**“ሰው ለሰንበት ተፈጠረ እንጂ ሰንበት ለሰው አልተፈጠረም”” (ማር. 2፡ 27)።

እግዚአብሔር በፍጥረት ሥራው ሣምንት መደምደሚያ ላይ ሰንበትን ፈጠረ። እርሱ በሰባተኛው ቀን ማረፍ ብቻ ሳይሆን ለምድር መፈጠር መሰረታዊ ክፍል የሆነውንም እረፍት እንደ ፈጠረ ሲነገር ይደመጣል። ሰንበት ከእግዚአብሔር ጋር ብሎም እርስ በርሳችን ትስስር እንድንፈጥር ሆነን የመፈጠራችን ማሳያ ነው።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያቀደውና ከትእዛዛቶቹ አንዱ የሆነው ሰንበት፤ ጥንት አዲስ ሆኖ የተቋቋመው የእስራኤል ሕዝብ እንደጠበቀው መመልከት ብዙም ላያስገርም ይችላል። ሰንበት በቀደሙት ዕብራውያን ህይወት ቁልፍ ሚና ነበረው።

ብዙውን ጊዜ ሰንበትን አስመልክቶ ስናወራ--እንዴት እንጠብቀው? የሚለው ሃሳብ ፈጥኖ ይንጸባረቃል። ማድረግ የሌለብን ነገሮች ምንድን ናቸው? ያለብንስ? ምንም እንኳ እነዚህ ጥያቄዎች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ የአምላካዊው ጸጋና ስጦታ ተምሳሌት የሆነው ሰንበት--በዓለምና በእግዚአብሔር ሕዝቦች ህይወት የራሱ ሚና እንዲሚኖረው ሆኖ የተነደፈበትን መሰረታዊ ዕቅድ ማስተዋል ይኖርብናል።

የሱስ እንደተናገረው ሰባተኛው ቀን ሰንበት የተፈጠረው ዘር ቀለም ሳይል ለሁሉም ሰብዓዊ ፍጡራን ነው። የሰንበትን ቀን በእውነት ስናስብ በሣምንቱ እያንዳንዱ ቀን የተለወጥን እንሆናለን። የሱስ እንዳሳየው--ሌሎችን መባረኪያ መንስኤ መሆንም ይችላል።

# እሑድ ሐምሌ 7

## በቂ መና

እስራኤላውያን የማይፈልጉትን እንዲቀበሉ ከተገደዱባቸው አያሌ ትውልዶች ካለፉበት የባርነትና የማኅበራዊ ዝቅታ ዘመን በኋላ--እግዚአብሔር ይህን አዲስ የነፃነት ባለቤት የሆነ ሕዝብ ወደ ተሻለ የአኗኗር ዘይቤ እያመላከተና ምርጥ የሆኑ ሕግና ደንቦችን እየሰጠ ወደ ወደ ከፍታ የማምጣት ምኞት አደረበት። ይህ ሂደት እውን ከሆነባቸው የመጀመሪያ ክፍሎች አንዱ ተግባራዊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን የተከተለ ነበር።

እስራኤላውያን ለቀጣዮቹ 40 ዓመታት በምድረ በዳ ባደረጉት መንከራተት ያለፉባቸው የህይወታቸው ክፍል፤ ማለትም በገሃድ የተመለከቱት አምላካዊ እርዳታና ራስ ወዳድ ያልሆነ ፍቅር--የእስራኤል ማኅበረሰብ ባህል አካል መሆን በቻለ ነበር። እስራኤላውያን ባረፉባቸው ሰፈሮች ሁሉ ሁሌም ማለዳ ላይ የሚበሉት መና ይወርድላቸው ነበር።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 16፡16-18። እያንዳንዱ ሰው የተወሰነ መጠን ያለው መና እንዲያገኝ አጽንኦት መሰጠቱ ለምን ይመስሎታል

---

---

---

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 8፡10-15 መልእክቱ ክርስቲያኖች እንዴት ሊሰጡ እንደሚገባ አስመልክቶ ይህንኑ ታሪክ ይጠቅሳል፡ "በአሁኑ ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ያሟላል፤ የእነርሱም ደግሞ በተራው የእናንተን ጉድለት ያሟላል። በዚህም ያላችሁን እኩል ትካፈላላችሁ" (ቁ. 14)።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ እና ለፍጥረታቱ በለጋስነት መስጠቱ ለእስራኤላውያን ብሎም ለእኛ የቀረበ ትምህርት ነው። የሚያስፈልገንን ብቻ ወስደን ትርፍ የሆነውን ለሌሎች ለማካፈል ዝግጁ ከሆንን የሚራብም ሆነ የሚጠማ አይኖርም። ሕዝቡ ለዕለቱ የሚያስፈልገውን በቂ መጠን ብቻ መውሰዱ በቀጣዩም ቀን ሌላ ተጨማሪ አለ ብሎ መተማመን እንዲያድርበት ያደርጋል። ልክ እንደ እስራኤላውያን በባርነት ቀንበር ውስጥ ያለፉ ሕዝቦች ትኩረታቸው የተቃኘው ከገዛ ህልውናቸው አኳያ ብቻ

ነው። እግዚአብሔር ግን የመታመን፣ የሊጋስነትና የማካፈል ሕይወት ሊያሳያቸው ወደደ።

ለእስራኤላውያን ይወርድ ከነበረው መና ጋር በተያያዘ ሌላም አስደናቂ ክስተት የነበረ ሲሆን፤ ይኸውም በየሣምንቱ ዓርብ ከሌላው ቀን እጥፍ መጠን የነበረው መና ለእነዚህ ሕዝቦች መውረዱ ነው። በመሆኑም በዚያ ቀንና በዚያ ቀን ብቻ-- ሕዝቡ ለሰንበት ዝግጅት ያደርግ ዘንድ ከተለመደው እጥፍ መና ይሰበስብ ነበር። ሰንበትን አስመልክቶ የተሰጣቸው ልዩ ደንብ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ በጌታ መታመንን የሚማሩበትን ተጨማሪ ዕድል ከፈተላቸው። ይህ የአምላካዊው ጸጋ አካል የሆነው ተጨማሪ መና፤ በሰባተኛው ቀን ሰንበት በማረፋቸው እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ደስታ ይበልጥ በሙላት እንዲያገኙ አስቻላቸው።

**እግዚአብሔር በሰጠን ሰንበት በተሻለ ሐሴት ማድረግ እንችል ዘንድ በዋዜማው አርብ፤ ምን ማከናወን ይኖርብናል?**

**ሰኞ** **ሐምሌ 8**

## ሰንበትን የምንጠብቅባቸው ሁለት ምክንያቶች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 20፡8-11፣ ዘዳ. 5፡12-15። እነዚህ ስለ አራተኛው ትእዛዝ የሚናገሩ ሁለት ሐተታዎች እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና ምን ይመስላል?

---

---

እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና አዳኛችን የመሆኑ ሐቅ ላይ ማዕከል ያደረገውን የቀደመ ግንኙነት ማስታወስ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ዳግመኛ ለመመስረት ለፈለገው ግንኙነት አንዱና በእጅጉ አስፈላጊው ክፍል ነው። ሁለቱም ሚናዎች በሁለቱ ሐተታዎች በቀረበው አራተኛው ትእዛዝ የታዩ ሲሆን፤ ይኸውም ከሰንበት እና አጠባበቁ ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው።

ስፍር ቁጥር የሌላቸው አማልክት ከሚመለኩበት ምድረ ግብፅ ተጽእኖ የወጡት እስራኤላውያን እውነተኛው አምላክ እንደ ፈጣሪነቱ ስለሚኖረው ሚና

እንዲያስታውሱ መደረግ ነበረባቸው። እስራኤላውያን በየሣምንቱ አርብ ከሌሎቹ ቀናት እጥፍ መና እንዲቀበሉ የተደረጉበት ዐውድ--የፈጣሪነቱ ብርቱ ምሳሌ የሆነው ሰንበት ትውስታን ለማምጣት እጅግ ወሳኝ ነበር። በዘፀ. 20 በቀረበው የአራተኛው ትእዛዝ ሐተታ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ ተገልጦአል።

እነዚህ ሕዝቦች ከባርነት ቀንበር ነፃ መውጣታቸው፣ መዋጀታቸውና መዳናቸው የአራተኛው ትእዛዝ ትኩረት ስለመሆኑ ከዘዳ. 5 ጋር በማነጻጸር መመልከት እንችላለን። ይህ እስራኤላውያን በተለይ በየሣምንቱ ሰንበት መልሰው፣ መላልሰው ሲያወሩት የሚኖሩት ታሪክ ነበር። ቀዳሚውና ከአፋቸው የማይጠፋው፤ ከግብፅ ባርነት በተጨባጭ፣ በአካል የወጡበት ታሪክ ሲሆን--ስለ እግዚአብሔርና አዳኝነቱ ያላቸው መረዳት በጎለበተ መጠን፤ ሰንበትም እንዲሁ ሣምንታዊ ምልክትና የመንፈሳዊ ደኅንነታቸው ክብረ በዓል ሆነላቸው።

ስለ ሰንበት የተጻፉት የእነዚህ ሁለት ሐተታዎች ሰበበ ድርጊት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መሃል ያለውን ግንኙነት ወደ ቀደመው ንጽህና መመለስ ነበር፡ “ ‘ “ደግሞም እኔ እግዚአብሔር እንደ ቀደስኋቸው ያውቁ ዘንድ፣ በእኔና በእነርሱ መካከልም ምልክት እንዲሆን ሰንበቴን ሰጠኋቸው” ’ ” (ሕዝ. 20፡13)። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ትእዛዙ የተሰጠው ለእነዚህ ሕዝቦች ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በዚህ የግንኙነት መሰረት ከእነርሱ ውጪ ለሆነው ሕዝብ መልካም፣ ለመላው ዓለም ደግሞ በረከት የሆነ በዓይነቱ ልዩ ማኅበረሰብ መመስረት ነበረባቸው።

“ ‘ስለዚህ አምላክህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ታከብረው ዘንድ አዘዘህ’ ” (ዘዳ. 5፡15)። ሰንበት የተፈጠርንበትና የተዋጀንበት ምልክት መሆኑን እያስታወስን ከጌታ ጋር ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ካሉ ወገኖች ጭምር ግንኙነት እየፈጠርን ማደጋችንን መቀጠል እንችላለን። እግዚአብሔር ለእኛ ቸር፣ ሊጋስና መሐሪ እንደሆነ ሁሉ እኛም ለሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ እናሳይ።

**ሰንበት መጠበቃችን በተሻለ ለሌሎች መልካም፣ ጥንቃቄ የሚያደርግና ርኅሩኅ ህዝብ የሚያደርገን እንዴት ነው?**

## ማክሰኞ ሐምሌ 9

# የእኩልነት ቀን

በዘፀ. 20 እና ዘዳ. 5 የቀረቡትን ዐሥርቱን ትእዛዛት ላይ ላዩን ገረፍ ስናደርግ ከሌሎቹ ይልቅ ለአራተኛው ትእዛዝ ሰፋ ያለ ዝርዝር መረጃ መሰጠቱን እንረዳለን። ምንም እንኳ ከዐሥርቱ ትእዛዛት መካከል አንዳንዶቹ በሁለት ቃላት (በዕብራይስጥ በቀረበው) ብቻ መገለጥ ቢችሉም፤ አራተኛው ትእዛዝ ግን ለምን፣ እንዴት እና ማን ሰንበትን ማስታወስ እንዳለበት አስመልክቶ ተጨማሪ ሀሳብ ይሰጣል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 20፡8-11። ስለ ቤት ውስጥ ወንድም ሆነ ሴት ሠራተኞች፣ ስለ እንግዶች እንዲሁም ስለ እንስሳት ሳይቀር ምን ይላል? ምን ለማለት ነው የተፈለገው?

---

---

ስለ ሰንበት ከተሰጡት ዝርዝሮች ወስጥ በቤት ውስጥ ስለሚያገለግሉ ወገኖች የቀረበው ትኩረት ልዩ አጽንኦት የሚሰጠው ነው። ይህ ዓይነቱ ትእዛዝ በዓለም ዙሪያ ካሉ ባህሎች በእጅጉ የተለየ ነው ሲሉ ሲግቭ ኬ. ቶንስታድ ይሞግታሉ። “በጀመሪያ ለደካሞችና ለጉዳት ተጋላጭ የማኅበረሰቡ አባላት ቅድሚያ የሚሰጠው የሰንበት ትእዛዝ፤ ከላይ ወደታች ሳይሆን ከታች ወደ ላይ ሲወጣ ይታያል። ሌት ተቀን በሥራ ተጠምደው የሚኖሩትና በእጅጉ እረፍት የሚያሻቸው ባሮች፣ በእንግድነት የተጠጉ ሰዎች እንዲሁም መደበኛውን የሸክም አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ የጋማ ከብቶችና ሌሎች አገልጋይ እንስሳት በተለየ ለተጠቀሰ ጉዳይ እንዲያርፉ ተደርገው ነበር።”— The Lost Meaning of the Seventh Day (Michigan: Andrews University Press, 2009), pp. 126, 127.

ሰንበት እያንዳንዱ ሰው የሚያርፍበትና ሐሴት የሚያደርግበት ዕለት በመሆኑ ዙሪያ ትእዛዙ ልዩ ትኩረት ያደርጋል። እኛ ሁላችን በሰንበት ብርሃን ስንታይ እኩል ነን። ለምሳሌ እርስዎ በሣምንቱ ውስጥ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞችን የሚቀጥሩ ቢሆኑ፤ የቀጠሯቸውን ሰዎች በቅዳሜ ቀን የማሠራት ሥልጣን ሊኖርዎት አይችልም። ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ለእነርሱም የሚያርፉበትን ቀን ስለ ሰጣቸው ነው። ምናልባት እርስዎ ተቀጥረው የሚሠሩ ወይም ከነጭራሹ ባሪያ ቢሆኑ ደግሞ--ከሁሉም ሰው ጋር በእኩል የተፈጠሩና በእግዚአብሔር የተዋጁ መሆንዎን የሰንበት

ዕለት ያስታውሶታል። ከሌሎቹ በሥራ ኃላፊነት ተጠምደው ከሚያሳልፏቸው የሣምንቱ ቀናት ይልቅ በዚህኛው ሐሴት እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ግብዣ ያቀርብሎታል። ትእዛዙ ሰንበትን ከሚጠብቁ ውጪ ያሉትን ሕዝቦች ጨምሮ "በግቢ ያለ መጻተኛም" (ዘፀ. 20፡10) ከሰንበት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል።

ይህ ጽንሰ ሃሳብ ከባርነት እና ዝቅ ተደርጎ የመፈረጅ ተሞክሮ ገና በቅጡ ባልወጡት እስራኤላውያን አመለካከት ላይ አስደናቂ ለውጥ ማምጣት ነበረበት። በአዲሲቱ ምድር ለመቋቋም በቅርብ ሂደት ላይ የነበሩት እስራኤላውያን፤ የቀድሞ ጨቋኞቻቸውን አስከፊ ልማድ የራሳቸው አድርገው እንዲቀጥሉበት የእግዚአብሔር አምላክ ፍላጎት አልነበረም። ጌታ ለማኅበረሰባቸው ዝርዝር ሕጎችን ከመስጠቱ በተጨማሪ ሁላችንም በፊቱ እኩል መሆናችንን የሚያስታውሰንን የሣምንቱን አስተዋሽ ሕግ (ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር) ሰጠ።

**ሰንበትን እንዴት ለማኅበረሰብዎ ማካፈል ይችላሉ? ማለትም--ሌሎች ከእርስዎ ሰንበት ጠባቂነት እንዴት መጠቀም ይችላሉ?**

## ረቡዕ ሐምሌ 10

## የፈውስ ቀን

የቀደመው የሰንበት እይታ ብሎም የሰንበት አጠባበቅ ሰፊና ሁሉን አካታች የነበረ ቢሆንም፤ ነገር ግን የሱስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ሰንበት ለብዙ የኃይማኖት መሪዎች ከቀደመው ድንጋጌ በእጅጉ የተለየ ገጽታ እንዲይዝ ተደርጎ ነበር። ዕለቱ የነፃነትና የእኩልነት ቀን በመሆን ፋንታ--የሰው፣ የባህላዊ ወጎችና የክልከላ መሣሪያ ሆነ። የሱስ በምድር ይመላለስ በነበረ ጊዜ ከእንዲህ ዓይነቱ መንፈስ በተቃራኒ ቆሞ ነበር--በተለይ በሌሎች ላይ ከሚቆለል ጫና!

የሱስ በሰንበት ቀን ብዙ ፈውሶችን በማድረግ ያን የቀደመ ጽንሰ ሃሳብ ሲያንጸባርቅ መመልከት በእጅጉ ደስ ያሰኛል። የሱስ ስለ ሰንበት የተሸሸገውን ነገር ለማሳየት በመፈለግ ከሌሎቹ ቀናት በተቃራኒ ሆነ ብሎ በሰንበት እነዚህን ታምራቶች ማድረጉን ለማስተዋል ብዙም አያዳግትም። እርሱ በሰንበት ቀን መፈወሱ ተገቢ መሆኑን አስመልክቶ በታሪኮቹ በተደጋጋሚ አስተያየት መስጠቱ የተመለከተ ሲሆን፤ ፈሪሳውያንም እነዚህኑ ንግግሮቹን የሱስን ለመግደል ለጠነሰሱት ሤራ እንደ ግብአት ተጠቅመውባቸዋል።

የሱስ በሰንበት የፈወሰባቸውን ታሪኮች ያንብቡ፡ ማቴ. 12:9–13፣ ማር. 1:21–26፣ 3:1–6፣ ዮሐ. 9:1–16። በታሪኮቹ ያስተዋሏቸው የላቀ ትርጉም ያዘሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

---

---

---

የሱስ ሰንበትን ስለ ማክበር አስፈላጊነት ማረጋገጫ ሰጥቶአል። የሰንበትን ቀን በተለየ መንገድ ለመጠበቅና ይህን ሣምንታዊ ጊዜ ከእግዚአብሔር አምላክ፣ ከቤተሰባችን፣ ከቤተ ክርስቲያናችንና ከማኅበረሰባችን ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሳደግ መጠቀም እንድንችል በሰንበት መግቢያና መውጫ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል። ደግሞም የሰንበትን ቀን ስለ ራሳችን ብቻ በማሰብ በራስ ወዳድነት ማክበር የለብንም። ይልቁንም የሱስ እንዳለው "'በሰንበት ቀን በጎ ማድረግ ተፈቅዶአል' " (ማቴ. 12፡12)።

ብዛት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት ለሌሎች ጥንቃቄ የማድረግ መጠነ ሰፊ ሥራ ይሠራሉ። ሆኖም ከዚህ በላቀ መሥራት እንዳለብን ብዙዎቻችን ይሰማናል። እግዚአብሔር ለተጎዱ፣ ለተጨቆኑ ወይም ለተዘነጉ እንደሚጠነቀቅ የምናውቅ እንደመሆኑ እኛም ይህንኑ ማድረግ ይኖርብናል። በሰንበት መደበኛ ሥራችንን ከመሥራት ታቅበንና ከሥራ ጫና ነጻ ሆነን፤ ዕለቱን በእውነተኛ መንገድ ከምናከብርባቸው መንገዶች አንዱ ለሌሎች ያለንን ተቆርቋሪነት በማሳየት ነው። "በአራተኛው ትእዛዝ እንደቀረበው ሰንበት ከሌሎቹ የሣምንቱ ቀናት ተለይቶ ለዕረፍትና ለመንፈሳዊ አምልኮ እንዲውል ታስቦ ተሰጥቶአል። ሁሉም ዓለማዊ ሥራዎች በዕለቱ እንዳይሠሩ ሲከለከሉ--ከጌታ ተግባር ጋር አብረው የሚሄዱት የምኅረትና የቸርነት ሥራዎች ይኸውም . . . ሥቃይን ማስታገስና ያዘኑትን ማጽናናት--ለእግዚአብሔር ቅዱስ ቀን ክብር የሚሰጥ የፍቅር ሥራ ነው።"—Ellen G. White, Welfare Ministry, p. 77.

**በሰንበት ቀን ለሌሎች ምን ዓይነት መልካም ተግባሮች ያደርጋሉ?**

**ሐሙስ** **ሐምሌ 11**

# የሰንበት ዕረፍት ለምድሪቱ

ሰንበት ሥር የሰደደ የእስራኤል ሕዝብ የሕይወት ዑደት አንዱ ክፍል መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። ሆኖም የሰንበት መርኅ በሣምንት አንድ ቀን ከሚመጣው ዕለት ጋር ብቻ የተቆራኘ አልነበረም። ይልቁንም በሰባት ዓመት አንዴ የሚመጣውንም የተለየ ዕረፍት ያካትት የነበረ ሲሆን፤ መደምደሚያው ግን ሰባት ጊዜ ሰባት ተባዝቶ ከሚገኘው አርባ ዘጠኝ ዓመት በኋላ ያለው 50ኛ ዓመት ወይም የኢዮቤልዩ ዓመት ነበር።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፥ ዘሌዋ. 25፥1-7። እንዲህ ዓይነቱን መመሪያ አስደናቂ የሚያደርገው ምንድን ነው? ይህ ዓይነቱን መርኅ ከህይወትና ከሥራዎ ጋር ማቆራኘት የሚችሉት እንዴት ነው?

---

---

የሰንበት ዓመት የእርሻው መሬት ለአንድ ዓመት ጦም እንዲያድር የሚፈቅድ ድንጋጌ ነበር። ይህ ዓይነቱ መሬቱን የመመገብ አስደናቂ ተግባር እና የእርሻ ጥበብ በብዙዎች ዘንድ በስፋት ሲታወቅ ኖሮአል።

ሰባተኛው ዓመት ለባሮችም ቢሆን ታላቅ ትርጉም ነበረው (ዘፀ. 21፥ 1-11)። ማንኛውም በእዳ ተዘፍቆ ራሱን የሸጠ እስራኤላዊ ሰባተኛው ዓመት ላይ ነጻ ይሆን ነበር። በተመሳሳይ ከፍተኛ መጠን የነበራቸው ዕዳዎች በሰባተኛው ዓመት መጨረሻ ይሰረዙ ነበር (ዘዳ. 15፥1-11)።

እስራኤላውያን በምድረ በዳ ጉዞአቸው እግዚአብሔር መና እንዳወረደላቸው ሁሉ፤ አሁንም ምንም ዓይነት ዘር ሳይዘሩና መከር ሳይሰበስቡ ካለፈው ዓመት የተትረፈረፈ ምርትና በዚህ የሰንበት ዓመት ምድሪቱ በራሷ ባበቀለችው ነገር ላይ ተስፋ በማድረግ፤ እግዚአብሔር በበቂ ሁኔታ ይመግበናል ብለው በእርሱ ላይ ያላቸውን መተማመን የሚያሳዩበት ወቅት ነበር። በተመሳሳይ ባሮችን አርነት ማውጣትና ዕዳቸውን መሰረዝ በራሱ የምኅረት ተግባር ቢሆንም፤ በተጨማሪ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ያሟላል ብሎ በአምላካዊው ኃይል ላይ እምነት መጣል ነው።

የሰንበት ጽንሰ ሃሳቦችና ንድፎች ከአጠቃላዩ የእስራኤል ማኅበረሰብ መዋቅር ጋር የቅርብ ትስስር እንዲኖራቸው የተቃኙ ነበሩ። በተመሳሳይ የዛሬው ሰንበት አጠባበቅ ሌሎቹን ቀኖቻችንን በሙሉ በሚለውጥ መንፈሳዊ ግብረገብነት የተሞላ መሆን ይጠበቅበታል። ሰንበት በቅድሚያ አምላካዊውን መንግሥት መሻት እንዳለብን አስመልክቶ የሱስ የሰጠውን መመሪያ በተግባር የምናሳይበት መሣሪያ ነው፡ "'የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል... እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል'" (ማቴ. 6፡32-33)።

**ሰንበትን መጠበቃችን በሌሎቹ ስድስት የሥራ ቀናት ላይ ምን ዓይነት ልዩነት ማምጣት ይኖርበታል? ለነገሩ ከእሁድ እስከ አርብ--ስስታም፣ ራስ ወዳድና ለሌሎች ግድ የማይሎት ሆነው ሰንብተው ሲያበቁ፤ በሰንበት ከዚህ በተቃራኒ መሆንዎ ፋይዳው ምንድን ነው?**

## አርብ ሐምሌ 12

ተጨማሪ ሀሳብ፡ *Read Ellen G. White, "From the Red Sea to Sinai," pp. 295–297, in Patriarchs and Prophets; "The Sabbath," pp. 281–289, in The Desire of Ages; Sigve K. Tonstad, "The Social Conscience of the Seventh Day," pp. 125–143, in The Lost Meaning of the Seventh Day.*

"በሥቃይ ያሉ ሰዎችን መከራ የማስታገስ ሥራ ከሰንበት ሕግ ጋር በተጓዳኝ እንደሚሄድ ጠቅሶላቸው ነበር። በሥቃይ ያለውን ሰብዓዊ ፍጡር ለማገልገል ሁሌም በሰማይና በምድር ከሚመላለሱ መላእክት ሥራ ጋር ለዛ ያለው ውህደት የፈጠረ ነበር...

"ሰውም እንዲሁ በዚህ ዕለት የሚያከናውነው ተግባር ተሰጥቶታል። በሰንበት ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሊታዩ፣ የታመሙ ተገቢውን እንክብካቤ ሊቸሩ፣ በድኽነት ያሉ ወገኖችም የጎደላቸው ሊሟላ ይገባል። የተቀደሰው የእግዚአብሔር የእረፍት ቀን ለሰዎች የተሠራ እንደመሆኑ፤ የምኅረት ሥራ ከእቅዱ ጋር ፍጹም ስምምነት አለው። በሰንበትም ሆነ በሌላ ቀን ፈውስ ማግኘት በሚችል ህመም ፍጡራኑ ለአንድ ሰዓት እንኳ ይሠቃዩ ዘንድ አምላካዊው ፈቃድ አይደለም።"—Ellen G. White, The Desire of Ages, pp. 206, 207.

# የመወያያ ጥያቄዎች:

1.ሰንበትን በእግዚአብሔር ላይ ያሎት መታመን ማሳያ አድርገው የተጠቀሙባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? በጌታ ላይ ላሳዩት መታመን በምላሹ እግዚአብሔር መና የመገቦት አጋጣሚዎች አሉ? ካለ በዚህ ዙሪያ የተማሩትን ለክፍሉ ያካፍሉ።

2.በዘፀ. 20፥8-11 እና ዘዳ. 5፥12-15 በቀረበው አራተኛ ትእዛዝ እግዚአብሔር የተለያዩ ገጽታዎች ለነበሯቸው ሰንበቶች አጽንኦት ሰጥቶ ነበር። እርስዎ የተለየ ስፍራ የሚሰጡት አንዱ የሰንበት ገጽታ የትኛው ነው?

3.የሰንበትን በረከቶችና ጥቅሞች ለማኅበረሰብዎ ማካፈል በሚችሉባቸው መንገዶች ዙሪያ በግልዎም ሆነ በክፍል ተወያዩ።

4.ሰንበት በሕይወትዎ ለውጥ እንዲመጣ ካደረገባቸው ነገሮች መሃል አንዳንዶቹ የትኞቹ ናቸው? የሰንበት ንድፎችና መርኅዎች መደበኛ ተጽእኖ ሊያሳርፉባቸው የሚገቡ ሌሎች የህይወትዎ ክፍሎች ይኖሩ ይሆን?

*ማጠቃለያ፡ እግዚአብሔር የፍጥረት ሥራንና መዋጀታችንን እንድናስታውስ ሰንበትን ቢሰጠንም፤ ሌሎች ብዛት ያላቸው ተጨባጭ ጥቅሞችም አሉ። ሰንበት በሚያስፈልገን ሁሉ በአምላካዊው ቸርነት ላይ እንድንታመን ያስተምረናል። እኩልነትን እንድንለማመድ በማስተማር--መላውን ግንኙነታችንን መለወጥ የሚችል መንፈሳዊ ግብረገብ መሆንም ይችላል። የሱስ በሽተኛውን በመፈወስ ሰንበት በዕጦት ያሉ ሁሉ የሚያተርፉበት ዕለት መሆኑን አሳየ።*

# 4ኛ ትምህርት

**ከሐምሌ 13-19**

# ምኅረት እና ፍትሕ በመዝሙረ ዳዊት እና በመጽሐፈ ምሳሌ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ መዝ. 9፡7–9፣ 13–20፣ መዝ. 82፣ መዝ. 101፣ መዝ. 146፣ ምሳ. 10፡4፣ ምሳ. 13፡23፣ 25፣ 30፡7–9።

**<u>የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-</u> “ለዐቅመ ቢሶችና ለድኻ አደጎች ፍረዱላቸው፤ የችግረኛውንና የምስኪኑን መብት አክብሩ። ወገን የሌለውንና ችግረኛውን ታደጉ፤ ከግፈኛውም እጅ አስጥሏቸው” (መዝ. 82፡3-4)።**

መዝሙረ ዳዊት እና መጽሐፈ ምሳሌ እንደው በአምልኮ ጊዜ ወይም በሌሎች ኃይማኖታዊ መርኀ ግብሮች ሳይሆን በተለመደው የዕለት ከዕለት ህይወት ከእግዚአብሔር ጋር የመኖርን ተሞክሮ ያካፍሉናል። መጽሐፈ ምሳሌ ከግንኙነት እና ቤተሰብ እስከ ንግድ ብሎም የመንግሥት አሠራር ልዩ ልዩ ተጨባጭ የጥበብ አማራጮችን ሲሰጠን--የመዝሙር መጽሐፍ ደግሞ ከሐዘን እንጉርጉሮ እስከ የእልልታ ምስጋና ያካተቱ የተለያዩ ስሜቶች እና መንፈሳዊ ተሞክሮዎች ስብስብ የሆኑ መዝሙሮችን ይዞአል። እግዚአብሔር ስለ እያንዳንዱ የህይወታችን ሁኔታ ግድ የሚለው አምላክ ከመሆኑ አኳያ እምነታችን በእያንዳንዱ ገጽታና ተሞክሮ ልዩነት ሲያመጣ መመልከት እምብዛም ላይከብድ ይችላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚህ በወደቀ ዓለም ማንኛውም የህይወት ነጸብራቅ የሰው ልጅ ሁኔታ ላይ የተንሰራፋውን የፍትሕ መጓደል ችላ ብሎ ማለፍ አይችልም። በእርግጥ ኢፍትሐዊነትን አስመልክቶ ጌታ ለወገኖቹ ጥንቃቄ እንደሚያደርግና ችግሩን ለማስታገስ እንደሚመኝ በተደጋጋሚ ገተልጾአል። ተስፋ ለሌላቸው ተስፋ የሆነው እነሆ እርሱ ነው።

ምንም እንኳ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በመጻሕፍቱ የቀረቡትን ሀሳቦች ገረፍ አድርገን ብቻ የምናልፍ ቢሆንም፤ ምናልባት በዙሪያችን የሚገኙ ድኾችን፣ የተጨቆኑትንና የተረሱትን ከማገልገል ብሎም ከመርዳት ግዴታ አኳያ የቀረበው ይህ ትምህርት ይበልጥ ወደ ተግባር እንዲገቡ ያነሳሳዎ ይሆናል።

## እሑድ ሐምሌ 14

## መዝሙረ ዳዊት፥ የተስፋ መዝሙር ለተጨቆኑ

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በችግርና በሥቃይ ውስጥ ያሉ ወገኖችን ይመለከታል፤ ይሰማልም። በእግዚአብሔር እየታመኑ ነገር ግን የፍትሕ መጓደል የገጠማቸውን ወገኖች የልቅሶ ድምፅ በመዝሙረ ዳዊት በተደጋጋሚ እንሰማለን። የአምላካዊው በጎነት፣ ፍትሕ እና ብርቱነት በተቃራኒው በተሰለፈ ኢፍትሐዊነትና ጭቆና ስር የወደቀ መስሎ በመዝሙሮቹ ድምጽ ውስጥ ይሰማል።

አዎ፤ ዛሬም በመዘመር ላይ ያሉት እነዚሁ መዝሙሮች ናቸው። የወገኖች ህይወትም ሆነ እምነት እነሆ ዛሬም አለ እንጂ አልጠፉም። አሁንም ተስፋ አለ። ክፉው ባለ ድል ከመሆኑ በፊት፣ የተጨቆኑት ሊሸከሙ ከሚችሉት በላይ በሚጫንባቸው መከራ ከመጥፋታቸው አስቀድሞ--ጉዳዩ ከቁጥጥር ሳይወጣ እግዚአብሔር ጣልቃ ይገባ ዘንድ ነጋ ጠባ ይወተወታል። የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ በእነዚህ ወገኖች የእምነት ማረጋገጫ እና በህይወት ፈተና መካከል ያለውን ክፍተት ለማገናኘት የሚሞክር ይመስላል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መዝ. 9፡7-9፣ 13-20። ባለ መዝሙሩ ዳዊት እነዚህን ስንኞች ሲጽፍ ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደ ነበር ለመገመት ይችላሉ? በእግዚአብሔር መልካምነት እና ዳዊት በወቅቱ በነበረው ተሞክሮ መካከል ያለው ውጥረት ሊሰማዎ ይችላል? ጽኑ ፈተና በገጠሞት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያሎትን እምነት ጠብቀው እንደያዙ ማለፍ የቻሉት እንዴ ነበር?

---

---

የእግዚአብሔር መልካምነትና ጻድቅ ፍርድ--ተስፋና ኪዳን ለዚህ ውጥረት ምላሽ በመሆን በመዝሙረ ዳዊት በተደጋጋሚ ቀርቦአል። ክፋትና ኢፍትሐዊነት ለጊዜው አሸናፊ ቢመስሉም፤ እግዚአብሔር ክፉ አድራጊዎችንና አመጻኞችን ይዳኛል። ጉዳት የደረሰባቸውና የተጨቆኑ ሲነጹና ወደ ቀደመው ንጽህና ሲመለሱ አመጻኞች ግን ፍርዳቸውን ያገኛሉ።

ሲ. ኤስ. ልዊስ በመባል የሚታወቁ ጸሐፊ ሪፍሌክሽንስ ኦን ዚ ሳልምስ በሚለው መጽሐፋቸው በመዝሙር መጽሐፍ በተደጋጋሚ በተገለጠው አምላካዊውን ፍርድ መናፈቅ ዙሪያ በመጀመሪያ የተሰማቸውን አግራሞት ይገልጣሉ። ዛሬ አያሌ መጽሐፍ

ቅዱስ አንባቢዎች አምላካዊውን ፍርድ የሚያስፈራ ነገር አድርገው እንደሚመለከቱ ማስተዋላቸውን የሚገልጹት እኚሁ ጸሐፊ፤ የቀደመውን የዕብራውያን አመለካከት በማጤን እንደሚከተለው ጽፈዋል፡ “ያፈሩትን ሐብት ንብረት የተገፈፉ በሺህ የሚቆጠሩ ባለመብቶች ድምፅ ቢያንስ በስተ መጨረሻ ይደመጣል። እርግጥ ነው እነዚህ ወገኖች ፍርድ አይፈሩም። የእነርሱ ጉዳይ ሊሰማ ይችል እንደሆን እንጂ ምላሽ እንዳጣ ያውቃሉ። በስተመጨረሻ--ጌታ ሊፈርድ ዳግም ሲገለጥ ግን ያኔ መፍትሔውም ይመጣል።”—C. S. Lewis, Reflections on the Psalms (New York: Harcourt, Brace and Company, 1958), p. 11.

በጭቆና፣ ምዝበራና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ላሉ ወገኖች እነሆ ዛሬም ተስፋ መኖሩን በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ እንመለከታለን።

**አምላካዊውን ፍርድ እንድንፈራው ሳይሆን በአዎንታዊ እንድናየው የሚያደርጉ ምን ዓይነት ምክንያቶች አሉን?**

## ሰኞ ሐምሌ 15

## “አምላክ ሆይ ተነስ፤ በምድር ላይ ፍረድ!”

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መዝ. 82። እዚህ ላይ የተሰጠን መልእክት ምን ይመስላል?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ማኅበረሰብ በታሪካቸው ብዛት ያላቸው ሕግና ደንቦች በተለያዩ ጊዜያቶች ሰጥቶአቸው የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ ግን በዚህ ዕቅድ መሰረት ከመኖር ተጨናገፈ። በቀላሉ በዙሪያቸው ከነበሩ ሕዝቦች ጋር በመመሳሰል ኢፍትሐዊና ጨቋኝ የአኗኗር ዘይቤ ተጽእኖ ስር ወደቁ። መሪዎችና ፈራጆች የግል ጥቅማቸውን ብቻ የሚያሳድዱ ሆኑ፤ ይሁንታቸው በጉቦ የሚገዛ ሆነ። ተራውን ሕዝብ፣ በተለይም ምስኪኑን የሚከላከል የሕግ ከለላ ባለመኖሩ ለጭቆናና ብዝበዛ ተጋላጭ ሆኑ።

መዝ. 82 ለእንዲህ ያለው ሁኔታ የተሰጠ ምላሽ ነው። እግዚአብሔር የፈራጆች ሁሉ ፈራጅ ሚና እንዳለው በመግለጽ የሕዝቡን መሪዎች እና ፈራጅ ዳኞች ሳይቀር እንደሚዳኝ ይሳያል። ይህ ክፍል አጽንኦት እንደሚሰጠው ከሆነ በማኅበረቡ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሚና መኖሩ የሚሰማቸው ሰዎች “በእርሱ ስር ፈራጆች ሆነው ይሾማሉ”—Ellen G. White, Prophets and Kings, p. 198. የእግዚአብሔር ተወካዮችና የበታቾቹ ሆነው ኃላፊነታቸውን በመረከብ ሥራቸውን ያካሂዳሉ። እንደ

ባለመዝሙሩ አመለካከት ከሆነ አምላካዊው ፍትሕ ምድራዊው ፍትሕ እንዴት መሥራት እንዳለበት የሚያሳይ ተምሳሌት ነው። ፍትሐዊነት ወይም ኢፍትሐዊነት የሚለካበት--ፈራጆቹም የሚዳኙበት ነው።

በዚያ አገር ተንሰራፍቶ በነበረው ኢፍትሐዊነት ላይ ጣልቃ ተገብቶ እንዲቆም እንዲደረግ በመጠቆም የዚህ ጽሑፍ ክፍል መልእክት ይደመደማል (መዝ. 82፡8)። እንደ አብዛኞቹ የባለ መዝሙሩ መልእክቶች ሁሉ ይህኛውም ድምጽ የሌላቸውና የተጨቆኑ--በሚኖሩበትና በሚሠሩበት ስፍራ ኢፍትሐዊ በሆነ ሥርዓት ጸጥ እንዲሉ የተደረጉ፤ ድምጻቸው እንዲሰማ ያደርጋል።

መዝ. 82--የሁሉ የበላይ ዳኛ ለሆነውና የዩኒቨርስ ብሎም የምድር መንግሥታት ሉዓላዊ ገዢው እግዚአብሔር አምላክ ተማጽኖ ያቀርባል። እንዲህ ዓይነቱ ልመና ሊቀርብለት የሚችል የላቀ ኃይል ባለቤት ፈራጅ ወይም ባለሥልጣን የለም። ምድራዊ ፍርድ ሰጪዎች የደኻውንና የተጨቆነውን የልቅሶ ድምፅ በማይሰሙበት ጊዜ (በመልእክቱ በተደጋጋሚ ሲከሰት እደተስተዋለው) እርዳታ የሚሻውንም ምስኪን ድምጽ የሚሰማና ምላሽ የሚሰጥ አምላክ ለመኖሩ አጽንኦት ይሰጣል።

በህይወታችን፤ በተለያዩ ጊዜያቶች የፍትሕ መጓደል ሰለባዎች ልንሆን ብንችልም፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ የፍትሕ መጓደል አድራሾቹ እኛው ራሳችን ሆነን ልንገኝ እንችላለን። እኛ ጨቋኞች ወይም ተጨቋኞች ብንሆንም--እንደ መዝ. 82 ዓይነት መልእክቶች ወደ ውስጣችን የመመልከት ዕውቀትና ጥበብ እንድናገኝ ያስችሉናል። እግዚአብሔር ልጆቹ እንደሆኑና በተሻለ መመላለሳቸውን እንደሚፈልግ የሚገልጽላቸው የኢፍትሐዊ ዳኞች ጉዳይም እንዲሁ እርሱን ያሳስበዋል (መዝ. 82፡6)። በተቃርኖ አቅጣጫ የተሰለፉ--ራሳቸውን ለመለወጥ ዝግጁ ከሆኑና ይህ እንዲሆን ከፈቀዱ ለእነርሱም ተስፋ እንዳለ መመልከት እንችላለን።

## ማክሰኞ ሐምሌ 16

## የንጉሥ የተስፋ ቃሎች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መዝ. 101። ምንም እንኳ መልእክቱ የተጻፈው በአስተዳደር ኃላፊነት ለተቀመጡ ቢሆንም--እኛ በየትኛውም የሕይወት መስክ ብንሰለፍም ከምዕራፉ ምን ዓይነት ጠቃሚ ምክረ ሀሳብ መውሰድ እንችላለን?

ከላይ እንደተጠቀሰው መዝ. 101 የተጻፈው በተለይ በአስተዳደር ኃላፊነት ለተቀመጡ ሰዎች ነው። ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በነገሠባቸው የመጀመሪያዎቹ ቀናት እነዚህን ጥቅሶች እንደ ደረሳቸው ይታመናል። እንደውም በውስጣቸው የያዟቸው ሀሳቦች ዳዊት በነገሠ ጊዜ ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ተወራራሽነት እንዳላቸው መመልከት ይቻላል። ዳዊት በመጀመሪያ የሳኦል ተዋጊ ወታደር፤ ቀጥሎ ደግሞ ከሳኦል ፊት የሚሸሽ ተቅበዝባዥ የነበረባቸው ቀናት--መንገዱን የሳተ ንጉሥ በአገሩና በቤተሰቡ ላይ እንዴት ጉዳት ማድረስ እንደሚችል ምስክር ሆነውታል። ዳዊት ከወትሮው የተለየ ንጉሥ ለመሆን ቆርጦ ተነስቶ ነበር።

ምናልባት ጥቂቶቻችን የፖለቲካ ሥልጣን ሊኖረን ቢችልም፤ በሌሎች ላይ ተጽእኖ የማድረግና የማበረታታት ኃላፊነት ያለብን ግን ሁላችንም ነን። እነዚህ ነገሮች--በህይወታችን፣ ማኅበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን፣ በቤተሰብ ወይም በቤተ ክርስቲያን ገቢራዊ መሆን ይችላሉ። "በመዝ. 101 የቀረቡት የዳዊት መሃላና ቃል ኪዳኖች በቤት ላይ ሊደርስ ለሚችል ተጽእኖ ዘብ የመቆም ኃላፊነት ያለባቸው ሁሉ መሃላና ቃል ኪዳን ሊሆን ይገባል።"—Counsels to Parents, Teachers, and Students, p. 119.

ዕድሉን ባገኘን ቁጥር እነዚህን መርኅዎች በእኛ ላይ የመሪነት ሚና ባላቸው መሪዎቻችን ላይ ለማስፋፋትና ለማስጠበቅ ዝግጁ ልንሆን ይገባል። ደግሞም እኛ ሁላችን እንደ መሪነታችንና ተጽእኖ አሳዳሪነታችን ለሌሎች በረከት መሆን እንድንችል የሚረዱንን የዳዊትን የመሪነት መርኅዎች ሥራ ላይ የማዋል ዕድሉ አለን።

የዳዊት መነሻ ነጥብ ለእርሱ የመሪነት ኃላፊነት የሁሉም ነገር መሠረት ለሆነለት ለእግዚአብሔር አምላክ ምሕረትና ፍትሕ ክብር መስጠት ነው (መዝ. 101፡1)። እነዚህኑ ልዩ ባህሪያት በህይወቱና በሥራው ለመማርና በተግባር ላይ ለማዋል ተመኝቶ ነበር። ይህን ለማድረግ በተለይ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች ወጥመድ የሚሆኑባቸውን--መጥፎ ተግባራት፣ ሙስና እና ታማኝነትን የማጉደል ፈተናዎች ተቋቁሞ ማለፍ ነበረበት።

ዳዊት ቀናውን እንዲያደርግ ሊረዱት የሚችሉ መልካም አማካሪዎች ከጎኑ እንደሚያስፈልጉት በማስተዋሉ፤ እምነት የሚጣልባቸውን አማካሪዎችና ሀቀኛ አስተዳዳሪዎችን ለመሾም ቁርጥ ሀሳቡ አደረገ። ፍትሕና ምህረት አብረውት ለሚሠሩትም ሳይቀር እንደ ግል የመሪነት መለያው መታወቅ ነበረባቸው።

***ምናልባት የየራሳችን አማካሪዎችና የበታች ሹማምንት ሊኖሩን ባይችሉም እንኳ በፍትሕና ምህረት እንድንኖርና እንድንመራ በሚያስችሉ ተጽእኖዎች መሞላት የምንችለው እንዴት ነው?***

## ረቡዕ ሐምሌ 17

# ከጌታ ጋር መራመድ

ወደ መዝሙር መጽሐፍ መደምደሚያ እየተቃረብን ስንመጣ በለሆሳስ ይደመጥ የነበረው የምስጋና ድምጽ እያደገና እየገዘፈ ማስተጋባት ሲጀምር ይስተዋላል። የመጨረሻዎቹ አምስት ምዕራፎች "ጌታን አመስግኑት!" በሚል ቀላልና ቀጥተኛ ትእዛዝ ቢጀምሩም--ምዕ. 146 ግን ለዚህ ምስጋና ተቀዳሚ ምክንያት የሆነውን ይኸውም፤ እግዚአብሔር የድኾች እና የተጨቆኑ ወገኖች ሁኔታ የሚያሳስበው አምላክ በመሆኑ ዙሪያ ልዩ ትኩረት ያደርጋሉ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መዝ. 146። በዚህ ምዕራፍ የቀረበልን መልእክት ምንድን ነው? በተለይ በመዝ. 146፡5-9 እግዚአብሔር ምን እያለ ነው?

---

---

እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ፈጣሪ እንደ መሆኑ መጠን (መዝ. 146፡6) ዳኝነቱ፣ ሰጪነቱ፣ አርነት አውጪ መሆኑ፣ ፈዋሽነቱ፣ ረዳትነቱና መከታነቱ በዚህ ዓለም ያለማቋረጥእየሠራያለውንሥራገልጠውያሳያሉ--በተለይዕርዳታዎቹለሚያሹዋቸው ወገኖች። ይህ ትዕይንት እግዚአብሔር በሕይወታችን፣ በማኅበረሰባችን ብሎም በዓለማችን የሚያደርገውንና ለማድረግ የሚመኘውን አብልጦ ያሳያል።

ለተቸገሩ እርዳታ ማድረግ ያለብን እግዚአብሔር አድርጉ ብሎ ስላዘዘን ነው ብለን አንዳንዴ እናስባለን። ነገር ግን ይህ ጉዳይ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረገው ነገር እንደመሆኑ እኛም እርሱን እንቀላቀል ዘንድ በመዝ. 146 ጥሪ ቀርቦልናል። ከድኸነት፣ ከጭቆና እና ከበሽታ በተቃራኒ ስንሠራ፤ ከእግዚአብሔርና ከእርሱ ዓላማ አኳያ መሰለፋችን እርግጥ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ፈጥሮ እንደ መዝ. 146 ያሉ መልእክቶችን ከግብ ለማድረስ ከመሥራት የላቀ ምን ዓይነት ልዩ መብትና ጥቅም አለ?

ነገር ግን ለእኛ የሚበጁ ሌሎች ጠቀሜታዎችም አሏቸው። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ለማግኘት ስላደረጉት ጥረትና ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለመመስረት ስላላቸው ምኞት በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣል። ሆኖም እግዚአብሔርን ከምናገኝባቸው መንገዶች አንዱ እርሱ ከሚሠራው ሥራ ጋር ጥምረት መፍጠር መሆኑን እንደ መዝ. 146፡7-9 ያሉ እና ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው አያሌ ጥቅሶች ያመላክቱናል። በመዝ. 146 እንደሚናገረው

እርሱ የደኸውን፣ የታመመውንና የተጨቆነውን ተስፋ ለማለምለም የሚሠራ ከሆነ እኛም አብረነው ልንሠራ ይገባል። “ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው ከፍ ያለውን የእርሱን ትኩረት ድርሻ ለተቀበሉ ድኾችና በሥቃይ ውስጥ ላሉ አብሮነቱን ለማሳየትና ለመሥራት ነው። እርሱ ዛሬም በልጆቹ ስብእና ውስጥ ሆኖ ወዮታንና ሥቃይን ያስታግስ ዘንድ ድኾችንና በእጦት የሚገኙትን ይጎበኛል።

“ሥቃይንና እጦትን ለማስወገድ ካልሠራን የአምላካዊውን ምኅረትና ፍቅር የምናስተውልበት ምንም መንገድ አይኖርም። በርኅራኄ የተሞላውንና የሌላውን ችግር የሚካፈለውን ሰማያዊ አባት አዛኝነት የምንረዳበት አንዳችም መንገድ አይኖርም። ወንጌል በብርቱ ዕጦትና ድኽነት ውስጥ ወዳሉ ማኅበረሰቦች ሲገባ የሚያገኘውን ያህል ታላቅ ፍቅር በሌላ ስፍራ አያገኝም።”—Ellen White, Testimonies for the Church, vol. 7, p. 226.

**ሌሎችን ለማገልገል እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ቀረቤታ መፍጠር እንዳለብን አስመልክቶ የእርስዎ ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

## ሐሙስ ሐምሌ 18

## መጽሐፈ ምሳሌ፣ ምኅረት በችግር ላሉ

መጽሐፈ ምሳሌ የጥበብ ቃላት ስብስብ እንደመሆኑ ስፋት ያላቸውን ልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮችና የህይወት ተሞክሮዎች ይዳስሳል። ከእነዚህ መሃል የድኽነት፣ የሐብት፣ የደስታ፣ የፍትሕ እና ኢፍትሐዊነት ነጸብራቆች ቀርበዋል--አንዳንዴም ለየት ካለ አመለካከት አኳያ። ህይወት ሁሌም ቀላልና አልጋ ባልጋ እንዳልሆነ ሁሉ፤ መጽሐፈ ምሳሌ በህይወታችን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ሁኔታዎችና ምርጫዎች ያስጠነቅቀናል። ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑትንም ያካትታል።

ጥቅሶቹን እያነበቡ ያነጻጽሩ፡ ምሳ. 10:4፤ 13:23-25፤ 14፡31፤ 15፡15፤ 14:31፤ 15:15-16፤ 19:15፤ 17፤ 30:7–9። ጥቅሶቹ ከሐብት፣ ከድኽነትና በዕጦት ያሉትን ከመርዳት ጋር በተዛዳኝ ምን ይላሉ?

---

---

እግዚአብሔር የድኾችና የጥቃት ተጋላጭ ደካሞች ጉዳይ እንደሚያሳስበው መጽሐፈ ምሳሌ አጽንኦት ይሰጣል። አንዳንዴ ሰዎች ዙሪያቸውን ባሉ ልዩ ልዩ ሁናቴዎች፣ በተሳሳተ ምርጫ ወይም በደረሰባቸው ብዝበዛ መንስኤ ሊደኸዩ ቢችሉም፤ ጌታ ግን ሁሌም ፈጣሪያቸው (ምሳ. 22፡2) እና መከታቸው ነው (ምሳ. 22፡22-23)። እነዚህ

ሰዎች የቱንም ዓይነት ስህተት ሊሠሩ ቢችሉም እንኳ የጭቆና ቀንበር ሊሸከሙ ወይም የሌሎች መጠቀሚያ ሊሆኑ አይገባም።

መጽሐፈ ምሳሌ ጥበብን በመምረጥና እግዚአብሔርን በመታዘዝ የተሻለ ህይወት ቢለግስም፤ ሐብት ሁሌም በእግዚአብሔር የመባረክ ውጤት መሆን አይችልም። ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ከሁሉም በላይ አስፈላጊና ውሎ አድሮ ከቁሳዊው የሐብት ክምችት በላቀ ተሸላሚ ማድረጉ እሙን ነው፡ "ከጽድቅ ጋር ጥቂት ነገር፣ በግፍ ከሚገኝ ብዙ ትርፍ ይሻላል" (ምሳ. 16፡8)።

ሌላው መጽሐፈ ምሳሌን የሚያሳስበው ጉዳይ በንግድ ሥራ፣ በመንግሥት ኃላፊነትና ፍትሕን በማስፈን ረገድ ሊኖር የሚገባ ሐቀኝነት ነው (ምሳ. 14:5፣ 25፣ 16:11–13፣ 17:15፣ 20:23፣ 21:28፣ 28:14–16)። መጽሐፈ ምሳሌን የሚያሳስበው የግለሰቦች ህይወት ሁኔታ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ባጠቃላይ ማኅበረሰቡ ስለ ሁሉም ጥቅም ሲባል እንዴት መሥራት እንዳለበት ብርሃን ይፈነጥቃል--በተለይ ከለላ ለሚያሻቸው ምስኪኖች። ሹማምንትና ገዢዎች በእግዚአብሔር እርዳታ ተግባራቸውን እንደሚያከናውኑ ድጋሚ ማስታወሻ (ምሳ. 8፡15-16) የተሰጠን ሲሆን፤ ለተቸገሩ ሁሉ የጸጋውና የርኅራኄው ወኪሎች ሆነው ይሠሩ ዘንድ ተጠርተዋል።

**በአጉል ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ሰዎች የሐዘኔታ ስሜት ማሳየት ቀላል ሊሆን ቢችልም፤ ይህን የሐዘኔታ ስሜት ወደ ድርጊት መለወጥ የምንችለው እንዴት ነው?**

## አርብ ሐምሌ 19

ተጨማሪ ሀሳብ: *Read Ellen G. White, "The Last Years of David," pp. 746–755, in Patriarchs and Prophets; C. S. Lewis, "'Judgment' in the Psalms," pp. 15–22, in Reflections on the Psalms.*

"የዳዊት መዝሙር ሰዎች እያወቁ ከሚፈጽሙት ጥልቅ በደል አንስቶ እራስን እስከ መውቀስና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እስከሚያስችል ግዙፍ እምነት ድረስ ያለውን አጠቃላይ የሕይወት ተሞክሮ ይዳስሳል። ኃጢአት ሐፍረትና መከራ ብቻ እንደሚያመጣ የዳዊት ሕይወት ታሪክ ይነግረናል። እጅግ ጥልቅ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት ግን የተጸጸተችውን ነፍስ ቀና በማድረግ የእግዚአብሔር ልጅነትን ማእረግ ያጎናጽፋታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከቀረቡት ጠንካራ አምላካዊ ማረጋገጫዎች አንዱ የሆነው ይህ ክፍል በታማኝነት፣ በፍትሕና በአምላካዊው ምህረት ኪዳን ዙሪያ ምስክርነቶችን ይዞአል።" የኃይማኖት አባቶችና

ነቢያት፡ ቅጽ 2 ገጽ 436።

በመጽሐፈ ምሳሌ የምናገኛቸው “መርኅዎች በመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ አስተዳደራዊ ሥርዓት የማኅበረሰቡን ደኅንነት የሚያስጠብቁ ናቸው። የማኅበረሰቡን ሐብት የማፍራትም ሆነ በሕይወት የመኖር ደህንነት የተጠበቀ የሚያደርጉት እነዚሁ መርኅዎች ናቸው። መርኅዎቹ በሁሉም ዘንድ መተማመን እንዲፈጠርና ትብብር እንዲኖር የሚያስችሉ ሲሆን፤ ዓለም ጌታ በቃሉ የሰጠውና በሰብዓዊው ልብ ሙሉ ለሙሉ ወደ መሰወር ያዘነበለው የዚህ አምላካዊ ሕግ ባለ ዕዳ ነው።”—Ellen G. White, Education, p. 137.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ራስዎን እንደ መሪ ወይም እንደ ተጽእኖ አሳዳሪ የሚያዩበት መንገድ ምን ይመስላል? በዚያ የሕይወትዎ ገጽታ የፍትሕ ወኪል መሆን የሚችሉት እንዴ ነው?**

**2.ስለሚኖሩበት ማኅበረሰብ ባህልና ማኅበረሰባዊ አወቃቀር አሰብ ያድርጉ። በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን ዕጣ ፈንታ የተሻለ ለማድረግ አሁን ያለውን መዋቅር ተጠቅመው እንዴት መሥራት ይችላሉ?**

**3.የፍትሕና የቅንነት መርኅዎች ጠንካራ ማኅበረሰብ ለመገንባት በጣም አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው?**

**4.መጽሐፈ ምሳሌ ሕይወታችንን በአግባቡ በምንመራበት ጥበብ ዙሪያ ትኩረት ከማድረጉ አኳያ እግዚአብሔር ምን ዓይነት አምላክ ስለመሆኑ ምን ይለናል?**

***ማጠቃለያ፡*** *መዝሙረ ዳዊትና መጽሐፈ ምሳሌ በተለይ በህይወት ዙሪያ ሊገጥሙ በሚችሉ የጋራ ተሞክሮዎችና ፈተናዎች መሃል በታማኝነት ስለ መኖር ይናገራሉ። ሁለቱም መጻሕፍት እግዚአብሔር ለማኅበረሰቡ ያለውን ራእይ ከማጋራታቸው ባሻገር፤ በተለይ የድኾችና በጭቆና ቀንበር ሥር ያሉ ምስኪኖች ሁኔታ በእጅጉ እንደሚያሳስበው ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። የመዝሙረ ዳዊት የልቅሶ ድምፆች እና የመጽሐፈ ምሳሌ የጥበብ ቃላት--በተደጋጋሚ ችላ የተባሉትን ወይም ብዝበዛ የደረሰባቸውን ምንዱባን ሁኔታ እግዚአብሔር እንደሚመለከትና መከታቸው ለመሆን ጣልቃ እንደሚገባ ያሳያሉ። እግዚአብሔር እንደዚያ ዓይነት አምላክ ከሆነ እኛም አርአያነቱን መከተላችን የግድ ይሆናል።*

# 5ኛ ትምህርት

**ከሐምሌ 20-26**

# የነቢያት ልቅሶ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 1ሳሙ. 8፡10–18፣ አሞጽ 5፡10–15፣ ሚክ. 6፡8፣ ዘፍ. 19፡1–13፣ ሕዝ. 16፡49፣ ኢሳ. 1፡15–23።

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-** **"ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን? (ሚክ. 6፡8)።**

ከመጽሐፍ ቅዱስ መሳጭ ገጸ ባህሪያት መካከል የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይጠቀሳሉ። ነቢያቱ ሁሌም በህዝቡ መሃል መሆናቸው ምቾት ባይሰጣቸውም እንኳ፤ ጎርናና ድምፃቸው፣ በድፍረት የተሞሉ መልእክቶቻቸው፣ ሐዘናቸው፣ ንዴታቸውና ቁጣቸው--በጣም አልፎ አልፎ የሚሰጧቸው መልእክቶች አፈጻጸም ችላ ሊባሉ የማይችሉ ሰዎች አድርጓቸው ነበር።

በቅድሚያ ወደ እስራኤልና ይሁዳ የተላኩት ነቢያት የተመረጡት ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ጥሪ እያቀረቡ ነበር። ሕዝቡና መሪዎቹ በአጎራባች አገሮች ጣኦት እና አጓጉል የአኗኗር ስልት በቀላሉ ተነድተው ይወሰዱ ነበር። አንዳንዴ የእግዚአብሔርን ፍቅር እያስታወሷቸው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ ሕዝቡ ያደረጋቸውን አስደናቂ ተግባራት እየጠቀሱ፣ መረር ሲል--ሊከተሏቸው የሚችሉትን ውጤቶች በማሳየትና በማስጠንቀቅ ወደ ንስሐ እንዲመጡ ማድረግ የውለታ ቢሶቹ ነቢያት ፈታኝ ኃላፊነት ነበር።

ነቢያት በኃጢአትና ክፉ ተግባራት ዙሪያ ለመሪዎችና ለሕዝቡ ከሚሰጧቸው ማስጠንቀቂያዎች ጎን ለጎን የድኾች ጭቆና እና አይዟችሁ ባይ ረዳት የሌላቸው ምስኪኖች ጉዳይ ከፍ ያለ አጽንኦት የሚሰጣቸው ነበሩ። ጣኦት ማምለክ ስህተተት ነው? አዎ! ሐሰተኛ ኃይማኖታዊ ልማዶችን መከተልስ? አዎ ስህተት ነው! በደካሞችና በድኾች ላብ ያላግባብ መበልጸግ ለኩነኔ ይዳርግ ይሆን? አዎ!

**እሑድ** **ሐምሌ 21**

# ስለ ፍትሕ ያለማሰለስ የሚቀርብ ጥሪ

የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር በግልጽ ዘርዝሮ ካስቀመጣቸው ዕቅዶች አኳያ ማለትም እንደ መጠራታቸው አልተመላለሱም። እግዚአብሔር በሰጣቸው የተስፋ ምድር ተቋቁመው ገና ብዙ ዘመን እንኳ ሳይኖሩ "'ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት ሁሉ'" (1ሳሙ. 8፡5) የሚመራቸው ንጉሥ ያነግሥላቸው ዘንድ ነቢይ እና ፈራጅ የነበረውን ሳሙኤል ጠየቁት።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ሳሙ. 8፡10-18። ሕዝቡ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ለሳሙኤል ላቀረበው ጥያቄ የሳሙኤል ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

---

---

ሳሙኤል ይህን ድርጊት ሌሎች ሕዝቦችን ለመምሰል ከሚደረግ እንቅስቃሴ አኳያ ተመልክቶት ነበር። ሳሙኤል የመጀመሪያውን ንጉሥ ይኸውም ሳኦልን ለማማከር ተመኝቶ የነበረ ቢሆንም፤ ይህ ትንቢቱ ሰምሮ ወደ ተግባር እስኪለወጥ ምንም ያህል ጊዜ አልወሰደም። የእስራኤል መንግሥት በአስገራሚ ከፍታ ላይ በነበረባቸው የዳዊትና የሰሎሞን ንግሥና ዘመናትም እንኳ ከንቅዘትና ሥልጣንን ያላግባብ ከመጠቀም ፈተና አላመለጡም ነበር።

በመላው የእስራኤልና ይሁዳ ግዛት ነገሥታት ዘመን እግዚአብሔር አምላካዊውን ፈቃድ የሚናገሩ ነቢያትን እየላከ የእስራኤል መሪዎችና ሕዝቡ ስለ ተረሱትና ስለ ተዘነጉት የማኅበረሰብ አባላት የሰጣቸውን ኃላፊነቶች ያስታውሳቸው ነበር።

እስራኤላውያን በጽድቅ እንዲመላለሱና በሕብረተሰቡ መሃል ፍትሕ እንዲያደርጉ የሚማጸን ያላሰለሰ ጥሪ በዕብራውያን ነቢያት መልእክቶች ውስጥ እናገኛለን። የእስራኤልንና የመሪዎቿን አመጽ ፊት ለፊት ይጋፈጡ የነበሩት ነቢያት ድምጻቸው ለማይሰማ ምስኪኖች ሁሌም ድምጽ ነበሩ--በተለይ እስራኤላውያን አምላካዊውን ፈቃድ ከመታዘዝ ሲያፈነግጡ በቀላሉ ለጉዳት ለሚጋለጡት።

እንደነ አብርሃምና ኢያሱ ያሉት ጥልቅ ስሜት የተንጸባረቀባቸው የብሉይ ኪዳን

ነቢያት--ፍትሕ በአፋጣኝ እንዲሰፍን ያቀረቡት ጥሪ ከእኛ ዘመን ዳተኝነት በእጅጉ ይቃረናል፡ “በወቅቱ ነቢያቱን አሳቅቀው የነበሩ ጉዳዮች ዛሬ የዓለማችን የዕለት ከዕለት ክስተቶች ናቸው. . . ትንፋሻቸውን ቀጥ ያደረገውና ትዕግሥታቸውን ያሟጠጠው ኢፍትሐዊነት እኛን ብርክ ባስያዘ ነበር። ያለማቋረጥ ገቢራዊ እየሆኑ ላሉ የኢፍትሐዊነት መገለጫዎች ማለትም--ግብዝነት፣ ዋሾነት፣ ጭካኔ የተሞላባቸው ተግባራት፣ ሥቃይና መከራ፣ አልፎ አልፎ ከመበሳጨት ውጪ ደስተኞች ለመሆናችን እኛ ራሳችን ምስክሮች ነን። ኢምንት የተባለው ኢፍትሐዊነት እንኳ ሳይቅር በነቢያቱ ዘንድ ግዙፍ ትኩረት ይቸረው ነበር።”—The Prophets (New York: Jewish Publication Society of America, 1962), pp. 3, 4.

እነዚህ ነቢያት የእግዚአብሔርን ልብ እና አእምሮ ገልጠው ያሳዩናል። እግዚአብሔርን በመወከል እየተናገሩ ዕንባ ባቀረሩ አምላካዊ ዓይኖች የዓለማችንን ኢፍትሐዊነትና ሥቃይ መመልከት እንድንችል ይረዱናል። ደግሞም ይህ ጥልቅ ስሜት--ወደ ተግባር ገብተን ከጌታ ጋር እየሠራን በጭቆና እና በሐዘን ተቆራምደው በዙሪያችን ለሚገኙ ምስኪኖች እፎይታ እንድናስገኝና መፍትሔ እንድንሆን የቀረበልን ጥሪ ነው።

***አንዳንዴ በእኛም ሆነ በሌሎች ላይ ጉዳት በሚያስከትሉ ማለትም “‘ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት’” ለመሆን የመመኘታችን ነገር ምን ይመስላል?***

## ሰኞ ሐምሌ 22

# አሞጽ

“አሞጽም ለአሜስያስ እንዲህ ሲል መለሰ፤ ‘እኔ እረኛና የባሉጥ ፍሬ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤’ እግዚአብሔር ግን የበግ መንጋ ከምጠብቅበት ቦታ ወስዶ፣ “ሂድና ለሕዝቤ ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ” ’ ” (አሞጽ 7፡14-15)

አሞጽ የእግዚአብሔር ነቢይ ለመሆን ጉድለቶች እንዳሉት ከመናገር ወደ ኋላ ያላለ ግልጽ ሰው ነበር። ሆኖም መልእክቱን ለእስራኤላውያን ሲያቀርብ አድማጮቹን ለመሳብ የሚያስችል በግልጽ የሚታይ ችሎታ እንዳለው ማስመስከር ችሎ ነበር።

አሞጽ ለእስራኤል አጎራባች የነበሩት--ሶርያ፣ ፍልስጥኤም፣ ፊንቄ፣ ኤዶም፣ አሞንና ሞዓብ አንድ በአንድ በሚጠቅስበትና ስለ ወንጀላቸው፣ ጭካኔ የተሞላ

ድርጊታቸውና ግፋቸው እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው በሚያወሳበት ዝናን ያተረፈ መልእክቱ ጽሑፉን ይጀምራል (አሞጽ 1፡3-2፡3)። እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ላይ በቀረበው የክስ ማስረጃ ማጨብጨባቸውን ለመገመት ብዙም አይከብድም--በተለይ አብዛኞቹ ወንጀሎች በቀጥታ ያነጣጥሩ የነበረው በራሳቸው በእስራኤላውያን ላይ ከመሆኑ አኳያ።

በመቀጠል አሞጽ ቀስ በቀስ ፊቱን ወደ አገር ውስጥ ጉዳይ ይመልስና የእስራኤል ደቡባዊ አጎራባች በሆነውና ከእስራኤል ተነጥሎ በነበረው በይሁዳ ግዛት ላይ አምላካዊው ፍርድ እንደሚሰጥ ያውጃል። እግዚአብሔርን በመወከል የሚናገረው አሞጽ ይህን አምላክ መቃወማቸውን በመጥቀስ፤ ትእዛዛቱን ለመጠበቅ አሻፈረኝ ማለታቸውንና ያንን ተከትሎ ስለሚመጡት ቅጣቶች ያወሳል (አሞጽ 2፡4-5)። አሞጽ በዙሪያቸው የነበሩ ሕዝቦች ያደርጉ የነበረውን ስህተት መጠቆሙን ተከትሎ የሰሜናዊ ግዛት ሕዝቦች አሁንም ደስ መሰኘታቸውን መገመት እንችላለን። የተቀረው የመጽሐፉ ክፍል በእስራኤል ይተገበሩ በነበሩ ክፉ ተግባራት፣ ጣኦት አምልኮ፣ ኢፍትሐዊነትና ተደጋጋሚ ውድቀቶች ዙሪያ ትኩረት ያደርጋል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ አሞጽ 3:9–11፤ 4:1-2፤ 5:10–15፤ 8:4–6። ስለ የትኛው ኃጢአት ነው ማስጠንቀቂያ የተሰጠው?

---

---

አሞጽ በመልእክቱ የተጠቀማቸው ቃላት ዲፕሎማሲያዊ አለመሆንና የማስጠንቀቂያዎቹ ክብደት--አምላካዊውን ጥሪ እጅግ ጽኑ ያደርጉታል። ይህ ደግሞ ወደ ልቦና መመለስና በመካከላቸው ላሉ ድኾች ጥንቃቄ ማድረግን ያካትታል፡ “ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣ ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍሰስ” (አሞጽ 5፡24)። የትንቢተ አሞጽ የመጨረሻዎቹ ጥቂት ቁጥሮች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደፊት ወደሚያገኙት ደኅንነት ያመላክታሉ (አሞጽ 9፡11-15)። “ሕዝቡ ጥልቅ በሆነ ክህደትና ታላቅ እጦት ላይ በነበረበት ሰዓት--እግዚአብሔር አምላክ የይቅርታና የተስፋ መልእክት ሰጣቸው።”—Ellen G. White, Prophets and Kings, p. 283.

**የተሳሳተውን ለማረም ጥብቅ ቃላት ለመጠቀም የተዘጋጀንባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆን? እነዚህ ቋንቋዎች ተገቢ የሚሆኑባቸውን ጊዜያቶች ለይተን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው?**

# ማክሰኞ ሐምሌ 23

## ሚክያስ

“ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን? (ሚክ.6፡8)።

ይህ ጥቅስ ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ አብልጠው ከሚታወቁ ጥቅሶች መሃል አንዱ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሆኖም ሌሎች ጥቅሶችን አዘውትረን እንደ ማስታወቂያ ወይም ፖስተር የምንጠቀመውን ያህል ይህንንም በተመሳሳይ ጥቅም ላይ አለማዋላችን ምናልባት ከጥቅሱ ዐውድ ጋር ያለን ቁርኝት እናስተውለዋለን ብለን ከምንገምተው በታች ሊሆን ይችላል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሚክ. 2:8–11፣ 3:8–12። ሕዝቡ ያደርግ የነበረውና ሚክያስ ያወገዘው ነገር ምን ነበር?

የእግዚአብሔር ሕዝቦች በታሪካቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ወደ አዲስ ዝቅታ ሲወርዱ የታየበት ክስተት ቢኖር የአካዝ በይሁዳ መንገሥ ነበር። የጣኦት አምልኮና ያንን ተከትለው የመጡ ልዩ ልዩ የእርክስና ተግባራት እየተስፋፉ መሄድ ጀመሩ። በተመሳሳይ በወቅቱ የነበሩ ሌሎች ነቢያት ጭምር እንደ ተገነዘቡት ከሆነ ድኾች አስከፊ የጭቆና ቀንበር መሸከማቸውና የሌሎች መጠቀሚያ መሆናቸው ቀጥሎ ነበር።

ሚኪያስ በዘመኑ ከነበሩ የአምላካዊውን ቁጣ ነጋሪ ነቢያት ያነሰ መልእክተኛ አልነበረም። ከመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች መካከል አብዛኞቹ--ሕዝቡ የፈጸመውን የእርክስና ተግባርና ይህን ተከትሎ የመጣውን አምላካዊ ቁጣ እና ሐዘን እንዲሁም በመንገዳቸው እየመጣ የነበረውን ጥፋት የሚገልጹ ናቸው።

ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ግን በሕዝቡ ተስፋ አልቆረጠም ነበር። የነቢያቱ ጎርናና

ድምጾችና ጥብቅ መልእክቶች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ፍላጎት ያልተገታ ለመሆኑ ማሳያ ናቸው። ስለዚህ ጌታ ለእነርሱ ካለው ፍቅርና ጥንቃቄ የተነሳ ማስጠንቀቂያዎቹን ሰጣቸው። እግዚአብሔር ይቅር ሊላቸውና ወደ ቀደመው ንጽህና ሊመልሳቸው ናፈቀ። እነሆ እርሱ ከዚህ በኋላ ለዘላም አይቆጣም (ሚክ. 7፡18-20)።

ይህ በብዙዎች የሚታወቀው--በጽድቅ የመመላለስ፣ ምኅረትን የመውደድ፣ በትህትና የመራመድ "ቀመር" ዐውድ ነው። ላይ ላዩን ሲያዩት ቀላል ሊመስል ቢችልም፤ ነገር ግን በተጨባጭ እንዲህ ያለውን የእምነት ህይወት መኖር ብርቱ ተግዳሮት የበዛበት ነው--በተለይ ይህን ማድረግ ከማኅበረሰቡ የሚያገልል ሆኖ ሲሰማ። ሌሎች በምኅረት እየተሳለቁና በትዕቢት እየተራመዱ ከኢፍትሐዊነት አትራፊ በሚመስሉበት ድባብ በጽድቅ መመላለስ፣ ምኅረትን መውደድና በትህትና መራመድ ወኔ እና ጽናት ይጠይቃል። አንድ በእርግጠኝነት መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር ይህን መንገድ ስንመርጥ ብቻችንን አንጓዝም። አምላካችን እግዚአብሔር አብሮን አለ።

***በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ በመመላለስ፣ ምኅረትን በመውደድና በትህትና በመራመድ መሀል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?***

**ረቡዕ** **ሐምሌ 24**

# ሕዝቅኤል

ስለ "ሰዶም ኃጢአት" ምንነት ለተወሰኑ ክርስቲያኖች ጥያቄ ብናቀርብ ከጥፋቱ አስቀድሞ የተፈጸሙትን ልዩ ልዩ የዝሙት እና የርኩሰት ተግባራት ጠቅሰው የሚያስረዱ ብዙዎች ናቸው። ለነገሩ ዘፍ. 19፡1-13 ከሚሰጠን ሥዕላዊ ዘገባ አኳያ ማኅበረሰቡ ይገኝበት የነበረው የርኩሰት ደረጃ አፋጣኝ ውሳኔ የሚሻ እንጂ እሹሩሩ የሚባልበት አልነበረም።

የሚገርመው ነገር መልሱ ከታሰበው ይልቅ በጣም ውስብስብ ነው። " ' "እነሆ የእኅትሽ የሰዶም ኀጢአት ይህ ነበር፤ እርሷና ሴት ልጆቿ እብሪተኞች፣ ጥጋበኞችና ደንታ ቢሶች ነበሩ፤ ድኾችንና ችግረኞችንም አይረዱም ነበር" ' " (ሕዝ. 16፡49)። ጌታ በከተማዋ ውስጥ ይስተዋል የነበረውን ሌላውን ዓይነት የዐመጻ ተግባር ችላ አለማለቱ በግልጽ የሚታይ ነበር። እዚህ ላይ የሕዝቅኤል ትኩረት በኤኮኖሚ ኢፍትሐዊነትና በድኽነት የሚማቅቁ ምስኪኖች ዙሪያ ማነጣጠሩን ልብ ይሏል።

በእግዚአብሔር ዐይን፤ እነዚህ ከኤኮኖሚ ጋር ቁርኝት ያላቸው ኃጢአቶች እንደ ዝሙቶቹ ሁሉ የከፉ ነበሩ?

ሕዝቅኤል ከአሞጽ፣ ከሚክያስና ከኢሳይያስ ዘመን በኋላ የመጣ ነቢይ እንደመሆኑ የእርሱ የቀደሙ ትንቢቶች እየመጣ ስለነበረው ጥፋት የሚሰጡት ማስጠንቀቂያ ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ሆኖም የሩሳሌም በባቢሎናውያን እጅ ከወደቀችና ሕዝቦቿ በግዞት ከተወሰዱ በኋላ የሕዝቅኤል ትኩረት እግዚአብሔር እነርሱን ነፃ ሕዝብ አድርጎ መልሶ በሚያቋቁምበት ተስፋ ዙሪያ ያነጣጠረ ሆነ።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሕዝ. 34፡2-4፣ 7-16። እግዚአብሔር ብልሹ ሁኔታ ውስጥ የነበሩትን የእስራኤል መሪዎች ከመንጋው አኳያ የገመገመበትን መንገድ ያስተያዩ። “ደካማ” የሆነውን በግ ያስተናገዱበት መንገድ ከእርሱ ዘዴ ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

---

---

---

ከሰዶም ጋር ተነጻጽረው መቅረባቸው ምን ያህል የከፋ ሁናቴ ላይ ይገኙ እንደነበር ቢያመላክትም፤ ጌታ ግን ከእርክስና መንገዳቸው ይመለሳሉ ብሎ ተስፋ በማድረግ እነርሱን ከመቅረብ አልተገታም ነበር። እግዚአብሔር የሩሳሌምን ወደ ቀድሞው ሁኔታዋ ለመመለስና ቤተ መቅደሱንም እንደገና ለመገንባት የሚያስችል ዕቅድ ዳግመኛ አውጥቶ ነበር። በእግዚአብሔር የተሰጧቸው ክብረ በዓላት ዳግመኛ መከበር ይጀምራሉ፤ ምድሪቱም እንደየ ትውልዳቸው ለሁሉም እኩል፣ እኩል ትከፋፈላለች (ሕዝ. 47፡13-48፡29)። ቀደም ሲል እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነፃ ሲወጡ በመጀመሪያ ለሙሴና ለእስራኤል ሕዝብ ግልጽ የተደረገው ዕቅድ አሁንም ሕዝቡ ከግዞት ሲመለስ ይተገበር ዘንድ አምላካዊው ፍላጎት መሆኑ ግልጽ ይመስላል። ይህ ደግሞ ለደካማው የሕብረተሰብ ክፍል እና ለመጻተኛው መቆርቆርን ያካትታል።

**እግዚአብሔር የተሻለ ምርጫ ማድረግ እየቻሉ በተሳሳተ መንገድ ለሄዱ ሕዝቦች ሳይቀር ሁለተኛ ዕድል የሚሰጥ አምላክ መሆኑ ለእርስዎ ምን ትርጉም አለው?**

## ሐሙስ ሐምሌ 25

# ኢሳይያስ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 1:15–23፤ 3:13–15፤ 5:7-8። ነቢዩ ዙሪያውን ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ ለተመለከተው ነገር የሰጠውን ምላሽ እንዴት ይገልጹታል?

---

---

የኢሳይያስ መልእክት መክፈቻ የሆኑት የመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕራፎች መረር ያለ ሒስ ቀላቅለው ይዘዋል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች አምላካቸውን ፈቃድ እንደተቃወሙና የከፋት ድርጊታቸውን የሙጥኝ ብለው እንደያዙ፤ መሆን የማይገባቸው ዓይነት ሕዝቦች መሆናቸውን ከገፉበት አይቀሬው ፍርድ እንደሚከተል--ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው በህይወታቸውና በማኅበረሰባቸው ላይ ተሐድሶ ካመጡ ግን ተስፋ ተሰጥቶአቸው ነበር። ምናልባት ጥልቅ የሐዘን ስሜት የሚፈጥሩ ቃላት በኢሳይያስ መልእክቶች ይደመጡ ይሆናል። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ምን ዓይነት አምላክ እንደሆነና ለሕዝቡ የሚሻው ምን እንደሆነ ካለው አረዳድ አኳያ--ስለ ጠፋው ነገር፣ በጉዳት ላይ ላሉና ለተረሱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች፣ እንዲሁም በአገሪቱ ላይ ሊመጣ ስላለው ፍርድ እያሰበ በከፍተኛ ሐዘን ውስጥ ነበረ።

ትንቢታዊ አገልግሎቱን በዚሁ መንገድ የገፋው ኢሳይያስ፤ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ነገር መለስ ብለው ያስታውሱ ዘንድ ሕዝቡን አጥብቆ ያበረታታል። በተጨማሪ እግዚአብሔር ወደ ፊት ሊያደርግላቸው ስላቀደው ነገር ተስፋ ይሰጣቸዋል። ስለዚህ ጌታን አሁኑኑ አጥብቀው መሻታቸው ወሳኝ ነበር። ይህ ከእርሱ ጋር የሚመሰርቱት የታደሰ ግንኙነት እየፈጸሙ የነበረውን የተሳሳተ ድርጊት ጨምሮ በሌሎች ላይ የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት እንዲለውጡ ጭምር የሚያደፋፍር ነበር።

ኢሳይያስ በምዕ. 58 እና 59 መልእክቱ ፊቱን በተለይ ወደ ፍትሕ ጉዳይ ይመልሳል። “ስለዚህ ፍትሕ ከእኛ ርቆአል፤ ጽድቅም በሩቁ ቆሞአል፤ እውነት በመንገድ ላይ ተሰናክሎአል፤ ቅንነትም መግባት አልቻለም” (ኢሳ. 59፡14)። እግዚአብሔር በጉዳዩ ዙሪያ ግንዛቤ እንዳለው አጽንኦት የሚሰጠው ኢሳይያስ፤ ሕዝቡን ሊታደግ “አዳኝ... ይመጣል” (ኢሳ. 59፡20) ሲል ይናገራል።

የመሲህን መምጣት ማወጅ--በመላው ትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ አበይት ትኩረት የተቸረው ክፍል ነው። እርሱ ፍትሕ የማስፈን፣ ምሕረት የማድረግ፣ የፈውስ እና ወደ ቀድሞ ንጽህና የመመለስ ተግባራትን በማከናወን አምላካዊውን የበላይነት ዳግመኛ ያረጋግጣል።

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 9:6-7፣ 11:1–5፣ 42:1–7፣ 53:4–6። እነዚህ ትንቢቶች ስለ የሱስ ህይወት፣ አገልግሎትና ሞት ካሎት አረዳድ ጋር እንዴት ይዛመዳሉ? ትንቢቶቹ ወደዚህ ዓለም ስለ መምጣቱ ዓላማ ምን ይጠቁማሉ?**

## አርብ ጥር 24

**ተጨማሪ ሀሳብ**: *Read Ellen G. White, "The Assyrian Captivity," pp. 279–292; "The Call of Isaiah," pp. 303–310, in Prophets and Kings.*

"በግልጽ የተመለከተውን ጭቆና፣ በከፋ ሁኔታ ላይ የነበረውን ኢፍትሐዊነት፣ ያልተለመደውን ቅንጦትና ብኩንነት በማውገዝ ከቀረበው መልእክት ባሻገር--ነቢያት በዘመናቸው ስለተስተዋለው ሐፍረተ-ቢስ ጾምና ሰካራምነት፣ አጸያፊ ዘማዊነትና ሴሰኝነት ድምጾቻቸውን ከፍ አድርገው ቢጮኹም፣ ተቃውሞአቸውም ሆነ ኃጢአትን ማውገዛቸው እንዲያው በከንቱ ነበር።"—Ellen G. White, Prophets and Kings, p. 282.

"በወቅቱ ሕዝቡ ይገኝበት የነበረው ማኅበራዊ ሁኔታ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ እንደ ነበር ኢሳይያስ ተመልክቶአል። ሰዎች የግል ሐብት ለማካበት ከነበራቸው ጥልቅ ምኞት የተነሳ በቤት ላይ ቤት፣ በመሬት ላይ መሬት ለመደራረብ ቀን ከሌት እንቅልፍ አልነበራቸውም. . . ፍትሕ ተጣመመ፣ ለድኾች ማዘንና ርኅራኄ ማድረግ አከተመ. . . ሌላው ቀርቶ ለረዳት ዐልባው ዘብ የመቆምና አለኝታ የመሆን ኃላፊነት የነበራቸው ገዢዎች ሳይቀሩ በድኾች፣ በመበለቶችና አባት በሌላቸው ህፃናት ላይ ለደረሰው ቀውስ ጆሮ ዳባ ልበስ አሉ. . .

"በዖዝያን ንግሥና የመጨረሻዎቹ ዓመታት ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን የማስጠንቀቂያና ግሳጼ መልእክቶች ይዞ ወደ ይሁዳ እንዲሄድ ጥሪ ቀርቦለት የነበረ ቢሆንም እርሱ ግን ኃላፊነቱን ሳይወጣ ቀረ።"—Pages 306, 307.

“እነዚህ በነቢያት የቀረቡ ግልጽ ተማጽኖዎች. . . እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ነፍስ የሚያቀርበው የጥሪ ድምፅ ሆነው በእኛም ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል። የቀደመውን ቅን የክርስትና አካሄድ እየተጠቀምን፤ ሸክም ለበዛባቸውና ለተጨቆኑ ምኅረት ለማድረግ የሚያስችለንን ማንኛውንም መልካም አጋጣሚ በከንቱ ማሳለፍ የለብንም።”—Page 327.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.የትንቢት ተግባር የወደፊቱን መተንበይ እንደሆነ አብልጠን እናስተውላለን። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ለኖሩበት ዓለም የሰጡት ትኩረት--በነቢያቱ ሚና ዙሪያ ያሎትን ግንዛቤ የሚለውጠው እንዴት ነው?**

**2.ለእውነት መቆም ምን የህል አስቸጋሪና አደገኛ ሊሆን እንደሚችል የነቢያቱ ህይወትና መልእክት በጉልህ ያሳያል። ነቢያቱ የተናገሯቸውም ሆኑ ያደረጓቸው ነገሮች እነዚያው የተገለጹት መሆናቸውን ለምን ያምናሉ?**

**3.እግዚአብሔር አንዴ ሲቆጣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ለሕዝቡ ሲጨነቅ የሚያሳዩ ተፈራራቂ ጽሑፎች በነቢያቱ ቀርበዋል። እነዚህን ሁለት ገጽታ ያላቸውን አምላካዊ ጸባዮች እንዴት በአንድ ማቅረብ ይችላሉ?**

*ማጠቃለያ፡ በተደጋጋሚ ሲቆጡና ሲበሳጩ የሚታዩት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ጠበቆችና ቀናኢ ተቆርቋሪዎች ነበሩ። ይህ ለድኾችና ለተጨቆኑ ፍትሐዊ ትኩረት እንዲቸር የሚጠይቅ ጥልቅ ስሜት የራሱን የእግዚአብሔር ሥጋት የሚያንጸባርቅ ነበር። ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ዘንድ በነቢዩ የቀረበው ጥሪ ኢፍትሐዊነት እንዲያከትም የሚጠይቅም ነበር። ይህ ደግሞ ስለ ሕዝቡ የተሻለ የወደፊት ሕይወት ሲል እግዚአብሔር እንደሚተገብረው በራእይ ቃል የገባው ነገር ነበር።*

# ፮ኛ ትምህርት

**ሐምሌ 27 - ነሐሴ 3**

# ፈጣሪን ማምለክ

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ መዝ. 115:1–8፤ ዘዳ. 10:17–22፤ መዝ. 101:1፤ ኢሳ. 1:10–17፤ ኢሳ. 58፤ ማር. 12:38–40።*

**<u>የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-</u> “ ‘እንግዲህ እኔ የመረጥሁት ጾም፣ የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ አይደለምን? ምግብህን ለተራበ እንድታካፍለው፣ ተንከራታቹን ደኻ ወደ ቤትህ እንድታስገባው፣ የተራቆተውን ስታይ እንድታለብሰው፣ የሥጋ ዘመድህንም ፊት እንዳትነሳው አይደለምን? (ኢሳ. 58፥6-7)።**

የብሉይ ኪዳን ነቢያትን መልእክት ላይ ላዩን ገረፍ አርገነው ብናልፍ እንኳ፤ ስለ ደኻውና ስለ ተጨቆነው ሰብዓዊ ወገን በደል የጻፏቸው መልእክቶች ጉዳዩን አሳሳቢ አድርገን እንድንወስድ ያስገድዱናል። ነቢያትም ሆኑ መልእክቱን የሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር ዙሪያ ገባውን ባሉ ሕዝቦች ዘንድ እየሆነ በነበረው ነገር (አሞጽ ምዕ. 1 እና 2) ክፉኛ ተቆጥቶ ነበር--በተለይ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መለኮታዊ በረከቶች ተቀባይ በነበሩት በራሳቸው በእግዚአብሔር ሕዝቦች ይፈጸሙ በነበሩ የርኩሰት ተግባራት። የአስደናቂ አርነት ታሪክና የእግዚአብሔር ሕግ ባለቤት የነበሩት እነዚህ ሕዝቦች በተሻሉ ነገሮች ሊታወቁ ሲገባ፤ የሚያሳዝነው ባብዛኛው ይህ ሳይሆን ቀርቶአል። እነዚህን አሳዛኝ ክስተቶች ተከትሎም ነቢያት እጅግ ብዙ ብለዋል።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ ፍትሕ እና ኢፍትሐዊነት ከሰጧቸው ዝነኛ መልእክቶች ውስጥ አብዛኞቹ የተበረከቱት ስለ አምልኮ ከተሰጡ መመሪያዎች ዕውድ መሆኑን መገንዘብ ደስ ያሰኛል። እውነተኛ አምልኮ እንደው በአንድ ኃይማኖታዊ ሥነስርአት ላይ ገቢራዊ የሚሆን ነገር ብቻ አይደለም። ይልቁንም እውነተኛ አምልኮ እግዚአብሔር ስለ ሌሎች ምቾትና ደስታ ያለውን ጭንቀትና ሥጋት የመጋራት ብሎም የተጨቆኑትና የተረሱት አንገቶቻቸውን ቀና እንዲያደርጉ የሚታትር ህይወት መኖር ነው።

## እሑድ ሐምሌ 28

# ጣኦት አምልኮ እና ጭቆና

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ከግብጽ ካወጣቸው በኋላ ብዙም ሳይቆይ በሲና ተራራ ላይ ተገናኛቸው። ከዚያም የመጀመሪያዎቹን ሁለት ትእዛዛት ማለትም ሌሎች አማልክት አይኑሩህ እና ለራስህ ጣኦት አታብጅ የሚሉትን ጨምሮ በድንጋይ ጽላት ላይ የተቀረጹትን ዐሥርቱን ትእዛዛት ሰጣቸው (ዘፀ. 20፡2-6)። በምላሹም ሕዝቡ ማንኛውንም የታዘዙትን ነገር ለመፈጸምና እንደ እርሱ ሕዝቦች ሆነው ለመኖር ቃል ኪዳን ገቡ (ዘፀ. 24፡1-13)።

በመሃል ሙሴ ወደ ተራራው እንደ ወጣ ሳይመለስ ስድስት ሣምንታት ገደማ በመቆጠራቸው ምን አግኝቶት ይሆን ብለው ማሰብ ጀመሩ። ለዐመጽ በተነሳሳው ህዝብ ጫና ውስጥ የወደቀው አሮን ከወርቅ የጥጃ ምስል ጣኦት ሠርቶ በመስጠት በምስሉ ፊት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ነገራቸው፡ “ከዚህም በኋላ ይበሉና ይጠጡ ዘንድ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሱ” (ዘፀ. 32፡6)። ሕዝቡ በፍጥነት ፊቱን ከእግዚአብሔር መልሶ ወደ ጣኦት አምልኮ መግባቱ ጌታንም ሆነ ሙሴን በእጅጉ አስቆጣ። እስራኤላውያን ለዚህ ጥፋታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት ከመቀበል ያተረፋቸው የሙሴ ልመና ነበር (ዘፀ. 32፡30-34)። የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በተደጋጋሚ የሚፈትንና የሚወድቁበት ኃጢአት ቢኖር ጣኦት አምልኮ ነበር። የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት የንግሥና ዘመናት በጣኦት አምልኮ ታሪክ የታጀቡ ቢሆኑም፤ ይባስ ብሎ ከነገሥታቱ መሃል አንዳዶቹ ሕዝባቸው ለእነዚህ ባእዳን አማልክት እንዲሰግዱ የሚያስገድዱ አሰቃቂ ተግባሮችን ይፈጽሙ ነበር። ሕዝቡን ከእንዲህ ያለው ታማኝነት የጎደለው ተግባር ወደ እግዚአብሔር እንዲጠሩ የተላኩ ነቢያት ተደጋጋሚ ትኩረት ይኸው ነበር። በሕዝቡ መሃል ተሐድሶና መነቃቃት እንዲመጣ ይቀርብ ከነበረው ጥሪ በተጓዳኝ ለድኾች፣ ለችግረኞችና ረዳት ለሌላቸው ወገኖች የተሻለ አያያዝ እንዲደረግ የሚጠይቁ ተማጽኖዎችም ይቀርቡ ነበር።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መዝ. 115፡1-8። ባለ መዝሙሩ እያነሳ ያለው ወሳኝ ነጥብ ምን ይመስላል?

---

---

የምናመልከውና ትኩረት እንደምናደርግበት ነገር ግልባጭ መሆን የእኛ የሰው ልጆች ዝንባሌ ነው። ይህን ተከትሎ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ዐይኖቻቸውን ከእርሱ ላይ አንስተው የጦርነት ወይም የመራባት (ፍሬያማነት) ጣኦቶች የነበሩትን የአጎራባች ሕዝቦችን ሐሰተኛ አማልክት ሲያመልኩ፤ ስለ ሰብዓዊ ወገኖች ብሎም ስለ ፍትሕ ይኖራቸው የነበረ የመቆርቆር ስሜት እየደበዘዘ መሄዱ ተፈጥሮአዊ ነበር። እስራኤላውያን ከእውነተኛው አምልኮ ማፈንገጥ በመረጡ ቁጥር፤ እንዴት ለሌሎች ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ጨምሮ፣ አመለካከታቸው በብዙ ይለዋወጥ ነበር። እነዚህ ሕዝቦች ለጌታ ታማኝ እንደሆኑ ቢጸኑ ኖሮ እግዚአብሔር በዙሪያቸው በእጦት ማዕበል ለሚንገላቱ ሰብዓዊ ወገኖች የነበረውን የመቆርቆር ስሜት በተጋሩ ነበር።

***የምናመልከው ግልባጭ በመሆናችን ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ምልከታ ያድርጉ። ዛሬ በእኛ ዘመን የዚህን መርኅ መገለጫዎች እንዴት እንመለከታቸዋለን?***

## ሰኞ ሐምሌ 29

## የአምልኮ መንስኤ

የእግዚአብሔር ሕዝቦች እርሱን ያመልኩ ዘንድ የቀረበላቸውን ያላሰለሰ ጥሪ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች የምንመለከት ሲሆን፤ እኛም ይህን የምናደርግበት ምክንያት በተደጋጋሚ ቀርቦልናል። እርሱ--እርሱ በመሆኑ፣ ለእኛ ባደረገው ነገር እና በባህሪው የተነሳ እነሆ እንድናመልከው ጥሪ ቀርቦልናል። መልካምነቱ፣ የፍትሕ አምላክ መሆኑና በምኅረት መሞላቱ በዋነኝነት ከሚጠቀሱት መሃል ናቸው። እግዚአብሔር ምን ዓይነት አምላክ እንደሆነ መለስ ብለን ስናስብ፣ ለእኛ ስላደረገልን ነገር (በተለይ በክርስቶስ መስቀል)፣ እንዲሁም ስለ ሰጠን የተስፋ ቃላት--አንዳችንም ብንሆን እርሱን ለማምለክና ለማወደስ ምክንያተ ቢሶች መሆን አንችልም።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘዳ. 10፡17-22፣ መዝ. 101፡1፣ 146፡5-10፣ ኢሳ. 5፡16፣ 61፡11። እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማወደስ መነሻ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

---

---

እነዚህ የአምልኮ መነሾዎች ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አዲስ አልነበሩም። የአዲስ ነጻነት ባለቤት በነበሩት እስራኤላውያን መሃል ይተገበሩ የነበሩ አንዳንድ አስደሳችና አጓጊ የአምልኮ ጊዜያት መንስኤዎች እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ጣልቃ የመግባቱ

ምላሽ መሆናቸው ግልጽ ነበር። ለአብነት ያህል ከግብፅ እንዲወጡና ቀይ ባሕርን እንዲሻገሩ ከተደረጉ በኋላ እግዚአብሔር እነርሱን ለመታደግ ያደረገውን ሁሉ በገዛ ዐይኖቻቸው በማየታቸው በሙሴና ማርያም ምሪት ለእግዚአብሔር ውዳሴ አቅረበው ነበር (ዘፀ. 15)።

አምላካዊው ፍትሕና ምሕረት እንዳይረሳ ሆኖ በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ልዩ ሥነ ስርዓቶች ቀርቦ ነበር። ሰዎች እነዚህን ታሪኮች ደጋግመው ለሌሎች በመንገር ህይወት በዘሩባቸው ቁጥር፤ ጌታ የሠራቸው ሥራዎች ለቀጣይ አምልኮ ዘመናቸው ብሎም ለመጪው ትውልድ አነሳሽ ኃይል መሆናቸው ቀጥሎ ነበር። ለዚህ አንድ ምሳሌ--ዘዳ. 10፡17-22 መመልከት ይቻላል።

በቅድሚያ--አምላካዊው ፍትሕ የእርሱ ባህሪ ወሳኝ ክፍል ነው። “በእውነት እግዚአብሔር ክፋትን አይሠራም፤ ሁሉን የሚችል አምላክ ፍትሕን አያጣምምም።” (ኢዮ. 34፡12)። እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ እንደ መሆኑ የፍትሕ ጉዳይ ያሳስበዋል። ይህ እርሱን እንድናመልከውና እንድናወድሰው ያደርገናል።

ሁለተኛ--አምላካዊው ፍትሕ ስለ ሕዝቡ እና ባጠቃላይ ለድኾችና ለተጨቆኑ ሰብዓዊ ወገኖች ባደረጋቸው ጻድቅ ተግባራት ታይቶአል። አምላካዊው ፍትሕ ብቻውን የባህሪው መገለጫ ሆኖ አያውቅም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምድር በገሃድ የሚስተዋለውን “የመከረኞችን ጩኸት ሰማ” (ኢዮ. 34፡28) በማለት እግዚአብሔርን ይስለዋል። ይህ ጉዳይ ውሎ አድሮ በአምላካዊው የመጨረሻ ፍርድ እና እንደ አዲስ የመፍጠር ሥራው ሙሉ ለሙሉ እውቅና የሚቸረው ይሆናል።

**ጥንት እስራኤላውያን ጌታን የሚያወድሱበት ምክንያት ከነበራቸው፤ ከመስቀሉ በኋላ ያለነው እኛ እርሱን ለማወደስ ምን ያህል የላቀ ምክንያት ሊኖረን ይችላል?**

## ማክሰኞ ሐምሌ 30

# ኃይማኖታዊ ጨቋኞች

ምንም እንኳ ያኔም ቢሆን አምልኮአቸው ዙሪያቸውን ከበዋቸው ከነበሩ ህዝቦች ጥሰው ከሚገቡ የጣኦት አምልኮ ጋር አልፎ አልፎ የተጠላለፈ ቢሆንም፤ የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት በተሻለ ሁኔታ ይገኙ በነበሩባቸው ወቅቶች ህዝቡ ፊቱን ወደ ቤተ መቅደስ መልሶ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ነቢያቱ እንደሚሉት ከሆነ ግን--ሕዝቡ በተሻለ ኃይማኖተኛ ለመሆን ያደረጋቸው ሙከራዎች እንኳ ሳይቀሩ፤ በየቀኑ ህይወታቸው ምድሪቱ ላይ ጠብቀው ካቆዩት የክፉ ተግባር እነርሱን ለመመለስ በቂ

አልነበሩም። ይፈጽሟቸው በነበሩ የአምልኮ ሥርዓቶች አማካይነት ኃይማኖተኛ ለመሆን የቱንም ያህል ጠንክረው ቢታትሩም፤ የመዝሙሮቻቸው ቅላጼ ከደኻውና ከተጨቆነው ልቅሶ መነጠል የሚችሉ አልነበሩም።

አሞጽ "ችግረኞችን የምትረግጡ፣ የምድሪቱንም ድኾች የምታጠፉ" (አሞጽ 8፡4) ሲል የእርሱን ዘመን ሕዝቦች ይገልጻቸዋል። ኃይማኖታዊ ሥርዓታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ተመልሰው ወደ ገበያ ወርደው መደብሮቻቸውን በመክፈት ያንኑ ወስላታ ንግዳቸውን ለማጧጧፍ የነበራቸውን የልባቸውን ምኞት አሞጽ ተመልክቶ ነበር "ድኻውን በብር፣ ችግረኛውንም በጥንድ ጫማ እንገዛለን" (አሞጽ 8፡6)።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 1:10–17፣ አሞጽ 5:21–24፣ ሚክ. 6:6–8። እነዚህ ሕዝቦች ይፈጽሙ ስለነበረው ኃይማኖታዊ ሥርዓት ጌታ ምን እያላቸው ነበር?

---

---

ራሳቸውን ከኃይማኖትና አምልኮ ነጥለው በሚሳለቁና በዙሪያቸው ከነበሩ ሰብዓዊ ወገኖች ሥቃይና ጭቆና በተጻራሪ በቆሙ ላይ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ጠንካራ ቋንቋ ተጠቅሞ ሲናገር ይደመጣል። "ተጸይፌአለሁ፣ ጠልቼውማለሁ" በማለት በአጠቃላይ በአምልኮአቸው መንገፍገፉን በአሞጽ 5፡21-24 እናነባለን። ጉባዔዎቻቸው የሚከረፉ መሥዋዕታቸውና መዝሙራቸውም ከንቱ እንደሆነ ይናገራል።

ሕዝቡ እንዴት ተገቢ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚችል አስመልክቶ በሚክ. 6 እየገነነ የሚሄድ አነጋገር የቀረበ ሲሆን፤ መልእክቱ ፌዝ ቀመስ አስተያየት ሳይቀር እንደ ተቀላቀለበት እናያለን። ነቢዩ ሕዝቡ ለሚቃጠል መሥዋዕት ይዞ ይቀርቡ ስለ ነበረው ነገር በመሳለቅ መጠኑን "በአንድ ሺህ አውራ በጎች፣ በዐሥር ሺህ የዘይት ፈሳሽ" (ሚክ. 6፡7) እያጎነ አስተያየት ይሰጣል። ይህን የሚለው አምላካዊውን ሞገስና ይቅርታ ለማግኘት ሲባል የበኩር ልጅን መሥዋዕት አድርጎ እስከ ማቅረብ የደረሰውን ጽንፍ የያዘ አሰቃቂ ድርጊት ከመንካቱ አስቀድሞ ነው።

በጽሑፉ መጨረሻ እግዚአብሔር በእውነት ይፈልግ የነበረው ነገር "ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትህትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?" (ሚክ. 6፡8) በማለት ይደመድማል።

***በዙሪያዎ የሚገኙ እርዳታዎ የሚያሻቸው ምስኪኖችን ከመጎብኘት ይልቅ በኃይማኖታዊ ቅርጽና ሥነ ስርዓት ላይ ይበልጥ በመጨነቅዎ የጸጸት ስሜት ተሰምቶት ያውቃል? ከዚህ ተሞክሮ ምን ተማሩ?***

**ረቡዕ** **ነሐሴ 1**

# የአምልኮ መንገድ

ነቢያቱ በአምልኮ እና በፍትሕ መካከል ስላለው ግንኙነት በሚያቀርቡት ማብራሪያ መሃል አጥብቀው የሚያሳስቡት አንድ ሌላ ቅደም ተከተል የነበረ ሲሆን ይኸውም የደኻውና የተጨቆነው ሰብዓዊ ወገን ጉዳይ እንደሚያሳስባቸውና በዕጦት የነበሩትን መርዳት ራሱን የቻለ አስፈላጊ የአምልኮ ክፍል መሆኑን ማስገንዘብ ነበር። ኢሳ. 58 ይህን የግንኙነት ሰንሰለት ግልጽ አድርጎ ያቀርባል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. ምዕ. 58። በዚህ ምዕራፍ የቀደመ ክፍል እንደ ተገለጠው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በነበረው ግንኙነት ላይ የተፈጠረው ስህተት ምን ነበር?

____________________________________________________________

________________________________________________________

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ይህ ትችት የተሰነዘረው በንቁ ኃይማኖተኛ ሕዝቦች ላይ ነበር። እግዚአብሔርን በጽኑ የሚሹ ቢመስሉም ነገር ግን አካሄዳቸው እየሠራ አለመሆኑ በገሃድ የሚስተዋል ነበር። ስለዚህ የቀድሞውን የአምልኮ ዘይቤ በመለወጥ እርሱን ከወትሮው በተለየ መንገድ ማገልገል እንደሚኖርባቸው በእግዚአብሔር ተነገራቸው። አምልኮአቸው እንዴት መሆን እንደሚኖርበት እርሱ የሚመርጥላቸው ቢሆን ኖሮ የእርሱን ፈቃድ እንዲህ ሲል ነግሮአቸዋል "የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ" (ኢሳ. 58፡6)። በተጨማሪ የተራቡትን ይመግባሉ፣ ቤት ለሌላቸው መጠለያ ይሰጣሉ፣ በእጦት ለሚገኙትም የእርዳታ እጆቻቸውን ይዘረጋሉ።

ምንም እንኳ እነዚህ እንቅስቃሴዎች እንደ ብቸኛ የአምልኮ መንገድ ባይቀርቡም ነገር ግን የአምልኮአቸው አካል ያደርጓቸው ዘንድ እግዚአብሔር አጥብቆ ሲያሳስባቸው ይታያል። በዚህም አምልኮ ትኩረት የሚያደርገው ወደ ውስጠኛው ማንነታችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በመላው እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ወገኖች ዙሪያ በረከት የሚያመጣ ይሆናል። "የኃይማኖት እውነተኛ ዓላማ ሰዎችን ከተጫናቸው ኃጢአት እያላቀቁ፣ ጠባብነትንና ጭቆናን እያስወገዱ ፍትሕን፣ ነጻነትንና ሰላምን ማስፋፋት ነው"—The SDA Bible Commentary, vol. 4, p. 306.

አምልኮ እንዲህ ዓይነቱን ቅርጽ ሲይዝ ስለሚመጣው አምላካዊ በረከት እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ በኢሳ. 58፡8-12 ቀርቦአል። እርሱ እንደሚላቸው ከሆነ--ሰዎች ስለ ገዛ ራሳቸው የሚሰጡትን ትኩረት ጋብ ቢያደርጉ ኖሮ፤ አምላካዊው ፈውስና ወደ ቀደመው ንጽህና የመመለስ ሥራ በውስጣቸው እየሠራ መሆኑን በተጨባጭ በተመለከቱ ነበር።

ደስ የሚለው ነገር በተጨማሪ ምዕራፉ እንዲህ ዓይነቱን አምልኮ በ “ደስታ” ከተሞላው ሰንበትን የመጠበቅ ትእዛዝ ጋር በአንድ አስተሳስሮታል። በሰንበትና በአገልግሎት መካከል ያሉትን አንዳንድ ጠንካራ ግንኙነቶች ቀደም ብለን የተመለከትን ቢሆንም፤ እነዚህ ቁጥሮች ግን ሁለቱንም ተግባራት ማለትም ሕዝቡ በአምልኮው እንዲነቃቃና አምላካዊውን በረከት እንዲያገኝ የቀረበውን ጥሪ አጣምረው ይዘዋል። ኤለን ኋይት በእነዚህ ጥቅሶች ላይ አስተያየቷን ስትሰጥ እንዲህ ትላለች፡ “የምሕረትና የቸርነት ተግባር ኃላፊነቶች የጌታን ሰንበት በሚጠብቁ ወገኖች ላይ አርፎአል”—Welfare Ministry, p. 121.

## ሐሙስ ነሐሴ 2

# ምሕረትና ታማኝነት

የሱስን “ከኃጢአተኞች” ጋር ለምን በላህ ብለው ከተቹት አንዳንድ የዘመኑ የኃይማኖት መሪዎች ፊት ለፊት በተጋፈጠበት ወቅት “ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ” (ማቴ. 9፡13 /ሆሴዕ 9፡13/) ተብሎ በነቢዩ ሆሴዕ የተጻፈውን ከጠቀሰላቸው በኋላ ወደ ቅዱሳን መጻሕፍት መለስ ብለው እግዚአብሔር ምን ለማለት እንደፈለገ እንዲፈትሹ ነገራቸው።

የሱስ ለሌሎች ጥንቃቄ የማድረግና አገልግሎት የመስጠት ህይወት ኖሮአል። የሱስ ከሌሎች ጋር መስተጋብር ፈጥሮ ባደረጋቸው ፈውሶች፣ ታምራቶች እንዲሁም ምሳሌያዊ አነጋገሮች--እርሱ የመራው ዓይነት ህይወት እውነተኛ አምልኮን ምርጥ በሆነ መንገድ እንደሚገልጽ የመሰከሩ ነበሩ። የኃይማኖት መሪዎች ዋንኞቹ ተቺዎቹ ቢሆኑም፤ የእርሱ ጠንካራ ሒስ ኢላማዎችም ነበሩ። እንደ ኢሳይያስ ዘመን የኃይማኖት መሪዎች ሁሉ እነዚህም ድኾችን እየበዘበዙና በዕጦት ያሉትን ቸል እያሉ በሚፈጽሟቸው ኃይማኖታዊ ሥነ ስርዓቶች ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የተለየ ግንኙነት እንደ ተረጋገጠ ያምኑ ነበር። አምልኮአቸው የድርጊቶቻቸውን ቅደም ተከተል ጠብቆ መጓዝ ባለመቻሉ፤ የሱስ እንዲህ ያለውን ግብዝነት ሳያወግዝ ማለፍ አልቻለም።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማር. 12፡38-40። የሱስ “የመበለቶችን ቤት ያራቁታሉ” በሚል የሰጠው አስተያየት ከመልእክቱ ዐውድ ውጪ ነው ወይስ በዋነኝነት ሊናገር የፈለገው ሀሳብ ነው? “እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ” የሚለውን አባባል እንዴት ይገልጹታል?

የሱስ በተለይ ለኃይማኖተኛ ሰዎች የሰጠው እጅግ አስፈሪ መልእክት ምናልባት በማቴ. 23 የሚገኘው ነው። የሱስ የእነርሱን እምነት ከገለጸበት መንገድ መረዳት እንደሚቻለው፤ እንዲህ ያለው ኃይማኖት በዕጦት ለሚኖሩ ምስኪኖች ህይወት ድጋፍ የማይሰጥ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ሸክም ነው። የኃይማኖት መሪዎች በእነዚህ ድርጊቶቻቸው--ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ በሩን ይዘጉባቸዋል (ማቴ. 23፥13)።

ከብዙ መቶ ዓመታት ቀደም ብለው የነበሩ የነቢያት ድምጾች በዚህ ዙሪያ ማስተጋባታቸው እንዳለ ሆኖ፤ የሱስም ይፈጽሟቸው በነበሩ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ግብረገብነት በጎደላቸውን ባህሪያት መካከል የነበረውን ክፍተት ፊት ለፊት አቅርቦአል። " 'እናንት ግብዞች የኦሪት መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋንኛ የሆኑትን ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር' " (ማቴ. 23:23)። ኃይማኖታዊ ስርዓቶችና አከባበሮች በራሳቸው ስህተት አለመሆናቸውን በፍጥነት እክሎ የተናገረው የሱስ--ነገር ግን ለሌሎች በጎ የመሆንን ስፍራ ሊወስዱ እንደማይገባ ተናገረ።

**እውነት አለኝ፣ እውነትን ማወቁ በቂ ነው የሚለውን ወጥመድ የሆነ አስተሳሰብ እንዴት ማስወገድ እንችላለን?**

## አርብ ነሐሴ 3

ተጨማሪ ሃሳብ፡ *Read Ellen G. White, "Isaiah 58—A Divine Prescription," pp. 29–34, in Welfare Ministry; "Woes on the Pharisees," pp. 610–620, in The Desire of Ages.*

*"የኃይማኖተኝነትን ተጨባጭ እሴቶች በጥብቅ ያሳስቡ የነበሩት ነቢያት ከሙቶዎች ዓመታት ቀደም ብለው ለእስራኤላውያን የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን እየደጋገሙ ያቀርቡ ነበር . . . ዘመን አልፎ ዘመን በተተካ ቁጥር የኃይማኖትን ቅርጽ ብቻ ይዘው ምሕረት ለማድረግ ዝንጉ የመሆን አደጋ ላይ እየወደቁ ለነበሩ፤ እነዚህ ምክረ ሀሳቦች በእግዚአብሔር ታማኞች በተደጋጋሚ ይቀርቡላቸው ነበር።"*—Ellen G. White, Prophets and Kings, pp. 326, 327.

"በኢሳይያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 58 ላይ የቀረበውን መልእክት ለሕዝባችን እንድጠቅስ ታዝዤ ነበር። ይህን ምዕራፍ በጥንቃቄ በማንበብ ለቤተ ክርስቲያኖች

ህይወት የሚያመጣውን አገልግሎት ማስተዋል ያሻል። የወንጌል ሥራ በልግስናችን እንዲሁም በአገልግሎታችን ወደ ፊት ሊራመድ ይገባል። እርዳታ ከሚያሻቸው በሥቃይ ያሉ ነፍሳት ጋር ሲገናኙ የልግስና እጅዎን ይዘርጉ። የተራቡትን ሲያገኙ ይመግቡ። ይህን ሲያደርጉ ከክርስቶስ አገልግሎት ጋር በተጓዳኝ ይራመዳሉ። የጌታ ቅዱስ ሥራ የደግነት ተግባር ነበር። በየቦታው የሚገኙ ሕዝቦቻችን በዚህ ድርሻ ይኖራቸው ዘንድ ይበረታቱ።"—Ellen G. White, Welfare Ministry, p. 29.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.ፍትሕ ማድረግንና ምሕረት መውደድን እንደ አምልኮ አካል አስበውት ያውቃሉ? ይህ ሁኔታ ለሌሎች ጥንቃቄ በማድረግ ዙሪያ ያሎትን አቋም እንዴት መለወጥ ይችላል? ስለ አምልኮ ያሎትን እሳቤስ እንዴት ይቀይራል?**

**2.በክርስትና ሕይወታችን እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን "በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን" (ማቴ. 23፡23) ችላ ከማለት እንዴት መጠበቅ እንችላለን? ምናልባት እርስዎ ትንኝን አጥርተው ግመልን ግን የዋጡበትን (ማቴ. 23፡24) ምሳሌ ከገዛ ተሞክሮዎ ማስታወስ ይችላሉ?**

**3.ግብዝነት እንደ ኃጢአት የሚታየው ለምንድን ነው? ቢያንስ መልካም ለማድረግ እየሞከርን መታየታችን የተሻለ አይሆንም?**

**4.በነቢያቱ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ለድኾችና ለችግረኞች ያለው ራእይና ጥልቅ ስሜት በዚህ ዓለም ላይ ያሎትን አመለካከት መለወጥ የሚችለው እንዴት ነው? ነቢያትን በዐይንዎ ቢመለከቱና በጆሮዎ ቢሰሙ የዛሬዎቹን የዜና ዘገባዎች ምን ይህል በተለየ መንገድ ያደምጧቸው ነበር?**

*ማጠቃለያ፡ ምንም እንኳ ምድሪቷ ላይ የተንሰራፋው ክፋት ነቢያትን ቢያሳስባቸውም፤ በተለይ ትኩረታቸው እግዚአብሔርን እንደ ራሳቸው አምላክ የሚመለከቱና እርሱን የሚያመልኩ ይሠሩት በነበረው የክፋት ሥራ ላይ ያነጣጠረ ነበር። ለነቢያትም ሆነ ለየሱስ--አምልኮ ከኢፍትሐዊነት ጋር መሳ ለመሳ አይሄድም። እንደውም እንዲህ ዓይነቱ ኃይማኖት ግብዝ ነው። እግዚአብሔር የሚሻው እውነተኛ አምልኮ ከጭቆና በተቃራኒ የሚሠራና ለድኻውና ለችግረኛው ጥንቃቄ የሚያደርግ ነው።*

# 7ኛ ትምህርት

ከነሐሴ 4–10

# የሱስ እና በእዕጦት ያለው ሰብዓዊ ወገን

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሉቃ. 1:46–55፤ 4:16–21፤ 7:18–23፤ ማቴ. 12:15–21፤ ማቴ. 21:12–16 ማር. 11:15–19፤ ኢሳ. 53:3–6።

**<u>የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-</u>" ' የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣ እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንዳወጣ፣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል" (ሉቃ. 4፡18-19)።**

የሱስ ሥጋ እንዲለብስ ከሆነባቸው ሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ አብ ምን እንደሚመስል ሊያሳየን ወደዚህ ምድር መጣ። ይህንንም በትምህርቱ፣ መሥዋዕትነቱና በሕይወቱ፤ ይኸውም ከተራ ሰዎች ጋር መስተጋብር በመፍጠር እውን አደረገ። አብዛኞቹ ድርጊቶቹ በሌሎች ህይወት ፈጣንና ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ችለዋል። ይህ የመሲህ አገልግሎት ገጽታ ብብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ በየሱስ እናት ማርያም እንዲሁም ተልዕኮውን ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ባደረገበት በመጀመሪያ ስብከቱ (ሉቃ. 4) በራሱ በየሱስ አስቀድሞ ተተንብዮ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የወንጌል ጸሐፊዎች የየሱስን ታሪክ ሲጽፉ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ቋንቋ በተደጋጋሚ ተጠቅመዋል። በዚህ መልኩ የየሱስ ሕይወት በነቢያቱ ትውፊት ውስጥ በጉልህ ታይቶአል--ለድኾችና ለተጨቆኑ የነበራቸውን ርኅራኄ ጨምሮ።

የሆነው ሆኖ የኃይማኖት መሪዎች የሱስን በጥርጣሬ ዐይን ይመለከቱት ነበር። በዘግናኙ ኢፍትሐዊ ተምሳሌነታቸውና ጨካኝነታቸው የሱስ እንዲታሰር አደረጉ፣ ፍትሕ የጎደለው ዳኝነት ሰጡ፣ በመጨረሻም ሰቀሉት። ኢፍትሐዊ ፍርድ ምንኛ ልብ እንደሚሰብር በገዛ ልጁ ሞት የደረሰበት እግዚአብሔር አብ ጠንቅቆ ያውቀዋል። እርሱ በሞቱ የክፉውን አሰቃቂ ማንነት ገልጦ አሳየ። በትንሳኤው ደግሞ የህይወት፣ የበጎነትና የደጎነት ድል አድራጊነቱን አስመሰከረ።

## እሁድ ነሐሴ 5

# የማርያም መዝሙር

ማርያም ከጥቂት ቀናት በፊት አንድ መልእክት ከገብርኤል ተቀበለች። መልእክቱ የልዑል አምላክ ልጅ፣ ይኸውም የየሱስ እናት እንደምትሆን የሚያበስር ነበር። ማርያም እነዚህን የሰማቻቸውን ቃላት ለማንም ከመንገሯ በፊት በዚያው ሰሞን በእርጅና ዘመን የነበረችውን ዘመዷን ኤልሳቤጥን ለመጠየቅ ወደ ደጋማው አገር ሄደች። የሚገርመው ኤልሳቤጥም እንዲሁ እግዚአብሔር በታምር የሰጣትን ጽንስ ለመውለድ ተቃርባ ነበር። ማርያም ገና ምንም ሳትናገር ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ማርያም ይዛ የመጣችውን የምስራች አስቀድማ አወቀች። ሁለቱም በአንድነት ሆነው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እና መልካምነት ሐሴት አደረጉ።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 1፡46-55። " 'ኃያል የሆነው እርሱ ታላቅ ነገር አድርጎልኛልና' " (ሉቃ. 1፡49) በሚል ለእርሷ ብቻ በግሏ ለሆነውና በአጠቃላይ ለሁሉም የሚተርፈውን ምስጋና ልብ ይበሉ። ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና እና አምልኮ ግላዊና ሁሉን አቀፍ አጽንኦት ሊያካትት የሚገባው ለምንድን ነው?

---

---

ይህ ከመዝሙረ ዳዊት ወይም ከሌሎች የብሉይ ኪዳን ነቢያት ጽሑፎች ጋር አቻ ሊሆን የሚችል አስደናቂ የመዝሙር ስንኝ ነው። ማርያም ስለ እግዚአብሔር አምላክ ገደብ ባለፈ አድናቆትና ምስጋና ተሞልታ ነበር። ማርያም እግዚአብሔር በገሃድ በህይወቷ እየሠራ መሆኑን ብትመለከትም ነገር ግን ከዚያ ባለፈ እርሱ ለሕዝቧና ለመላው ሰብዓዊ ዘር ያለውን የገዘፈ አንደምታም እንዲሁ በሚገባ ታስተውል ነበር።

ማርያም እንደ ነበራት ግንዛቤ ከሆነ እግዚአብሔር ኃያልና ምስጋና የሚገባው ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም መሐሪና ይቅር ባይ፣ ትሑት የሆነውን፣ መንፈሱ የተሰበረውንና ደኻውን በተለየ ዐይን የሚመለከት አምላክ ነው። መልአኩ መልካሙን የምስራች ለማርያም አብስሮ ከሄደ በኋላ እንዲህ ስትል ዘመረች " 'ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል፤ ትሑታንን ግን ከፍ ከፍ አድርጎአቸዋል፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል፤ ሀብታሞችን ግን ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል' " (ሉቃ. 1፡52-23)።

የየሱስ ምድራዊ ህይወት ጅማሬ ላይ እርሱ እንደ ገዢ--ማለትም ከወትሮው የተለየ መንግሥት ገዢ ሆኖ ሲተዋወቅ እንመለከታለን (ሉቃ. 1፡43)። አያሌ የመጽሐፍ

ቅዱስ ሐተታ አቅራቢዎች እንዳሉት ከሆነ የሱስ ሊያቋቁምና ሊመሰርት የመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት እዚህ ከተለመደው ጋር ሲተያይ የምድራዊውን መንግሥት ሥርዓተ አወቃቀር የሚገለባብጥ ነበር። የየሱስ መንግሥት ከተገለጸባቸው መንገዶች አኳያ የዚህ ምድር ገዢዎችና ባለጸጎች የተሰጣቸው ስፍራ ከሁሉ ዝቅ ያለ ሲሆን፤ ድኾች እና የተጨቆኑ ነጻ ወጥተዋል "በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል"።

***ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚገለጥባት መሣሪያ መሆን ካለባት፤ ማርያም እንዳስቀመጠችው የዚህ ዓለም ኃያላን ዝቅ--ትሑታን ደግሞ ከፍ ከፍ የሚሉበት ምሳሌ መሆን የምትችለው እንዴት ነው? ገናና ምድራዊ ስም ያላቸውንና ሀብታሞችን ሳናገልና እነርሱም የክርስቶስ ፍቅር ተቀባይ መሆናቸውን ሳንዘነጋ የእንዲህ ዓይነቱ ነገር ምሳሌ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?***

## ሰኞ ነሐሴ 6

# የየሱስ ተልዕኮ መግለጫ

የሱስ ከኢሳይያስ መጽሐፍ ጥቅል አውጥቶ ያነበበው ጥቅስ የዕለቱ የጥቅስ ንባብ እንዲሆን አስቀድሞ የተመደበ ይሁን ወይም የሱስ ሆን ብሎ ያወጣው (ኢሳ. 6፡1-2) ለመጀመሪያው ይፋዊ የስብከት አገልግሎቱ መዋሉ አጋጣሚ አልነበረም። ወይም ደግሞ ሉቃስ "'ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ' " (ሉቃ. 4፡21) ሲል የዘገበው የየሱስ አጭር ስብከት ታሪክም እንዲሁ በአጋጣሚ የሆነ አልነበረም።

የሱስ "ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል" የሚለውን የማርያም ድምጸት የአገልግሎቱ አካል ማድረግ ጀመረ። የሱስ ያደርግ የነበረውንና ለማድረግ የተዘጋጀበትን ተልዕኮ አስመልክቶ ሉቃስ የኢሳይያስን ትንቢት ተጠቅሞ ስለ እርሱ ታሪክ ቢተርክልንም፤ ነገሩ ማርያም ከ30 ዓመታት በፊት የገለጸችውና በሌላ መንገድ የቀረበበትም ነበር። ድኾች፣ በጉዳት ላይ የነበሩና የተጨቆኑ የተለየ ትኩረት የተቸራቸውና የሱስ ይዞት እየቀረበ የነበረው መልካም የምሥራች ተቀባዮች ነበሩ። የሱስ በኢሳ. ምዕ. 61 የሚገኙትን እነዚህን ጥቅሶች እንደ ተልዕኮው መገለጫ አድርጎ ወስዷቸዋል። አገልግሎቱና ተልዕኮው ሁለቱም ማለትም መንፈሳዊና ተግባራዊ መሆን ነበረባቸው። እኛ አንዳንዴ ከምናስበው በተቃራኒ እነዚህ ሁለቱ እንደማይራራቁ ማሳየት ነበረበት። ለሰዎች አካላዊና ተግባራዊ ድጋፍ ማድረግ--የሱስና ደቀ መዛሙርቱ ቢያንስ በመንፈሳዊ ረገድ አገልግሎት የሚሰጡበት ክፍል ነበር።

ጥቅሶቹን ካነበቡ በኋላ ያነጻጽሩአቸው፡ ሉቃ. 4፡16-21 እና 7፡18-23። የሱስ በዚህ መልኩ መልስ የሰጠው ለምን ይመስሎታል? በመለኮትና በየሱስ መሲህነት ዙሪያ ሊነሱ ለሚችሉ ተመሳሳይ ጥያቄዎች እርስዎ እንዴት ምላሽ መስጠት ይችላሉ?

---

---

የሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲልክ የሰጣቸው ተልዕኮ ከዚህ ተልዕኮ ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ ነበር። “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች” (ማቴ. 10፡7) ብለው ማስታወቃቸው እንዳለ ሆኖ “‘በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሱ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ’ ” (ማቴ. 10፡8) ሲል ተጨማሪ ትእዛዝ ሰጥቶአቸው ነበር። የየሱስን አገልግሎት እሴቶችና መርኅዎች በስሙ እያንጸባረቁ ለመንግሥቱ ላደማቸው ሕዝቦች መተግበር የአገልግሎታቸው አካል ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ቢሆኑ የተረሱትን፣ እንደ ሰው የማይቆጠሩትንና የጠፉት መቀላቀል ነበረባቸው።

***ይህን ሥራ ወሳኝ ከሆነው የሦስቱን መላእክት መልእክት ለጠፋው ዓለም ከመስበክ ኃላፊነት ጋር ሚዛናዊ አድርገን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው? የምናደርጋቸው ነገሮች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ “ወቅታዊውን እውነት” ከመስበክ ጋር ዝምድና ሊኖራቸው የሚገባው ለምንድን ነው?***

## ማክሰኞ ነሐሴ 7

# የየሱስ ፈዋሽነት

ወንጌል በየሱስ የታምራት ሥራ ታሪኮች የተሞላ ነው--በተለይ በፈውስ ሥራዎቹ። ኢሳይያስ በትንቢት እንደ ተናገረው ዐይነ ሥውሮችን ፈውሶአል አልፎ አልፎም ለብዙ ዘመናት የአልጋ ቁራኛ የነበሩትን ሳይቀር ከደዌ እስራት ፈትቶአል (ማር. 5፡24-34፣ ዮሐ. 5፡1-15)። ከዚህ በላቀ አንካሳው ዳግመኛ እንዲራመድ፣ እንደ እርኩስ ይቆጠር የነበረውንም ለምጻም በእጁ ዳስሶ እንዲነጻ አድርጎአል። በሰዎች አእምሮና አካል ውስጥ የተንሰራፉ አጋንንትን ገስጾ አስወጥቶአል፣ የሞተውንም ሳይቀር አስነስቶአል።

ምናልባት እነዚህ የሠራቸው ታምራቶች ሕዝቡን ወደ እርሱ የሚስቡ፣ ለብዙዎቹ ተጠራጣሪዎችና ነቃፊዎቹ ኃያልነቱን ያስመሰከሩ አድርገን እንወስድ ይሆናል። ይሁን

እንጂ ነገሮች ሁሌም የዚህ ዓይነት ገጽታ አልነበራቸውም። ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ የሱስ ከፈወሰ በኋላ የተደረገውን ለማንም እንዳይነግሩ ያዝ ስለ ነበር ነው። ሆኖም ፈውስ ያገኙ ሰዎች ድንቅ የሆነውን የምሥራች ለማንም ሳይተነፍሱ ለራሳቸው ብቻ እንዳመቁ መቅረታቸው የማይሆን ነገር ይመስላል። የሱስ እነዚህ ታምራቶች በዐይን ከመታየት የላቀ አንደምታ እንዳላቸው ለማሳየት እየሞከረ ነበር። በእርግጥ የታምራቱ የመጨረሻ ግብ ፈውስ ያገኙት ሰብዓዊ ወገኖች እርሱን ተቀብለው የዘላለም ህይወት ባለቤት መሆናቸው አይደል? ደግሞም የሱስ የፈጸማቸው የፈውስ ታምራቶች የርኅራኄው መገለጫዎችም ነበሩ። ለአብነት ያህል የሱስ 5000 ሰዎችን እንዲመግብ መንስኤ የሆነውን ማቴዎስ ሲጽፍ "ኢየሱስም ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ አይቶ ራራላቸው፤ ሕመምተኞቻቸውንም ፈወሰላቸው" (ማቴ. 14፡14)። በጉዳት የነበሩ ሰዎች ህመም ይሰማው የነበረው የሱስ አጠገቡ የነበሩትን ይረዳና መንፈሳቸውንም ያለመልም ነበር።

በማቴዎስ ወንጌል የቀረበውን ይህን የኢሳይያስ ትንቢት ያንብቡ፡ ማቴ. 12፡15-21። የሱስ ለጥቂቶች ወይም በሙቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ስላደረገው የፈውስ አገልግሎት ኢሳይያስና ማቴዎስ በተለየ ያሳዩት መንገድ ምን ይመስላል?

________________________________________

________________________________________

"ክርስቶስ የፈጸመው እያንዳንዱ ታምራት የመለኮትነቱ ምልክት ነበር። እርሱ ይፈጽማቸው የነበሩ ተግባራት አስቀድመው ስለ መሲህ የተነገሩ ቢሆንም፤ እነዚህ የምህረት ሥራዎች ፈሪሳውያኑን በተጨባጭ ያስቀይሙ ነበር። በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት እንዲሉ የአይሁድ መሪዎች ለሰብዓዊው ሥቃይ ምላሽ ቢስ ልበ ደንዳኖች ነበሩ። ስግብግብነታቸውና ጨቋኝነታቸው ክርስቶስ ያስገኘውን እፎይታ በብዙ መልኩ ሥቃይና እንግልት ውስጥ የሚከት ነበር። በመሆኑም የእርሱ ታምራቶች ለእነርሱ ግሳጼ ነበሩ።"—Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 406.

የየሱስ የፈውስ ታምራቶች የርኅራኄና የፍትሕ መገለጫዎች ነበሩ። ሆኖም በራሳቸው የሁሉም ነገር መደምደሚያ አልነበሩም። ክርስቶስ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ አጠቃላይ ዓላማ ሰዎችን ወደ ዘላለማዊ ህይወት መምራት ነበር።

**ረቡዕ** **ነሐሴ 8**

# ቤተ መቅደሱን ማጽዳት

በወንጌል የተጻፉትን የየሱስ ታሪኮች ስናነብ--ለበሽተኞችና ለህጻናት የነበረው ጥንቃቄ፣ የጠፋውን ስለ መፈለግ የተናገራቸው ታሪኮች እንዲሁም ስለ መንግሥተ ሰማይ የተናገራቸው ልብ የሚያሞቁ መልእክቶች አብልጠው ወደ ደርባባ ማንነቱ ይስቡናል። እርሱን በምንመለከታቸው ሌሎች ታሪኮች ውስጥ ደግሞ ኃይለኝነቱንና እውነትን አፍረጥርጦ መናገሩን--በተለይ በዘመኑ የነበሩትን የኃይማኖት መሪዎችና እኩይ ተግባሮቻቸውን በመቃወም ያደረጋቸው ሊያስደምሙን ይችላሉ።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 21፡12–16፣ ማር. 11፡15–19፣ ሉቃ. 19፡45–48፣ ዮሐ. 2፡13–17። እነዚህ ተመሳሳይ የወንጌል ዘገባዎች በእያንዳንዱ የወንጌል ክፍል የቀረቡበት ተጨባጭ አንደምታ ምንድን ነው?

---

---

ይህ ክስተት በእያንዳንዱ ወንጌል ውስጥ እንዲካተት የተደረገበት ምክንያት ብዙም አያስገርምም። ታሪኩ ተውኔታዊ፣ በድርጊት የተሞላና ጥልቅ ስሜት የሚታይበት ነው። በገሀድ እንደቀረበው ቤተ መቅደሱ በዚህ መልክ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ፤ ማለትም እውነተኛው አምልኮ ለመሥዋዕት በሚቀርቡ እንስሳት ግዢና ሽያጭ መተካቱ የሱስን ክፉኛ አሳስቦት ነበር። እነዚህ መሥዋዕቶች ስለ ዓለም ኃጢአት የሚሞተውን እርሱን እንዴት ባለ የእርክስና ተግባር እየወከሉ ነበር!

እንዲህ ያለው ቀጥተኛ ድርጊት ከዕብራውያን ነቢያት የቀደመ ተግባር ጋር ጥሩ አድርጎ ይዛመዳል። ይህን ድርጊት አስመልክቶ በራሱ በየሱስ ወይም የወንጌል ጸሐፊዎች ከኢሳይያስ፣ ከኤርምያስ ወይም ከመዝሙረ ዳዊት እየጠቀሱ በእያንዳንዱ የወንጌል መጽሐፍ አስተያየት ሰጥተውበታል። የሱስ ነጋዴዎችንና ገንዘብ ለዋጮችን ካበረረ በኋላ (ማቴ. 21፡11) ሕዝቡ የሱስን እንደ ነቢይ ስለ ተቀበለው ወደ እርሱ መጥተው በዚያው በቤተ መቅደሱ ቅጥር በመፈወስና በማስተማር አገለገላቸው። እነዚህ ሕዝቦች ትምህርቱን ሲሰሙና በእጆቹ ፈውስ ሲያገኙ ተስፋ በልባቸው ማንሰራራት ጀመረ።

የኃይማኖት መሪዎች የሱስን እንደ ነቢይ ቢቀበሉትም--ለሥልጣናቸውና ለማኅበራዊው አወቃቀር አደገኛ አድርገው ስለተመለከቱት በአለፉት ምዕተ ዓመታት

አባቶቻቸው ነቢያትን ለመግደል እንዳሴሩት፤ እነርሱም እርሱን ለመግደል ሴራ መጎንጎን ጀመሩ (ሉቃ. 19፡47-48)።

ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ዘመን በቤተ መቅደሱ ላይ የደረሰው ችግር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችን እንዳይደርስ እንደ ቤተ ክርስቲያን አባልነታችን የድርሻችንን ለመወጣት ምን ማድረግ እንችላለን? በመንፈሳዊነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው? ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

## ሐሙስ ነሐሴ 9

# የክርስቶስ መስቀል

እግዚአብሔር የደኻውንና የተጨቆነውን ልቅሶ የሚያይ፣ የሚሰማና የሚያጽናና አምላክ ነው። እርሱ በየሱስ ውስጥ ሆኖ የምድራችንን የመጨረሻ ውርደት፣ ሥቃይና ኢፍትሐዊነት በሚያስገርም ሁኔታ የተቀበለ አምላክ ነው። ምንም እንኳ የየሱስ ርኅራኄና መልካምነት አንድም ሳይቀር በህይወቱና በአገልግሎቱ ተገልጦ ቢታይም፤ ከመጠን ያለፈ ጥላቻ፣ ምቀኝነትና ኢፍትሐዊነት ለሞት አበቃው።

የሱስ በጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ከጸለየው የጭንቀት ጸሎት አንስቶ ሲታሰር፣ ሲፈረድበት፣ ሲገረፍ፣ ሲፌዝበት፣ ሲሠቀልና ሲሞት በነበረው ቅደም ተከተል እጅግ ዘግናኝ የመከራና የጭካኔ ሂደት ውስጥ አለፈ። ይህ ሁሉ የከፋ ሥቃይ የተፈጸመው ጥፋት ባልተገኘበት፣ ንጹህና መልካም በሆነው በእርሱ ላይ ነበር፡ “ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ” (ፊልጵ. 2፡7-8)። ምንም እንኳ በደኅንነት መነጽር አማካይነት የሱስ ስለ እኛ የከፈለውን አስደናቂ መሥዋዕትነት በመመልከት ሐሴት ብናደርግም፤ ነገር ግን የደረሰበትን ጨካኝ ተግባርና ሥቃይ ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 53፡3-6። ጥቅሶቹ ስለ በደለኞች ሲል ንጹሁ የሱስ ስለ ደረሰበት ሥቃይ ምን ይነግሩናል? ለእኛ ሲል ያለፈበትን አሰቃቂ መንገድ ማስተዋል እንድንችል ይህ እንዴት ይረዳናል?

የከፉውና የኢፍትሐዊ ፍርድ ሰለባ በመሆን ምን ዓይነት ስሜት እንዳለው እግዚአብሔር አምላክ በየሱስ ያውቀዋል። ንጹህ የሆነውን ሰው መግደል ፍጹም የጭካኔ ተግባር ቢሆንም--እግዚአብሔርን መግደል ግን እጅግ የከፋ ነው። ምንም እንኳ እኛ በተበጠሰና በወደቀ ሁናቴ ውስጥ ብንገኝም እግዚአብሔር ግን የእርሱን በጎ አሳቢነት፣ ርኅራኄና ታማኝነት እንዳንጠራጠር አድርጎ ራሱን ገለጠልን፡ "በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሠራም" (ዕብ. 4፡15)። የአምላካችን ጸባይ እንዴት ፍጹም ሆኖ ተገልጦአል! አእምሮአችን መስቀሉ በሚወክለው መልካም የምሥራች ዙሪያ ይኸውም ስለ እግዚአብሔር እንዲያሰላስል ማድረግ የምንጀምረው እንዴት ነው?

***ለጌታ በምናደርጋቸው ነገሮች በተለይ በዕጦት ለሚገኙ ስንደርስ የሱስ ስለ እኛ መሞቱን ያውም እገዛችን ለሚያሻቸው ምስኪኖች ጭምር መሥዋዕት የመሆኑን እውነታ የተልዕኮአችንና የዓላማችን ማዕከል አድርገን መያዝ የለብንም?***

## አርብ ነሐሴ 10

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** *Read Ellen G. White, "In the Footsteps of the Master," pp. 117–124, in Welfare Ministry; "Days of Ministry," pp. 29–50, in The Ministry of Healing; "The Temple Cleansed Again," pp. 589–600; "In Pilate's Judgment Hall," pp. 723–740, in The Desire of Ages.* "እግዚአብሔር ሕጉን የሚተላለፉትን እንደሚቀጣ የሚያመላክት ወሳኝ ቃል በማስረጃነት ሰጥቶአል። እርሱን በኃጢአተኞች ላይ ፍርድ እንደማይሰጥ እጅግ መሐሪ አድርገው ራሳቸውን የሚሸነግሉ ቀራኒዮ መስቀል ላይ የሆነውን መመልከት ብቻ ይበቃቸዋል። ኃጢአት ያልተገኘበት የእግዚአብሔር ልጅ ሞት 'የኃጢአት ደመወዝ ሞት' መሆኑን ይመሰክራል። እያንዳንዱ በአምላካዊው ሕግ ላይ የሚፈጸም ጥሰት ጻድቅ ፍርድ መቀበሉ የግድ ይሆናል። ኃጢአት የማያውቀው ክርስቶስ ስለ ሰዎች ኃጢአት ሆነ። ሐዘን ልቡ እስኪሰበርና ህይወቱ እስኪቀጭ የበደለኛውን መተላለፍ ተሸከመ፣ የአባቱም ፊት ከእርሱ ተሰወረ። ኃጢአተኞች ይቤዡ ዘንድ እነሆ ይህ ሁሉ መሥዋዕትነት ተከፈለ። ከዚህ ውጪ በምንም መንገድ ሰብዓዊው ፍጡር ከኃጢአት መቀጮ ነፃ ሊሆን አይችልም። እንዲህ ያለ ዋጋ ተከፍሎ የቀረበውን ሥርየት ተካፋይ

ለመሆን እንቢ የሚል ማንኛውም ነፍስ የበደለኝነቱንና የመተላለፋን ቅጣት በራሱ መቀበሉ የግድ ይሆናል።"—Ellen G. White, The Great Controversy, pp. 539, 540.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

***1.ከላይ የቀረበውን የኤለን ኋይት መግለጫ ያንብቡ። በተጨባጩ ኢፍትሐዊነት ዙሪያ ማለትም አንዳችም ኃጢአት ያልተገኘበት ክርስቶስ እንደ በደለኛ ተቆጥሮ ስለ ተቀበለው ቅጣት ተነጋገሩ። ይህን ወሳኝ እውነት ሁሌም ከፊታችን ማስቀደማችን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?***

***2.የሱስ በተደጋጋሚ ይጠቅስ የነበረውን "መንግሥት" ለማምጣት የፖለቲካ ተሐድሶ እንዲደረግ የተከራከረበት አጋጣሚ ፈጽሞ አልነበረም። ለነገሩ ዓለም ለተጨቆኑና ለተበዘበዙ ፍትሕ እናሰፍናለን፣ እኩልነት እናመጣለን በሚል መፈክር ባነሷቸው ብጥብጦችና ሁከቶች መልሰው ጨቋኝና አምባ ገነን በሆኑባቸው አሳዛኝ ታሪኮች የተሞላች ናት። አንደኛው ጨቋኝ ሌላውን ጨቋኝ ገልብጦ ሥልጣን ላይ ሲወጣ መመልከት የተለመደ ክስተት ነው። ምንም እንኳ ክርስቲያኖች የተጨቆኑትን ለመርዳት በሥልጣን ላይ ካለው ኃይል ጋር በአንድ ላይ መሥራት የሚችሉና የሚጠበቅባቸው ቢሆንም፤ ሁሌም ቢሆን ፖለቲካን ተጠቅመው እነዚህን ነገሮች ለማሳካት ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው ለምንድን ነው?***

***3.የደጎንነት እቅድ የሱስን ስለ ጠየቀው ነገር ያስቡ። ጻድቁ የሱስ ጻድቅ ላልሆንነው ስለ እያንዳንዳችን ሲል ሥቃይ ተቀበለ። ይህ ስለ እኛ የተከፈለ ታላቅ መሥዋዕትነት በክርስቶስ አዲስ ሕዝቦች የሚያደርገን እንዴት ነው?***

*ማጠቃለያ፡ በወንጌል ላይ የተዋወቅነው የየሱስ አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ሥራ ጋር ተጣቅሶ ተብራርቶአል። የወንጌል ለድኾች መሰበክ፣ የተጨቆኑ አርነት መውጣትና መንፈሳቸው ለተሰበረ የቀረበው ፈውስ የመሲህ አመላካች ሆነው በይፋ ተነግረዋል። ይህ ደግሞ የሱስ በመላው አገልግሎቱ ያሳየው እውነታ ነው። ስለ ኃጢአታችን መሥዋዕት ለሆነው ለየሱስ ኢፍትሐዊ ሞት ምስጋና ይግባውና በደላችን ይቅር መባል የሚችል ሆነ፤ የዘላለማዊ ህይወት ተስፋ ባለቤቶች ለመሆንም በቃን።*

# 8ኛ ትምህርት

ከነሐሴ 11–17

# ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማቴ. 5:2–16፣ 38–48፣ ሮሜ 12:20-21፣ ሉቃ. 16:19–31፣ 12:13–21፣ ማቴ. 25:31–46።

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-"ንጉሡም መልሶ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው' አላቸው" (ማቴ. 25፡40)።**

የሱስ ስለ ሌሎች የመቁርቆር ህይወት የመኖሩን እውነታ--በተለይ በእጦት ስለ ተንገላቱና ስለ ጠፉ ከተመለከትን በኋላ፤ ለሌሎች ጥንቃቄ ስለ ማድረግ ብዙ የሚናገረው ሊኖረው እንደሚችል መጠበቅ ይኖርብናል። ተግባራዊው የየሱስ አስተምህሮ እንደ እግዚአብሔር ተከታይነታችን እንዴት መኖር እንዳለብን ትኩረት ያደርጋል። የሱስ በዚህ ምድር እንዳደረገው ሁሉ እኛም ፍትሕ እንድናደርግ፣ ደግነት እንድናሳይና ምህረት እንዳይለየን አጥብቆ ሲያስገነዝበን መመልከት እንችላለን። ምሳሌውን የምንከተል ከሆነ እርሱ እንዳደረገው ሌሎችን እናገለግላለን። በተጨማሪ የሱስ ስለ ሰማያዊው መንግሥት ተናግሮ ነበር። የሱስ በሰጠው መግለጫ መሰረት የሰማይ መንግሥት ዛሬም የምንወርሰው ተጨባጭ እውነታ ነው። ሰማያዊው ህይወት ለወትሮው በምድራዊው መንግሥት ቅድሚያ ከምንሰጥበት በተለየ ቅደም ተከተል እሴቶችንና የሥነ ምግባር ስብስቦችን የያዘ ነው። ከሰማያዊው መንግሥት ንድፍ ጋር የሚያስተዋውቁን የየሱስ አስተምህሮዎች--እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል ብሎም ከሌሎች ጋር ዝምድና ስለ መፍጠር ያስተምሩናል። በተጨማሪ ሌሎች ለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ጥንቃቄ እያደረጉ እነርሱን ማበረታታትና ማገልገል ለእግዚአብሔር ቀጥተኛ አገልግሎት ከምንሰጥባቸው መንገዶች አንዱ ነው።

**እሑድ** **ነሐሴ 12**

# ከተራራው ስብከት ጋር መተዋወቅ

ከየሱስ ስብከቶች ረጅሙ ወይም ልዩ ልዩ አስተምህሮዎችን አሰባጥሮ የያዘ ቢኖር የተራራው ስብከት ነው። ይህ የሰማያዊውን መንግሥት ህይወት የቃኘበት ሦስት ምዕራፍ፤ ብፁዓን በሚል በሚታወቅ ቃል የሚጀምሩ እሴቶችን ይዞአል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 5፡2-16። የሱስ "የተባረኩ ናቸው" እያለ የገለጻቸው የእነዚህ ዘጠኝ እሴቶች ወይም ሰዎች የጋራ ባህሪ ምንድን ነው?

---

---

ከእነዚህ ቃላት ጥልቅ መንፈሳዊ ትግበራ ጎን ለጎን በሥራ ላይ ሊውል የሚችለውንም ምንባብ እንዲሁ መሳት የለብንም። የሱስ በራሳችን እንዲሁም በዓለም ላይ ያለውን ድኽነት ለይተን መገንዘብ እንዳለብን ተናግሮአል። በተጨማሪም ስለ ጽድቅ፣ ትህትና፣ ምህረት፣ ሰላም ስለ መፍጠርና ስለ ልብ ንጽህና ተናግሮአል። እነዚህን ምርጥ እሴቶች ስንኖራቸው በሕይወታችን ብሎም በዓለም ላይ ሊመጣ የሚችለውን ተጨባጭ ልዩነት ልብ ልንል ይገባል። ይህ በየሱስ አጽንኦት የተሰጠው በሥራ ላይ ሊውል የሚችል ምንባብ ደቀ መዛሙርቱ ለዚህ ዓለም ጨው እና ብርሃን ይሆኑ ዘንድ አጥብቆ ያስገነዝባል (ማቴ. 5፡13-16)።

ጨው እና ብርሃን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲደረግ ጣል በተደረጉበት ዐውድ ሁሉ ልዩነት ያመጣሉ። ለምግብ ጣዕም ከመስጠቱ በተጨማሪ ምግብ ነክ ነገሮች ሳይበላሹ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚረዳው ጨው፤ በዙሪያችን ለሚገኙ ወገኖች መልካም የመሆናችን ተምሳሌት ነው። በተመሳሳይ ብርሃን ጨለማን ገልጦ መሰናክሉንና አደጋውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። መኖሪያ ቤት ወይም ከተማ ደኅንነቱ አስተማማኝ እንዲሆን፣ አደጋን ከሩቅ ለይቶ ለመመልከት እንዲሁም እንደልብ ወዲህ ወዲያ ለመዘዋወር ብርሃን ወሳኝ ነው። በድቅድቅ ጨለማ ብርሃን ልንሆን እንደሚገባ የሱስ ይናገራል "ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ" (ማቴ. 5፡16)።

እነዚህ ሁለቱም ማለትም የጨው እና የብርሃን ተምሳሌቶች የየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ሁሉ ዙሪያቸውን ባሉ ሰዎች ተጽእኖ እያሳደሩ ህይወታቸውን የማሻሻል ኃላፊነት እንዳለባቸው ያሳያሉ። ካዘኑ ጋር ስናዝን፣ የልብ ንጽህና ሲኖረን፣ ትህትናን

ስንለማመድ፣ ምህረት ስናደርግ፣ ሰላም ስንፈጥርና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ ያኔ--ጨው እና ብርሃን ነን። የሱስ ስብከቱን የሚጀምረው የመንግሥቱ አካል ሆነው እያለ፤ ዝቅ ያለ ዋጋ የተሰጣቸውን እሴቶች አጥብቀን እንድንይዝ ጥሪ በማድረግ ነው።

***የቤተ ክርስቲያንዎ ማኅበረሰብ ለአካባቢው ነዋሪ እንደ ጨውና ብርሃን ሆኖ እየሠራ የሚገኘው በምን መልኩ ነው? የቤተ ክርስቲያንዎን እንቅስቃሴ ተከትሎ የእርስዎ ማኅበረሰብ የተሻለ ስፍራ መሆን የቻለው እንዴት ነው? በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚያ ስፍራ ባትኖር ማኅበረሰብዎ ላይ ምን ዓይነት ልዩነት ሊፈጠር ይችል ነበር?***

## ሰኞ ነሐሴ 13

## ክፉውን በበጎ ማሸነፍ

የየሱስን አስተምህሮ ልብ ብለን ስናጤን፤ መልእክቱን እያቀረበላቸው የነበሩትን እነዚህ ሕዝቦች ይኖሩ የነበረበትን ሁናቴ ከግንዛቤ ማስገባት ፋይዳው የላቀ ነው። የሱስ አገልግሎት መስጠት በጀመረበት አካባቢ ብዙ ሰዎችን ወደ እርሱ መሳብ ችሎ ነበር (ማቴ. 4፡25፣ 5፡1)። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ በሮም ንጉሣዊ አስተዳደር ስር የሚኖሩ ተራ ሕዝቦች ሲሆኑ ከመካከላቸው ጥቂቶቹ ግን የአይሁድ ገዢዎችና የኃይማኖት መሪዎች ነበሩ። የተራው ሕዝብ የዕለት ከዕለት ሕይወት አስቸጋሪ ነበር። በህይወታቸው እጅግ በጣም ውሱን አማራጮች ብቻ የነበሯቸው እነዚህ ሕዝቦች በከፍተኛ ግብር ጫና እና ኃይማኖታዊ ወግ ቀንበር ስር ወድቀው ነበር።

እነዚህን ሕዝቦች ሲያስተምር፣ የአኗኗራቸው ሁኔታ ያሳሰበው የሱስ በየትኛውም ሁናቴ ቢገኙ፤ አሁን ከሚኖሩት በተሻለ ክብርና ወኔ የሚመላለሱበትን አቅጣጫ እያመላከታቸው ነበር። ለዚህ አንድ ምሳሌ በማቴ. 5፡39-48 ማግኘት እንችላለን፡ “ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ አዙርለት”፣ “ካባህን ጨምረህ ስጠው”፣ “ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ”--የተሰኙት በስፋት ከሚታወቁት መካከል ናቸው።

የሱስ በዚህ ስፍራ የገለጻቸው ትዕይንቶች የአብዛኞቹ አድማጮቹ የተለመዱ የዕለት ከዕለት ህይወት ነበሩ። እነዚህ ሕዝቦች በበላዮቻቸው ወይም በጌቶቻቸው ተደጋጋሚ ጥቃት ደርሶባቸዋል። በተደጋጋሚ ዕዳ ውስጥ በመግባታቸው ንብረቶቻቸውን ለመሬቱ ጌታ ወይም ለአራጣ አበዳሪው አስረክበዋል። ቅኝ ገዢዎቻቸው የሮም ወታደሮች ከባድ ሥራ እንዲሠሩ ጫና ያደርጉባቸው ነበር። ሕዝቡ ለሚደረግበት

ጫና ሐቀኛ ምላሽ እንዲሰጥ፣ ለጨቋኞቻቸው የማይገባውንና የተሻለውን ክብር እንዲቸር የሱስ ሕዝቡን አስተምሮአል። እነዚህ ጨቋኞች ሥልጣናቸውን ያለአግባብ ለመጠቀም በሞከሩ ቁጥር ሕዝቡ እንዴት መላሽ መስጠት እንዳለበት ሁልጊዜም ምርጫ ያለው ሲሆን፤ ይኸውም ውስጣቸውን ፈንቅሎ ለመውጣት የሚፈልገውን አመጸኝነት ገትተው በቸርነት በተሞላ ምላሽ የሚፈጸመውን ክፉ ድርጊት፣ ጭቆና እና ኢፍሐዊነት ገልጦ ማሳየት በመቻል ነው።

ጥቅሶቹን ያስተያዩ፡ ማቴ. 5፡38-48 እና ሮሜ 12፡20-21። እነዚህን ሥር ነቀል የለውጥ መርኆዎች በህይወታችን መኖር ያለብን እንዴት ነው?

---

---

**የሱስ ኦሪትንና ነቢያትን በአንድ በማጠቃለል የብሉይ ኪዳንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፍሬ ነገር ወርቃማ ሕግ በመባል በሚታወቀው ቀለል ያለ መርኅ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል፡ "'ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው' " (ማቴ. 7፡12)። ትእዛዙ የቱንም ያህል ዋጋ ሊያስከፍለን ቢችል እንኳ በዚህ ስፍራ የተሰጠንን ትእዛዝ ለመተግበር ከአሁን ጀምሮ ጥረት ለማድረግ የሚንቀሳቀሱበት መንገድ ምን ሊሆን ይችላል?**

## ማክሰኞ ነሐሴ 14

## ደጉ ሳምራዊ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 10፡25-27። ለየሱስ ጥያቄ ያቀረበው ሕግ ዐዋቂ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለውን ህይወት ለመኖር መሰረታዊ ያላቸውን የብሉይ ኪዳን ትእዛዛትን በአጭሩ አቅርቦለት ነበር። ለመሆኑ እነዚህ ሁለት ትእዛዛት እንዴት ይተሳሰራሉ?**

---

---

---

የሱስ ጥያቄ ሲቀርብለት ይሰጥ የነበረው መልስ ድምዳሜ ጠያቂው አገኘዋለሁ ብሎ ከሚጠብቀው የተለየ ውጤት ይዞ ይመጣ ነበር። "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" በሚል በዘሌዋ. 19፡18 ለተሰጠው መመሪያ ምላሽ ብዙዎች በእርሱ ዘመን

የነበሩ ኃይማኖተኛ ሰዎች የዚህ የ "ባልንጀራ" መርኀ መጠንና ገደብ የት ድረስ ነው-- በሚለው ዙሪያ ሰፊ ክርክር ያካሂዱ ነበር።

ሰዎች መውደድ ያለባቸው ባልንጀሮቻቸውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለሁሉም ሰው በጎ ማድረግ እንደሚገባ በመናገርና የስያሜውን ፍቺ ሰፋ አድርጎ በማቅረብ፤ የሱስ ተከታዮቹ እንዲያስተውሉት የነበረውን ብርቱ ፍላጎት አሳይቶአል፡ "'እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ። እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሐዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኃጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል'" (ማቴ. 5፡44-45)።

ነገር ግን የኃይማኖት ሕግ ዐዋቂው የሱስን ሊፈትነው ስለፈለገ ሰፊ ክርክር ይካሄድበት ወደ ነበረው ጥያቄ በመውሰድ፡ "ባልንጀራዬ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው (ሉቃ. 10፡29)። የሱስ በምላሹ የደጉን ሳምራዊ ታሪክ ቢነግረውም፤ "ባልንጀራ" ለተሰኘው ስያሜ ፍቺ መስጠት የመልሱ መጨረሻ አልነበረም። ይልቁንም በሥራ ላይ እንዲያውል የነገረው ይህን ነበር--"የአንተን እርዳታ ለሚሹ ሁሉ ፈጥነህ ባልንጀራቸው ሁን!" (ሉቃ. 10፡36-37)።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 10፡30-37። የሱስ በመንገድ ላይ ወድቆ እርዳታቸውን ይሻ የነበረውን ሰው በተመለከቱ ሦስት ገጸ ባህሪያት መካከል ያደረገው ንጽጽር አንደምታው ምንድን ነው?

---

---

ራሳቸውን ኃይማኖተኛ እያደረጉ ነገር ግን ስለ ሌሎች ሥቃይና እንግልት ግድ በማይሰጣቸው ላይ የሱስ የሰላ ትችት ሲሰነዝር መመልከት የተለመደ ነበር። "ክርስቶስ በደጉ ሳምራዊ ታሪክ የእውነተኛ ኃይማኖትን ተፈጥሮ ስሎልናል። እውነተኛ ኃይማኖት የሚገለጠው ሥርዓትና ወግ በመጠበቅ ሳይሆን በፍቅር የተሞሉ ተግባራትን በመፈጸም፣ ለሌሎች በጎ በማድረግና ከልብ በመነጨ መልካምነት ነው።"—Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 497.

እግዚአብሔር ጥሪ የሚያቀርበው የእርሱ ተከታዮች ለመሆን ለሚሹ ሁሉ እንደሆነ ለማሳየት የፈለገው የሱስ በአስተምህሮው--ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልሆነ ተደርጎ ይቆጠር የነበረን የባዕድ አገር ሰው ተጠቀመ። እንደ መጀመሪያ አድማጮቹ

ሁሉ፤ እኛም ወደ የሱስ ቀርበን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ምን ማድረግ እንዳለብን ብንጠይቀው፤ ሊሰጠን የሚችለው የመጨረሻ ትእዛዝ--የእናንተን እርዳታ ለሚሹ ሁሉ ፈጥናችሁ ባልንጀራችው ሁኑ፤ የሚል ይሆናል።

## ረቡዕ ነሐሴ 15

## ሀብታሙ ሰውና አልዓዛር

ስለ ሀብታሙ ሰው እና ስለ አልዓዛር በቀረበው ምሳሌያዊ ታሪክ (ሉቃ. 16፡19-31) የሱስ የሁለት ሰዎችን ማለትም የአንድ ሀብታም እና ፍጹም ደኻ የነበረን ሰው ህይወት በንጽጽር ያቀርባል። እንደ ዛሬው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የሕዝብ ጤና ተቋማት ባልነበሩበት በዚያ ዘመን በከፍተኛ እጦት ውስጥ የነበሩ ምስኪኖችና አካል ጉዳተኞች በሀብታሞች ደጃፍ ተኮልኩለው ይለምኑ ነበር። ሀብታሞች በጥቂቱም ቢሆን ለድኾች የችሮታ እጆቻቸውን ዘርግተው ሥቃያቸውን ያስታግሱላቸዋል ተብሎ ይጠበቃል። በዚህ ታሪክ የቀረበው ሀብታም ሰው ግን "በብርቱ ሥቃይ ለነበረው ወንድሙ ንፉግና ግዴለሽ ነበር"—Ellen G. White, Christ's Object Lessons, p. 261. የምድራዊ ህይወታቸው ሁኔታ ሳይለወጥ ቢቀርም--ነገር ግን ሲሞቱና በእግዚአብሔር ሲዳኙ የነበራቸው ስፍራ በሚገርም ሁኔታ ተለዋወጠ።

ጥቅሶቹን ያስተያዩ፡ ሉቃ. 16፡19-31 እና ሉቃ. 12፡13-21። በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች መሃል ያለው መመሳሰልና ልዩነት ምንድን ነው? በአንድነት ምን ያስተምሩናል?

---

---

ሰዎቹ ክፉ ተግባር ፈጽመው ወይም ግፍ ሠርተው ሀብት እንዳካበቱ የሚጠቁም ምንም ዓይነት ማስረጃ በሁለቱም ታሪኮች አናገኝም። ምናልባት ሁለቱም ሰዎች ጠንክረው ሠርተው፣ ንብረታቸውን በአግባቡ አስተዳድረውና በእግዚአብሔር ተባርከው ሊሆን ይችላል። ሆኖም በህይወት ላይ በነበራቸው አመለካከት ይሁን ወይም በእግዚአብሔር፣ በገንዘብ ወይም በሌሎች ነገሮች ብቻ አንድ የተፈጠረ የከፋ ስህተት ነበረ። ይህ ደግሞ እጅግ የላቀውን ዋጋ ማለትም የዘላለምን ህይወት አሳጥቶአቸዋል።

በየሱስ ዘመን ይንጸባረቅ ከነበረው ከህይወት በኋላ ዝነኛ ምናባዊ አመለካከት በመነሳት፤ በዚህ ህይወት የምናደርጋቸው ምርጫዎች ለቀጣዩ ተጽእኖ እንዳላቸው የሀብታሙ ሰውና የአልዓዛር ታሪክ ያስተምረናል። እርዳታችንን አጥብቀው ለሚሹ

የምንሰጠው ምላሽ ምርጫዎቻችንና ቅድሚያ የምንሰጣቸውን ነገሮች ገልጸው ያሳያሉ። "አብርሃም" በሥቃይ ውስጥ ወዳለው ሀብታም ሰው እያመላከተና የተሻለውን ስለ መምረጥ መጽሐፍ ቅዱስ ከበቂ በላይ አቅጣጫዎችን እንደሚሰጥ እየጠቆመ "ሙሴና ነቢያት አሏቸው፤ እነርሱን ይስሙ" (ሉቃ. 16፡29) ሲል መለሰለት።

የሱስ እንዳስተማረው ከሀብት ጋር የሚመጣን ፈተና መቋቋም ካልቻልን በቀር ከመንግሥቱ ሊያስቀረን፣ ከሌሎች ሊነጥለንና እኔነትን የሙጥኝ ብለን እንድንቀር ያደርገናል። በቅድሚያ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንሻ በመቀጠል የተቀበልነውን በረከት በዙሪያችን ላሉ በተለይም በእጦት ለሚንገላቱ እንድናካፍል የሱስ ጥሪ ያቀርብልናል።

***የእርስዎ የገቢ ሁኔታ የቱንም ዓይነት ሊሆን ቢችል፤ ገንዘብ ወይም የገንዘብ ፍቅር ክርስቲያኖች በህይወታቸው ትኩረት ሊያደርጉ የሚገባውን ነገር እንዳያዛባ እንዴት መጠንቀቅ ይችላሉ?***

## ሐሙስ ነሐሴ 16

## ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት

የሱስ ለቀረበለት ጥያቄ ከተጠበቀው ፍጹም የተለየ መልስ ከሰጠባቸው ክስተቶች ሌላኛው በማቴ. 24 እና 25 ይገኛል። ደቀ መዛሙርቱ ወደ የሱስ ቀርበው በየሩሳሌም ስለሚገኘው ቤተ መቅደስ መፍረስና ስለ የሱስ ዳግም ምጽአት ጠይቀውት ነበር (ማቴ. 24፡1-3)። የሱስ ለዚህ ጥያቄ የሰጠው ረዘም ያለ ምላሽ መደምደሚያው የተራቡትን ማብላት፣ የተጠሙትን ማጠጣት፣ እንግዶችን መቀበል፣ የታረዘውን ማልበስ፣ የታመመውን መንከባከብና የታሰሩትን መጠየቅ ነበር። "ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው" (ማቴ. 25፡ 40፤45)።

ይህ ነጥብ የሱስ በመጨረሻው ፍርድ ጥያቄዎች ዙሪያ ትምህርቱን በመጀመር ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጣቸው ሥዕል ጋር ትስስር አለው። የሱስ በደቀ መዛሙርቱ በቀረቡለት ጥያቄዎች ስለ የሩሳሌም ጥፋት ምልክቶችና ማስጠንቀቂያዎች እንዲሁም ስለ መጨረሻው ዘመን በዛ ያሉ ቀጥተኛ መልሶችን በመላው ማቴ. 24 የሰጠ ቢሆንም፤ ተግቶ ስለ መጠበቅ አስፈላጊነትና በዳግም ምጽአቱ ተስፋ ብርሃን በተሻለ ህይወት ስለ መመላለስም እንዲሁ ተናግሮአል። ባልታሰበ ጊዜ ሊደርስ ወይም ሊዘገይ የሚችለውን ሙሽራ ለመቀበል ሁሌም ተዘጋጅተን መጠበቅ እንዳለብን

አጥብቆ የሚያሳስበው የዝንጉዎቹና አስተዋዮቹ ልጃገረዶች ምሳሌ ታሪክ በማቴ. 25 የመጀመሪያ ክፍል ቀርቦአል። የሦስቱ አገልጋዮች ታሪክ ደግሞ እርሱን እየተጠባበቅን--እንደሚፈለግብን መመላለስና ሥራችንን በትጋት መሥራት እንዳለብን ይነግረናል። እንዲሁም ስለ በጎችና ፍየሎች የቀረበው ምሳሌያዊ ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተለይ አጥብቀው ሊጠመዱ በሚገባቸው ኃላፊነቶች ዙሪያ ይናገራል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 25፡31-46። የሱስ ስለ ምን እየነገረን ነው? ለምንድን ነው ይህ ደህንነት በሥራ ያልሆነው? እዚህ ላይ የሚያድን እምነት ምን ማለት እንደሆነ አስመልክቶ አምላካዊው ቃል ምን ያስተምረናል?

---

---

ሌሎችን ስናገለግል እርሱን እንዳገለገልንና ለእርሱ እየሠራን ተደርጎ እንደሚቆጠር አስመልክቶ የሱስ የሰጠው ይህ መግለጫ በሁሉም ግንኙነቶቻችንና አመለካከቶቻችን ላይ ተሐድሶ ሊያመጣ ይገባል። የሱስን ምሳ ወይም እራት ሲጋብዙት ወይም ደግሞ በሆስፒታል ሲጠይቁት በዐይነ ህሊናዎ ለመሳል ይሞክሩ። ይህን አገልግሎት ለማኅበረሰባችን አካል ለሆኑ ስናበረክት ለእርሱ እንዳደረግን እንደሚቆጠር የሱስ ነግሮናል። አቤቱ እንዴት ያለ አስደናቂ ዕድል ሰጥቶናል!

**የሱስ በእነዚህ ጥቅሶች የተናገራቸውን መልእክቶች በጸሎት መንፈስ ሆነው ያንብቧቸው። የሱስ ራሱን ከተራቡ፣ ከታረዙና ከታሰሩ ሰዎች ጋር ካዛመደበት ከዚህ ጽንሰ ሀሳብ ምን እንረዳለን? እንዴት መመላለስ እንዳለብን አስመልክቶ ይህ በእኛ ላይ ምን ዓይነት ብርቱ ግዴታዎች አስቀምጦአል?**

## አርብ ነሐሴ 17

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** *Read Ellen G. White, “The Good Samaritan,” pp. 497–505, and “ ‘The Least of These My Brethren,’ ” pp. 637–641, in The Desire of Ages; “ ‘A Great Gulf Fixed,’ ” pp. 260–271, “ ‘Who Is My Neighbour?’ ” pp. 376–389, in Christ's Object Lessons.*

“ክርስቶስ የመለያየትን፣ የራስ ወዳድነትንና ከፋፋዩን የጠባብ ብሔርተኝነት ግድግዳ በማፈራረስ ለሁሉም ሰብዓዊ ቤተሰብ ፍቅርን ያስተምራል። ሰዎችን ከራስ ወዳድነት ጠባብ ቀለበት ውስጥ አውጥቶ ከፋፋይ የሆኑ የክልል ድንበሮችንና ሰው ሰራሽ ማኅበረሰባዊ ልዩነቶችን ያስወግዳል። እርሱ በጎረቤቶችና በመጻተኞች፣ በጓደኞችና

በጠላቶች መካከል አንዳችም ልዩነት አያደርግም። እያንዳንዱን ችግርተኛ ነፍስ እንደ ባልንጀራችን፤ ዓለምን ደግሞ እንደ *ሥራ* መስካችን እንድንመለከት ያስተምረናል።”— Ellen G. White, Thoughts From the Mount of Blessing, p. 42.

*“ወርቃማው ሕግ እውተኛ የክርስቲያኖች ሕግ ነው። ከዚህ መደበኛ ሕግ ጋር ገጣሚ ያልሆነ ሁሉ አሳች ነው። ክርስቶስ ራሱን ስለ ሰብዓዊው ፍጡር በመስጠት ያከበረውን ስብዕና ዝቅ አድርጎ የሚመለከት፣ ስለ ሰብዓዊው እጦት፣ ሥቃይ ወይም መብት ግዴለሽ እንድንሆን የሚመራ ኃይማኖት ሐሰተኛ ነው። የደኻውንና በሥቃይ ውስጥ ያለውን የበደለኛውን ሰብዓዊ ወገን መብት ስንንቅና ስናቃልል ራሳችንን በክርስቶስ ላይ ክህደት ከሚፈጽሙ ተርታ እንፈርጃለን። ክርስትና በዓለም ላይ ያለው ኃይል እጅግ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት ሰዎች የክርስቶስን ስም መጠሪያቸው እያደረጉ ባህሪውን ግን በሕይወታቸው በመካዳቸው ነው”*—Ellen G. White, Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 136, 137.

# የመወያያ ጥያቄዎች

**1.በዚህ ሣምንት ካጠናናቸው መሃል ይበልጥ ለእርስዎ ተወዳጅ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው? ለምን?**

**2.ኤለን ጂ. ኋይት ለሰብዓዊው እጦት፣ ሥቃይ ወይም መብት ግዴለሽ ወደ መሆን ሊመራን ስለሚችል ኃይማኖት የጻፈቸውን መልእክት ይመልከቱ። እውነት ስላለን ምንም የሚመጣብን ነገር አይኖርም የሚለውን ወጥመድ በማስወገድ ረገድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ለምንድን ነው?**

**3.የ “እውነት” ባለቤት መሆን ስለሚጠይቀው ነገር በሐሙስ ጥናት የቀረቡት ጥቅሶች ምን ያሳዩናል?**

*ማጠቃለያ፡ የሰማይ ዜጎችና የእግዚአብሔር መንግሥት ወኪሎች በዚህ ምድር ሊኖራቸው ስለሚገባው የተለየ ዓይነት አኗኗር ጅማሮ የየሱስ አስተምህሮዎች በቂ ገለጻ ያደርጋሉ። ለድኾችና ለተጨቆኑ ጥንቃቄና ድጋፍ በማድረግ ዙሪያ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን መሰረት አድርጎ የገነባውን መልእክት ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የሚያስተጋባው ጌታ፤ ተከታዮቹ የእርሱን ዳግም ምጽአት እየተጠባበቁ በርኅራኄና በምኅረት የተሞላ ህይወት በመኖራቸው ዙሪያ አጽንኦት ይሰጣል።*

# ፱ኛ ትምህርት

ከነሐሴ 18–24

# አገልግሎት በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሐዋ. 2:42–47፣ 4:32–37፣ ማቴ. 25:38-40፣ ሐዋ. 9:36፣ 2ቆሮ. 8:7–15፣ ሮሜ 12፣ ያዕ. 2:1–9፡፡

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-“በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጹህና ነውር የሌለበት ኃይማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኩሰት ራስን መጠበቅ ነው” (ያዕ. 1፡27)፡፡**

ታላቁ ተልዕኮ በመባል የሚታወቀው በማቴ. 28፡18-20 የምናገኘው መልእክት ቢያንስ በክርስቲያኖች ዘንድ በጉልህ ይታወቃል፡፡ ጥቅሱ የተልዕኮአችን መገለጫ በመሆን አዘውትሮ ከማገልገሉ በተጨማሪ ለማንኛውም ዓይነት የወንጌል እንቅስቃሴና የሥራ እቅዶች በአነሳሽነት ይታወቃል፡፡ እርግጥ ነው በእነዚህ ጥቅሶች መነሳሳት ያገኙ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለማሰራጨት በመላው የምድር ክፍል ተንቀሳቅሰዋል፣ ይህን ተከትሎ አልፎ አልፎ ከፍተኛ ዋጋ እስከ መክፈልም ደርሰዋል።

የሱስ ታላቁን ተልዕኮ ሲሰጥ ምን ብሎ ነበር? ሕዝቦችን ደቀ መዝሙር ስለ ማድረግ፣ ስለ ማጥመቅ እና ስለ ማስተማር ከነገራቸው በኋላ “ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው” (ማቴ. 28፡20) አላቸው፡፡ ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የሱስ ከሰጠን ትእዛዛት መካከል አብዛኛው ችግረኞችን፣ ጉዳት የደረሰባቸውንና እራሳቸውን መርዳት የማይችሉትን ከመንብኘትና ከመርዳት ጋር ቁርኝት አለው፡፡ እነዚህ ለየሱስ የመጀመሪያ ደቀ መዝሙሮች የተሰጡ መመሪያዎች ከዚያ ቀደም ተሰምተው ወይም ታይተው የማይታወቁ አለመሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ ይልቁንም የሱስ አስቀድሞውኑ ከእነርሱ ጋር የመሰረተው ተልዕኮ ቀጣይ አካል ነው፡፡ እንዲህ ያለው የየሱስ አስተምህሮ--የታላቁ ተልዕኮ አካል በመሆን በአዲሷ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ህይወት ውስጥ በግልጽ መታየት ይችላል፡፡

## እሁድ ነሐሴ 19

# አዲስ ዓይነት ማኅበረሰብ

ከየሱስ ዕርገትና ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ በአንድ የተሰባሰቡት አማኞች በፈጣን ዕድገት የመሰረቷት ይህች የቀደመች ቤተ ክርስቲያን--ከየሱስ ተከታዮች መሃል በዓይነቱ አዲስ በሆነ ማኅበረሰብ እና በቀደሙት ደቀ መዛሙርት ትመራ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ አዲስ ማኅበረሰብ እንዲሁ በራሱ የተቋቋመ ሳይሆን በየሱስ አስተምህሮዎችና አገልግሎት እንዲሁም ረጅም ዘመን ባስቆጠሩ የዕብራውያን ቅዱሳት መጻሕፍትና ነቢያቶች ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 2፡42-47፣ 4፡32-37፡፡ ስለ ቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ በቀረቡት በእነዚህ መግለጫዎች ምን ዓይነት ቁልፍ መሰረታዊ ነገሮች ይመለከታሉ?

---

---

እስራኤላውያን አምላካዊን ንድፍ የተከተለውን ሐቀኛና በቸርነት የተሞላ ማኅበረሰብ ለመመስረት ያስችላቸው የነበረውን ህይወት በሙላት ሳይኖሩ ያለፉ ቢመስሉም፤ የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ግን "'በመካከልህ ደኻ አይኖርም'" (ዘዳ. 15፡4) በሚል የተሰጠውን መመሪያ በጽሞና ተቀብላ ሥራ ላይ አውላ ነበር፡፡ እምነታቸው በተግባር ይገለጥ ከነበረባቸው መንገዶች አንዱ ቁሳዊ ሀብታቸውን በጋራ የመጠቀም ማኅበራዊ አኗኗራቸው ነበር፡፡ መሬታቸውን ሳይቀር እየሸጡ ገንዘቡን (ሐዋ. 4፡34-5፡2) ለአማኝ ወገኖቻቸው ችግር መቅረፊያና በዘላቂ ማቋቋሚያ ያውሉት ነበር፡፡ ደግሞም ገና በሚገባ ካልጠናው ማኅበረሰብ ውጪ ወደ ነበሩ ሰዎች ለመድረስ ጭምር--በተለይ በፈውስ አገልግሎት (ሐዋ. 3፡1-11፣ 5፡12-16) በረከት ለመሆን ይሠሩ ነበር፡፡

ሆኖም ይህ ማኅበረሰብ ማንኛውም ነገር ፍጹም በሆነ ለዛና መዋሃድ ይሠራበት የነበረ፣ እንከን ዐልባውና ምናባዊው utopian society አልነበረም፡፡ የአማኞች ቁጥር እያደገ በሄደ ቁጥር እነዚህን ሐብቶች በማስተዳደሩ ዙሪያ ውጥረቶች እየጨመሩ መጡ--በተለይ በየዕለቱ ይከናወን የነበረው ምግብ የማደል አሠራር ላይ መበለቶች ችላ ተብለዋል በሚል (ሐዋ. 6፡1)፡፡ የቡድኑ የበላይ ኃላፊዎች የነበሩት ደቀ መዛሙርት ሙሉ ትኩረታቸውን ማድረግ የፈለጉት ወንጌል በመስበክ አገልግሎት ላይ ነበር፡፡ ስለዚህ በመሀላቸው ለተፈጠረ ችግር መፍትሔ የሚሆን አንድ ግብረሃይል ለማቋቋም ወሰኑ፡፡

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ተጨባጭ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ሰባት አባላት ያሉት አንድ ዘርፍ ተቋቋመ፡፡ ይህ ዘርፍ ምናልባት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከሚሰጡ የተለያዩ ዘርፎች ቀዳሚውን እውቅና ያገኘው ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ ተግባራዊ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ህይወትና ምስክርነት ያለውን አስፈላጊነትን ያሳየ ነበር፡፡ "በሙሴ እና በዳዊት ዘመን በሕዝቡ መሃል የነበሩ መሪዎችን ይመሩ የነበሩ ተመሳሳይ የቅድስናና የፍትሕ መርኅዎች፤ ወንጌልን እንድትሰብክ ኃላፊነት የተሰጣትንና አዲስ የተቋቋመችውን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ መምራት ነበረበት፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 95.

***የዚያ የቀደመ ማኅበረሰብ ሁኔታ ምን ይመስል እንደ ነበር በዐይነ ህሊናዎ ለመመልከት ይሞክሩ፡፡ እኛ ዛሬ እነዚያን መርኅዎች ማንጸባረቅ የምንችለው እንዴት ነው?***

## ሰኞ ነሐሴ 20

# የዶርቃ አገልግሎትና ምስክርነት

የሱስ " ' በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ' " (ሐዋ. 1፡8) ሲል አስቀድሞ እንደተነበየው ቤተ ክርስቲያን እያደች መሄድ ጀመረች፤ አዳዲስ አማኞችም እምነቱንና የየሱስን አገልግሎት መቀበል ጀመሩ፡፡ ከእነዚህም መካከል ዶርቃ አንዷ ነበረች፡፡ በኢዮጴ ትኖር የነበረችው ዶርቃ--ጣቢታ በመባልም እንዲሁ ትታወቅ ነበር፡፡ የየሱስን መመሪያ ከልብ ተቀብላ ትተገብር የነበረችው ዶርቃ የታረዙትን ስታለብስ ለራሱ ለየሱስ እንዳደረገች ይሰማት ነበር (ማቴ. 25፡38፣ 40)፡፡

የዶርቃን አገልግሎት አስመልክቶ በሐዋ. 9፡36 የቀረበውን መግለጫ ያንብቡ። የእርስዎ ህይወትና አገልግሎት ከዚህ ይዞታና አቀራረብ በተመሳሳይ እንዴት ይገለጻል? እርስዎ እንዴት ቢገለጹ ይመርጣሉ?

________________________________________

________________________________________

ዶርቃ እንደ "ደቀ መዝሙር" (ሐዋ. 9፡36) የተገለጠችበት አገልግሎት፣ ታማኝነት፣ ጉልበትና በሌሎች ላይ የነበራት ትኩረት ከመኖሪያ ከተማዋ ባሻገር እንድትታወቅ አስችሏት ነበር፡፡

 

ጴጥሮስ ለኢዮጴ ቅርብ በነበረው በልዳ አማኞችን እየጎበኘ መሆኑ ሲሰማ፤ የኢዮጴ ሰዎች ፈጥኖ እንዲመጣ መልእክት ላኩበት (ሐዋ. 9፡37-41)። ጴጥሮስ በዚያ እንደ ደረሰ ለድኾች እርዳታ ታደርግ የነበረችውና ያለ ጊዜዋ የሞተችው ዶርቃ ድጋፍ ያደረገችላቸውን ብዙ ሰዎች አገኘ። ዶርቃ የሠራቻቸውን ልብሶች ለጴጥሮስ ያሳዩ የነበሩት መበለቶች እንዴት ለምስኪን ደራሽና ርኅሩኅ ሴት እንደነበረች አስመልክቶ ብዙ ታሪኮች ሳይነግሩት እንዳልቀረ ይታመናል።

ጴጥሮስ ለዶርቃ ከጸለየ በኋላ እግዚአብሔር እስትንፋሷን መመለሱ፤ ብዙዎች ስለ ሌሎች በጎ ቀን ከሌት ደፋ ቀና ቢሉም እንኳ ህይወት ሁሌም በአስተማማኝ ለመቀጠሏ ዋስትና አለመኖሩን ያሳያል። ለነገሩ ዶርቃ እንኳ መጀመሪያ ታማ ነበር። ከዚያም ያው አይቀሬው ሞት መጣ። ነገር ግን ከቀደሙት ዲያቆናት አንዱ የነበረውና የቤተ ክርስቲያን መበለቶችን እንዲያገለግል ኃላፊነት የተሰጠው እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ሰማዕት ለመሆን በቃ (ሐዋ. 7፡54-60)። የአገልግሎት ህይወት ሁሌም አልጋ በአልጋ አይደለም--አባጣ ጎርባጣም እንጂ!

በዶርቃ ህይወትና ሞት የተለየ እውቅና የተቸራቸው ሁለት ነገሮች ማለትም--አምላካዊው ፍቅር እና ኃያልነት በኢዮጴ ሕዝቦች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደ ነበራቸው መመልከት ይቻላል፡ “ይህም ነገር በመላው ኢዮጴ ታወቀ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ” (ሐዋ. 9፡42)።

***መቼም ማለፍ አይቀርምና እርስዎም አንድ ቀን ቢያልፉ፤ በጎነትዎና አስተዋጾዎ እንደ ዶርቃ የብዙዎችን ልብ የሚሰብርና እንዲታወሱ የሚያደርግ ይሆን? የመልካም አገልግሎት ቅርስ ትተን ማለፍ የምንችለው እንዴት ነው? ዶርቃ የልብስ ስፌትና የሽመና ሙያ እንደ ነበራት ሁሉ እርስዎስ ሌሎችን የሚያገለግሉበት ምን ዓይነት ሙያ አሎት?***

## ማክሰኞ ነሐሴ 21

## መስጠት - - ካለን ላይ ማካፈል

ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን ከተቀበለና ከተለወጠ በኋላ ወንጌልን ለአሕዛቡ ዓለም የማድረስ ተልዕኮ ወሰደ። እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው ስኬት ከአይሁድ ማንነት ወደ ክርስትና በመጡትና በአዳዲሶቹ አሕዛብ ተከታዮች መካከል ባለው ግንኙነት ዙሪያ ታላቅ ጥያቄ አስነሳ። በዚህ አንገብጋቢ ርዕሰ ነጥብ ላይ ውይይት አድርጎ ውስብስቦቹን ጥያቄዎች በአምላካዊው ምሪት ለመፍታት፤ የአይሁድና አሕዛብ ክርስቲያኖች ጉባኤ በየሩሳሌም ተጠራ። ጉባኤውም ሆነ በጉባኤው የተገኙ ውጤቶች በሐዋ. ምዕ. 15 ቀርበዋል።

ጳውሎስ ስለዚህ ጉባዔ ያዘጋጀው ሪፖርት በገላ. 2 የሚገኝ ሲሆን፤ ከየሩሳሌም ጉባኤ ከተቀበላቸው ትእዛዞች መሠረታዊ ከሆኑት መካከል ለቀጣይ የአሕዛብ አገልግሎቱ አንድ ሌላ አስፈላጊ ነጥብ ያክላል፡ “አጥብቀው ዐደራ ያሉን ድኾችን ማሰባችንን እንዳናቋርጥ ብቻ ነው፤ እኔም ይሄንኑ ለማድረግ ጉጉቴ ነበር” (ገላ. 2፡10)፡፡

ጳውሎስ በአጠቃላይ አገልግሎቱ በዚህ ነጥብ ላይ ትኩረት ማድረጉን ገፋበት (ሐዋ. 20፡35)፡፡ ጳውሎስ በየሩሳሌም ከነበረችው የቀደመች ቤተ ክርስቲያን በተመሳሳይ፤ ሁሉንም አማኞች ለማቀፍ በሚያስችል መልኩ የክርስትናው ማኅበረሰብ ራእይ እየተስፋፋ እንዲሄድ አደረገ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 8፡7-15፡፡ ጳውሎስ ወንጌልን በለጋስነት ከመስጠት ጋር የሚያስተሳስርበት መንገድ ምን ይመስላል?

---

---

አማኞች በልግስና እንዲሰጡና በአስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ይገኙ ለነበሩ አማኝ ወንድም እህቶቻቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማነሳሳት ጳውሎስ በተጨማሪ ሁለት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ጥቅም ላይ ሲያውል ይስተዋላል፡፡ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ጉዞአቸው እግዚአብሔር በልግስና ያወረደላቸውን መና ሐዋርያው የመስጠትና የማካፈል ምሳሌ አድርጎ ለመላው የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ያቀርባል (2ቆሮ. 8፡ 15)፡፡ በተጨማሪ “በተነ፤ ለድኾችም ሰጠ፤ ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል” (2ቆሮ. 9፡ 9) ሲል ከመዝሙረ ዳዊት 112፡9 ይጠቅሳል፡፡

ጳውሎስ አንባቢዎቹ በመስጠት ዙሪያ ልዩ ትኩረት ያደርጉ ዘንድ አጥብቆ አሳስቧቸዋል፡፡ አማኞች ከገቢያቸው ላይ የተወሰነውን ለይተው ካስቀመጡና እርሱ ወይም ቲቶ ጉባኤያቸውን በሚጎበኙበት ወቅት ይህ ስጦታ ተዘጋጅቶ ቢጠብቃቸው፤ በየሩሳሌም ለነበሩ አማኝ ችግርተኞች ለማድረስ ቀላል ይሆናል፡፡ ሐዋርያው በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ምሳሌ በመጥቀስ ሌሎቹን ለማነሳሳት ይሞክራል፡ “የክርስቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ስለ ታዘዛችሁና ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ስላሳያችሁት ልግስና ሰዎች ተፈትኖ ስላለፈው አገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ያከብራሉ” (2ቆሮ. 9፡13)፡፡

**በፊታችን ለሚቀርብ እያንዳንዱ የበጎ አድራጎት ጥያቄ ምላሽ መስጠት የማንችል ሲሆን፤ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን አንገብጋቢ ጉዳይ መለየት የምንችለው እንዴት ነው?**

## ረቡዕ ነሐሴ 22

# እንደ አምላካዊው ፈቃድ እየኖሩ ሌሎችን መውደድ - - ሐዋርያው ጳውሎስ

ጳውሎስ ለሮም ሰዎች የላከው ደብዳቤ ማለትም የሮሜ መጽሐፍ--በክርስቶስ ሞት የተገኘውን የደኅንነት በእምነት ኃይማኖታዊ አስተምህሮ በጥልቀት የገለጸበት ሥራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከዐሥራ አንደኛው ምዕራፍ በኋላ ግን የትኩረት አቅጣጫ ወይም የአጽንኦት ለውጥ ያደርጋል፡፡ በየሱስና በወንጌል ታሪክ እንደ ተገለጸው ሐዋርያው በአምላካዊው ጸጋና ፍቅር ላይ የተመሰረተ ህይወት ስለ መኖርና ስለ መዋደድ ተግባራዊ ምሪት ይሰጣል፡ "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅርኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው" (ሮሜ 12፡1)፡፡ በሌላ አነጋገር፤ እግዚአብሔር በየሱስ ካደረገልን ነገር አኳያ ልንኖር የሚገባው እንዲህ ነው--እያለን ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ ምዕ. 12፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስለ ፍቅርና ለሌሎች ጥንቃቄ ስለማድረግ--በተለይ በዕጦት ስለሚገኙ ችግርተኞች የቀረቡትን መመሪያዎች በሚገባ ለመመልከት ይሞክሩ።

---

---

ሮሜ 12--ጳውሎስ ይበልጥ ዘርዘር ያለ ትኩረት ለሚያደርግባቸውና አብዛኞቹ ሌሎች ደብዳቤዎቹ ለዳሰሳቸው ርዕሰ ነጥቦች እንደ ማጠቃለያ ሊያገለግል ይችላል። ሌሎችን ማገልገል፣ ማበረታታትና በለጋስነት መስጠትን ጨምሮ (ቁ. 3-8) የቤተ ክርስቲያን አካል ስለሆኑ ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችና ስጦታዎች ይናገራል፡፡ ሆኖም እነዚህ ነገሮች እንደው በደምሳሳው ሳይሆን በትጋት፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በፍቅር ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል (ቁ. 9-11)፡፡

ይህ ዓይነቱ ህይወት ምን ማለት እንደሆነ ጳውሎስ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ይናገራል። አማኞች በአስቸጋሪ ሁናቴና በስደት ለሚገኙ--ትዕግሥተኞች፣ በእጦት ያለውን የሚንከባከቡ፣ በተቻላቸው ከፉን በመልካም የሚያሸንፉ እንጂ በክፉ የማይሸነፉ የሰላም መልእክተኞች ይሆኑ ዘንድ ሐዋርያው ጥሪ ያቀርባል (ሮሜ 12፡20)፡፡

ይህ ምዕራፍ እንደ አዲስ ሰው የመኖርን ፍቺ እንዲሁም እግዚአብሔርን በግልና በጋራ ስለ ማገልገል በቂ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ የሱስ በመስቀል ላይ ሞቱና የዘላለማዊ ህይወት ተስፋ በመስጠት ለእነርሱ ስላደረገላቸው ነገሮች በምላሹ--ህይወታቸው፣

ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮችና ድርጊቶቻቸው ሊለወጡ እንደሚገባ ሐዋርያው ለአዳዲሶቹ የየሱስ ተከታዮች ነግሮአቸው ነበር፡፡ እነዚህ በጭቆና እና በጨካኝ ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያወቁ፤ በሮም መንግሥት ስር የሚኖሩ ሕዝቦች--ከቀድሞው በተለየ አኳኋን እንዲኖሩ ሐዋርያው ያስተምራቸዋል፡ “በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ” (ሮሜ 12፡2)፡፡

**ዛሬ እንደ የሱስ ተከታይነትዎ ከመኖርና ሌሎችን ከመውደድ ሊያስተጓጉልዎ የሚችሉና ሊታገሏቸው የሚገቡ ማኅበረሰባዊ አመለካከቶችና ልምዶች ምንድን ናቸው?**

## ሐሙስ ነሐሴ 23

## ያዕቆብ - - የየሱስ ወንድም

የቀደመው የክርስትና ወግ እንደሚጠቁመው ከሆነ የየሩሳሌም ጉባኤ ሊቀመንበር የነበረው የየሱስ ወንድም ያዕቆብ (ሐዋ. 15፣ ገላ. 1 እና 2) በየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያንም መሪ ነበር፡፡ ይህ ሐዋርያ በያዕቆብ መጽሐፍ ደራሲነትም እንዲሁ ይታወቃል፡፡

ልጅን በእርሱ መጠሪያ ስም መጥራት በዘመኑ እጅግ የተለመደ ነበር፡፡ ያዕቆብ ለሌሎች ችግር መፍትሔ ቅድሚያ የሚሰጥና ለተረሱ ወይም ዝቅ ተደርገው ይታዩ ለነበሩ አብልጦ የሚጠነቀቅ ብልህ መሪ ነበር፡፡ ይህ “የአዲስ ኪዳኑ መጽሐፈ ምሳሌ” በሚል የተገለጸና በእርሱ መጠሪያ ስም የሚታወቅ መጽሐፍ፤ የእግዚአብሔር ተከታዮች በቅድስና እና በጥበብ መመላለስ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

“ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ” (ያዕ. 1፡22) ብሎ ክርስቲያን መሪዎችን ለማስታወስ ጉጉ የነበረው የያዕቆብ መጽሐፍ ደራሲ፤ በእግዚአብሔር ዐይን ንጹህና ዘላቂ በሆነው፣ ፋይዳ ያለው ኃይማኖት ይኸውም--ማሕበረሰቡን ከብቦት የነበረውን የብልሹ አሠራር ተጽእኖ ተቋቁመው በችግር ውስጥና በጭቆና ለነበሩት ጥንቃቄ ማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ ነበር ያዕ. 1፡27)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ያዕ. 2፡1-9፣ 5፡1-5፡፡ ያዕቆብ ለሀብታሞች የነበረው አስተሳሰብ ከዘመኑ ማኅበረሰብ እሳቤ የተለየ የሆነው እንዴት ነበር? ሀብታሞች እና ድኾች በቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ እንዴት መታየት እንዳለባቸው አጽንኦት የሚሰጡት የእርሱ የተለዩ መመሪያዎች ምን ነበሩ?

ምስኪኖች በብርድና በረሃብ እየተሰቃዩ “በሰላም ሂዱ፣ አይብረዳችሁ፣ ጥገቡ” የተሰኘው መልካም ምኞት ሊያመጣ የሚችለው መጽናናት እጅግ አነስተኛ ነው--ሲል ያዕቆብ ይሞግታል፡፡ ለችግረኛው የሚበላ ወይም የሚለበስ መጽዋት መስጠት ከማንኛውም መልካም ምኞት በላቀ ለምስኪኑ ደኅ ያለንን ጭንቀት በተጨባጭ ገልጦ ያሳያል (ያዕ. 2፡14-16)፡፡ ያዕቆብ ይህን የእምነትና የሥራ መስተጋብር ምሳሌ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን የግንኙነት ዐውድ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም የሱስ ባልንጀራን እንደ ራስ ስለ መውደድ ያስተማረውን (ያዕ. 2፡8) ትምህርት እንዴት በየዕለቱ ህይወታችን መታዘዝ እንዳለብን በማሳየት ደግሞ አቅርቦታል፡፡ ይህ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሌሎች በምንሰጠው አገልግሎት በህይወታችን ገልጠን የምናሳየው ነገር፤ የእውነተኛ እምነት መገለጫ እንጂ ደኅንነት እናገኝበታለን ብለን የምናደርገው ነገር አይደለም፡፡

**ከድኽነት ይልቅ ሀብትን በደመነፍስ እንኳ ለመምረጥ የሚቀለን ለምንድን ነው?**

## አርብ ነሐሴ 24

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Read Ellen G. White, “Dorcas—Her Ministry and Its Influence,” pp. 66, 67, in Welfare Ministry; “A Liberal Church,” pp. 335–345, in The Acts of the Apostles; “This Is Pure Religion,” pp. 35–41, in Welfare Ministry.

“በሐዘን ውስጥ ላሉና ፈተና ለተጋረጠባቸው ነፍሳት ብቁ አገልግሎት የምትሰጥ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ሲል አዳኙ የከበረ ህይወቱን ሰጠ፡፡ አማኞች--ድኾች፣ በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያላለፉና የማይታወቁ ቢሆኑ እንኳ፤ ነገር ግን በክርስቶስ አማካይነት--በቤታቸው፣ በጎረቤታቸው፣ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በተለያዩ ርቀት ባላቸው ስፍራዎች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ዘላለማዊ ውጤት ሊያስከትሉ ይችላል፡፡”—Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 640.

“አማኞች የወንጌልን መልእክት በጨለማ ወዳሉት ለማድረስ ባደረጉት ያላሰለሰ በጎነት ለራሱ ቅድሚያ ያልሰጠው ለጋስነት የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሐሴት ጎዳና መራት፡፡ ደግነትና ርኅራኄአቸው የእግዚብሔርን ጸጋ በከንቱ አለመቀበላቸውን መመስከር ቻለ፡፡ እንዲህ ያለው ለጋስነት

በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ እንጂ ምን ሊያስገኝ ይችል ነበር? የአምላካዊው ታምራት ጸጋ አማኝ በሆኑም ሆነ ባልሆኑ ዐይኖች በጉልህ ይታይ ነበር፡፡”— Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 344.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.የቤተ ክርስቲያንዎ ማኅበረሰብ በአመዛኙ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፎች እንደተገለጸው ዓይነት መሆን የሚችለው እንዴት ነው? ቤተ ክርስቲያንን በዚህ አቅጣጫ ለማበረታታት የሚችለው አመራር በሥራ ላይ ሊያውላቸው የሚችሉ ቅደም ተከተሎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

2.ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዐሥራትና ስጦታ በተለያዩ የዓለም ክፍል እንዲከፋፈል በማድረግ አንዳንዶቹን በዚህ ሣምንት የተነጋገርንባቸውን መርኅዎች ጥቅም ላይ በማዋል በዓለማቀፍ ደረጃ እየሠራችበት ትገኛለች። ሀብትን በዚህ መልኩ በዓለማቀፍ ደረጃ የማከፋፈል ዘዴ መከተል ምን ዓይነት ጥቅሞች ያስገኛል?

3.ለምሳሌ በሮሜ 12 የቀረቡት ዓይነት የህይወት መመሪያዎች በህይወታችን በተግባር መገለጽ የሚችሉ ናቸው? በገሀዱ ዓለም ሥራ ላይ መዋል ይችሉ ይሆን? ወይስ ቆየት ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የመስታወት መስኮቶች ላይ የተሳሉ ፍጹም የሆኑ “ቅዱሳን” ምስል ዓይነት ስሜት ይሰጣሉ?

4.ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የሚያስተጋቡ ዓይነት ጠንከር ያሉ ቃላትና ማስጠንቀቂያዎች በያዕ. 5፡1-5 ቀርቦአል፡፡ እንዲህ ያለው ጠንካራ አገላለጽ ተገቢና አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

***ማጠቃለያ፡ በየሱስ ተልዕኮና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተበረታቱት ደቀ መዛሙርት እና የቀደሙት አማኞች የየሱስን መልእክትና ተልዕኮ በተቻላቸው መጠን በስፋት ማስተጋባት ጀመሩ። የየሱስን አስተምህሮና የብሉይ ኪዳንን መልእክቶች አጣምራ የያዘችው የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አባላት ያላቸው ለሌላቸው የሚያካፍሉበት አዲስ ዓይነት ማኅበረሰብ አቅፋ ይዛ ነበር። የቀደሙት የክርስትና እምነት መሪዎች በምሳሌነታቸውና በትምህርታቸው ለእነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች በጻፏቸው ደብዳቤዎች አማኞች በታማኝነት እንዲኖሩና እንዲያገለግሉ--በተለይም ችግርተኞችን! አጥብቀው አስገንዝበዋል።***

# 10ኛ ትምህርት

**ከነሐሴ 25-ጳጉሜ 1**

# ወንጌልን መኖር

ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** ሮሜ 8:20–23፣ ዮሐ. 3:16-17፣ ማቴ. 9:36፣ ኤፌ. 2:8–10፣ 1ዮሐ. 3:16-17፣ ራእ. 14:6, 7፡፡

***የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-*** - ***“በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን፡፡”*** (ኤፌ. 2፡8-10)፡፡

ስለ እግዚአብሔር ትእዛዞች፣ መመሪያዎች ወይም በአጠቃላይ እርሱ ከእኛ ስለሚፈልጋቸው ነገሮች ተነጋግረን ብዙም ሳንቆይ ሥራችን ለደኅንነታችን አስተዋጾ እንደሚኖረው ወይም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ እንደሚያስገኝልን በማሰብ ራሳችንን ለፈተና እያጋለጥን እንሰጣለን፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ እንደሚነግረን እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን የዳንነው በአምላካዊው ጸጋ ይኸውም በመስቀል ላይ ቤዛ ሆኖ በሞተልን በየሱስ ነው፡፡ ለመሆኑ በዚህ ላይ ምን መጨመር እንችላለን? “አንድ ሰው በሰብዓዊው ፍጡር ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ማንኛውንም መልካም፣ ቅዱስ፣ የከበረና ተወዳጅ የተባለ ነገር ሁሉ በአንድነት ሰብስቦ የሰውን ነፍስ ሊያድን ይችል እንደሆን ጉዳዩን በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ቢያቀርብ ሀሳቡ እንደ ክህደት ተቆጥሮ ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡”—Faith and Works, p. 24.

በመሆኑም በችግርና በእጦት ለሚገኙ ወንድም እህቶቻችን የምናደርገው የምኅረትና የርኅራኄ ተግባር በራሱ ሕግን የመጠበቅ አካል ተደርጎ መስተዋል የለበትም፡፡ በተቃራኒው በክርስትና ህይወታችን እየጎለመስን፣ የደኅንነትን ምስጢር እያስተዋልንና እያደነቅን በመጣን ቁጥር፤ በእግዚአብሔር ፍቅር እና እርሱ ለድኾችና ለተጨቆኑ ባለው መቆርቆር መሃል ያለው ትስስር--የፍቅሩ ተቀባዮች ወደ ሆንነው ወደ እኛ ይተላለፋል፡፡ በነጻ እንደ ተቀበልን ሁሉ በነጻ እንሰጣለን፡፡ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ወደደን መመልከት ስንችል እርሱ ሌሎችንም በምን ያህል ፍቅር እንደ ወደደና እኛም እነርሱን እንድንወድ ያቀረበልንን ጥሪ ለመረዳት ብዙም አንቸገርም፡፡

## እሑድ ነሐሴ 26

# “እግዚአብሔር... ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና”

“እግዚአብሔር... ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና” (ዮሐ. 3፡16)፡፡ ጥቅሱ የተወሰደው kosmos ከተሰኘ የግሪክ ቃል ሲሆን “የተቀናበረውን የፍጥረት ሥራ፣ አንድነት ያለውን አካል” የሚል ፍቺ አለው፡፡”—The SDA Bible Commentary, vol. 5, p. 929. ጥቅሱ ስለ ሰብዓዊው ፍጡር ደኅንነት የሚናገር ሲሆን፤ አምላካዊው የደኅንነት ዕቅድ አንደምታ ግን ለመላው የፍጥረት ሥራ ጭምር ነው፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ሮሜ 8፡20-23፡፡ በደኅንነት እቅድ እጅግ ሰፊ ስለሆኑት ጉዳዮች ይህ ምን ያስተምረናል?

---

---

በእርግጥ በአንድ በኩል ደኅንነት እያንዳንዳችን ከጌታ ጋር በግል ባለን ግንኙነት ላይ አጽንኦት ቢሰጥም ነገር ግን ጉዳዩ ከዚያም የላቀ አንደምታ አለው፡፡ መጽደቅ ኃጢአታችን ተረሳልን እንደ ማለት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ጌታ በየሱስ እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት አምላካዊውን ቤተሰብ የመፍጠሩ፣ ይቅር የመባላችንና የመዳናችን ማረጋገጫ ማግኘታችን እንዲሁም ከሌሎች ነገሮች ጎን ለጎን በመልካም ተግባሮቻችን ጭምር ለዓለም ምስክር መሆናችን ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 3፡16-17፡፡ ቁ. 17--በቁጥር 16 የቀረበውን ሀሳብ በስፋት እንድናስተውል አስተዋጾ የሚያደርገው እንዴት ነው?

---

---

እኛ ሌሎችን ከምንወደው በላቀ እግዚአብሔር ሰዎችን የመውደዱን እውነታ መቀበል እንችላለን፡፡ እኛ የሚወዱንን እንወዳለን፤ በዚህም በእጅጉ ደስተኞች ነን። በተጨማሪ እርሱ አምላካዊውን ፍቅር ለማካፈል የምንተጋላቸውን ወገኖችም መውደዱና እኛም ለዚህ እውነት እውቅና መስጠታችን ወደ እነርሱ ለመድረስ መበረታቻ ምክንያታችን ነው፡፡ ሆኖም ለእኛ ብዙም የማይመቹንን--እንደውም የምንፈራቸውን ሳይቀር እርሱ ይወዳል፡፡ እግዚአብሔር በየትኛውም ስፍራ የሚገኙትንም ሆነ በተለይ ልንወዳቸው የምንቸገርባቸውን ሳይቀር ይወዳል፡፡

ፍጥረት ይህ ተገልጦ ማየት የምንችልበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ያለማቋረጥ በዙሪያችን ያለውን ዓለም በማስረጃነት ያሳየናል፡ “ ‘እርሱ ፀሐዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኃጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል’ ” (ማቴ. 5፡45)፡፡ ህይወት ራሷ ከእግዚአብሔር የተቸረች ስጦታ ናት፡፡ አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ምላሽ ወይም የሚኖረው አመለካከት የቱንም ዓይነት ሊሆን ቢችልም፤ እያንዳንዱ ሰው የዚያ ስጦታ ተቀባይ ነው፡፡

**ሌሎችም በእግዚአብሔር የተፈጠሩና የተወደዱ መሆናቸውን በጥልቅ ማስተዋላችን በእነርሱ ላይ ያለንን አመለካከት የሚለውጠው እንዴት ነው?**

## ሰኞ ነሐሴ 27

# ርኅራኄና ንስሐ

ውሁድ ባህሪ ያላቸው የደህንነትና እልህ አስጨራሾቹ የታላቁ ተጋድሎ ታሪኮች የዓለማችንንም ሆነ የራሳችንን መሰረታዊ እውነታ በጥልቀት አስተውለንና አምነን እንድንቀበል ጥሪ የሚያደርጉልን ሲሆን፤ ይኸውም እኛም ሆንን ዓለማችን የወደቅን፣ የተበላሸንና ኃጢአተኞች የመሆናችንን ሐቅ ነው፡፡ ዓለማችን የተፈጠረችው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንድትወድቅ አልነበረም፡፡ እኛም የፈጠረንን አምላካዊ አምሳል ብንይዝም የብልሹው ዓለም አካል ነን፡፡ በእኛ ውስጥ ያለው ኃጢአት በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ ህመም፣ ጭቆና እና ብዝበዛ ካስከተለው ክፋት ጋር ተመሳሳይ ተፈጥሮ ይጋራል፡፡

ስለዚህ ከምንገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በዓለምም ሆነ ዙሪያችንን ባሉ ሰብዓዊ ወገኖች ላይ ጉዳት፣ ጉስቁልና፣ እጦትና ሐዘን መመልከት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ በዚህ ህይወት ላይ እየደረሰ ያለው ህመም እንዳይሰማን ሮቦቶች መሆን አለብን፡፡ በመዝሙረ ዳዊት የቀረቡ የልቅሶ ድምጾች፣ የኤርምያስ ሰቆቃና የሌሎችም ብሎም የየሱስ እንባና ርኅራኄ ለዓለምና ለክፋቷ የእንዲህ ዓይነቱን ምላሽ ተገቢነት ያሳያሉ--በተለይ በክፉው ተደጋጋሚ የጉዳት ገፈት ቀማሾች!

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 9:36፣ 14:14፣ ሉቃ. 19:41-42፣ ዮሐ. 11:35፡፡ በእነዚህ በቀረቡት በእያንዳንዱ ጥቅሶች የየሱስ ልብ አጥብቆ የተነካባቸው ትእይንቶች

የትኞቹ ነበሩ? በዙሪያችን ላሉ ህመምና ሥቃዮች የሚራራ ልብ ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?

---

---

እንዲሁም ኃጢአትና የክፋው ሀሳብ ከእኛ ተነጥሎ በባይተዋርነት የተቀመጠ ነገር ወይም የሌላው ውድቀት ውጤት አለመሆኑን አንዘንጋ፡ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" (1ዮሐ. 1፡8)፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት መረዳት ከሆነ ኃጢአት አሳዛኝ ክስተት የሆነው ገና መጀመሪያ የሆነ ሰው "ሕጎቹን" በመጣሱ ሳይሆን ነገር ግን ኃጢአት በእግዚአብሔርና በፍጡሮቹ መካከል የነበረውን ግንኙነት በመበጠሱ እና የእኛ ኃጢአት ሌሎችን በመጉዳቱ ነው። ምናልባት መጠኑ ሊያንስ ወይም ሊበዛ ቢችልም ክፋው ግን ያው ክፉ ነው፡፡

የዓለም የክፋት ተግባራት የሆኑት የኢፍትሐዊነት፣ የድኽነትና የጭቆና ሥረ መሰረቶች--ራስ ወዳድነት፣ ስስት፣ ርኩሰት፣ ጭፍን ጥላቻ እንዲሁም ስለ ሌላው ግድ አለማለት ናቸው፡፡ ይህን የክፋው ተግባር ለመቋቋም ተቀዳሚው ተግባር ኃጢአተኝነታችንን መናዘዝ እና የእግዚአብሔር ፍቅር ባለ መብት የሆነበትን ስፍራ ይኸውም ልባችንን እንዲወስድ መፍቀድ ይሆናል፡ "ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከአመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው" (1ዮሐ. 1፡9)፡፡

**እስቲ ወደ ራስዎ ይመልከቱ፡፡ እርስዎ በተለይ ሊቋቋሙት የሚገባ የትልቁ ችግር አካል የሆነው የክፉ ተግባር የትኛው ነው? ለዚህ ብቸኛውን መልስ ከወዴት ያገኛሉ? ሊሄዱ የሚገባውስ ብቸኛው ስፍራ?**

## ማክሰኞ ነሐሴ 28

## ጸጋ እና መልካም ሥራ

ጥቅሶቹን ያንብቡና ሀሳቡን በራስዎ ቃላት ለመጻፍ ይሞክሩ፡ ኤፌ. 2፡8-10፡፡ በጸጋ እና በመልካም ሥራ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን ይነግሩናል?

---

---

እኛ ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ እግዚአብሔርን እንድናመልክ እና ሰብዓዊውን ወገን እንድናገለግል መፈጠራችንን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ይህ ማንነት ኃጢአት

በሌለበት ሁኔታ ምን ሊመስል እንደሚችል በዐይነ ህሊናችን ብቻ ለማየት መሞከር እንችላለን፡፡

እኛ አሁን የምናውቀው በኃጢአት ምክንያት የፈረሰውንና የወደቀውን ዓለም ብቻ ነው፡፡ ስለ ዓለም ኃጢአት ሲባል በየሱስ መሥዋዕትነት የተገለጠውና በተግባር የታየው የእግዚአብሔር ጸጋ የይቅርታና የፈውስ ጎዳና ከፈተ፡፡ በእንዲህ ያለው የፈረሰ ህልውና ውስጥ ሆነንም እንኳ ህይወታችን በአመዛኙ አምላካዊውን አሠራር ሲከተል፤ በሌሎች ህይወት ላይ የደረሰውን ውድመትና ጉዳት ለመፈወስና ወደ ቀድሞ ሁኔታው ለመመለስ ከእርሱ ጋር አንድነት እንድንፈጥር ይጠቀምብናል (ኤፌ. 2፡ 10)፡፡ “በነፃ የተቀበሉ በነፃ ሊሰጡ የተገባ ነው፡፡ እርዳታ የሚሹ ጥሪዎች ከእያንዳንዱ አቅጣጫ እየመጡ ነው፡፡ ሰዎች ሰብዓዊ ወገኖቻቸውን በደስታ ያገለግሉ ዘንድ እነሆ እግዚአብሔር ጥሪ ያቀርባል፡፡”—Ellen G. White, The Ministry of Healing, p. 103.

ለመጽደቅ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለመቆም ብለን ደኻውን የመንከባከብ፣ የተጨቆኑትን ቀና የማድረግና የተራበውን የማብላት ሥራ አንሠራም፡፡ ይልቁንም በክርስቶስ ላይ ባለን እምነት የተነሳ ሁሌም ከእግዚአብሔር ጋር መቆምን እንሻለን፡፡ ምንምእንኳ ራሳችንንእንደ ኃጢአተኛናየኃጢአት ሰለባ ብንቆጥርም፤ በእግዚአብሔር የተወደድንና የተዋጀን ነን፡፡ በእርግጥ ዛሬም ከራስ ወዳድነትና ከስስት ጋር ግብግብ ላይ ብንሆንም፤ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠው ትሑቱ አምላካዊ ጸጋ ማንነታችንን የሚለውጥ አዲስ ህይወትና የተትረፈረፈ ፍቅር ይሰጠናል፡፡

ወደ መስቀሉ ቀና ብለን ስለ እኛ የተደረገውን ታላቅና ፍጹም መሥዋዕትነት ስንመለከት፤ በክርስቶስ በተደረገልን ነገር ላይ አንዳችም ነቁጥ ማከል እንደማንችል እንገነዘባለን፡፡ በእርግጥ በክርስቶስ ለተበረከተልን ነገር ምንም ዓይነት አጸፋዊ ምላሽ መስጠት የለብንም ማለት አይደለም፡፡ ምላሽ መስጠታችንማ የግድ ነው፡፡ ለእኛ ያሳየንን ያንን አቻ የማይገኝለት ፍቅር ለሌሎች ከማሳየት ውጪ ምን የተሻለ ምላሽ የምንሰጥበት መንገድ ይኖራል?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ዮሐ. 3፡16-17፡፡ ለመስቀሉ ልንሰጥ የሚገባውን ምለሽ አስመልክቶ ጥቅሶቹ በብርታት የያዙት ሀሳብ ምን ይመስላል?**

## ረቡዕ ነሐሴ 29

# በአንድ የምንጋራው ሰብዓዊነት

የሱስ በአገልግሎቱም ሆነ በአስተምህሮው ሁሉንም ሰብዓዊ ማንነት ላካተተው ሥር ነቀል አምላካዊ ጥሪ አጽንኦት ሰጥቶ ነበር፡፡ አጉል ስም የነበራት ሴት ብትሆን ወይም ቀረጥ ሰብሳቢ፣ በለምጽ የተመቱ ወይም ሳምራውያን፣ የሮም ሙቶ አለቆች ወይም የኃይማኖት መሪዎች ወይም ደግሞ ህጻናት--የእርሱን ትኩረት በቅንነት እስከ ሻቱ ድረስ ከልብ የመነጨውን ጥንቃቄና በጎ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በብርቱ የለውጥ ጎዳና ላይ በነበረችባቸው በእነዚያ ቀናት ይህ ስር ነቀል ለውጥ የአምላካዊው የደኅንነት ስጦታ አካል ሆኖ ተካትቶ ነበር፡፡

የቀደሙት አማኞች ቀስ በቀስ የወንጌልን ሁሉን አካታችነት እየተገነዘቡ በመጡ ቁጥር ሌሎች መልካሙን ሥራ ብቻ እንደ “ጥሩ” ነገር አክለው እንዲይዙ አላበረታቱም፡፡ ሐዋርያት በየሱስ ህይወት፣ አገልግሎትና ሞት በነበራቸው ተሞክሮ ይህ ወንጌልን የማስተዋላቸው--የልብ ትርታ ለመሆን በቃ፡፡ በጊዜው ይነሱ ከነበሩ አወዛጋቢ ነጥቦችና ጥያቄዎች ጋር ያደርጓቸው በነበሩ ትግሎች መጀመሪያ እንደ ጳውሎስና ጴጥሮስ ዓይነቶቹ መሪዎች--በግል (ሐዋ. 10፡9-20)፤ በመቀጠል እንደ ቤተ ክርስቲያን አካል በየሩሳሌም ጉባዔ (ሐዋ. 15)--ይህ መልካም የምሥራች ይዞ የመጣውን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ሁሉን አካታች አስገራሚ ለውጥ መገንዘብ ጀመሩ፡፡ እንዲሁም እርሱን ለመከተል የሚሹ እንዴት በህይወታቸው ሊተገብሩትና ሊኖሩት እንደሚገባም ተረዱ፡፡

የሚከተሉት ጥቅሶች ሰብዓዊ ማንታችን ስለሚጋራቸው ነገሮች ምን ያስተምሩናል? እያንዳንዱ ጽንሰ ሀሳብ በሌሎች ላይ በሚኖረን አመለካከት ዙሪያ ተጽእኖ ማሳደር የሚችለውስ እንዴት ነው?

ሚልክ. 2:10__________________________________________________

ሐዋ. 17:26__________________________________________________

ሮሜ 3:23__________________________________________________

ገላ. 3:28__________________________________________________

በገላ. 3፡28 የቀረበው ነጥብ የሱስ ስለ መልካሙ ሳምራዊ የተናገረው ታሪክ ሥነ መለኮታዊ ማጠቃለያ ሀሳብ ነው፡፡ ማንን የማገልገል ሞራላዊ ግዴታ ነው ያለብን እያልን ሙግት ከማንሳት ይልቅ ወጥተን ማገልገልና ምናልባትም ያገለግሉናል ብለን የማንጠብቃቸው ሊያገለግሉን እንደሚችሉም እንጠብቅ፡፡ የዓለማቀፉ ሰብዓዊ ቤተሰብ የጋራ ባህሪ--በወንጌል፣ ወደ አንድነት በሚጠራን በአዳኙ አምላካዊ ፍቅርና በእርሱ አማካይነት በአንድ በተሳሰሩ ተራ ሰዎች ከፍ ባለ ደረጃ እውን ሆኖ መታየት ችሎአል፡ "አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነፃ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና" (1ቆሮ. 12፡13)፡፡

## ሐሙስ ነሐሴ 30

## ዘላለማዊው ወንጌል

ወንጌል "ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወገን" (ራእ. 14፡6) እንዲሰበክ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣው ግብዣና ተማጽኖ የመላው ክርስትና ታሪክ አካል ሆኖ ኖሮአል፡፡ የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ስለ የሱስ የቀረቡትን መልካም የምሥራቾች ከመጨረሻው ዘመን ትዕይንት ጋር አጣምሮ በአዲስ ዓይነት እወጃ ይገልጻቸዋል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡6-7፡፡ በቁ. 7 በግልጽ የቀረበው የመልአኩ መልእክት ታክሎበት--በተለይ በዮሐ. 3፡16 ከቀረበው መልእክት አኳያ የተለመደው የወንጌል አረዳድ ምን ይመስላል?

---

---

እግዚአብሔር ስለ ክፉው፣ ስለ ድኽነትና ጭቆና አብዝቶ ግድ እንደሚለው እስካሁን በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ግንዛቤ ያገኘንባቸውን ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ራእ. 14፡7 በአንድነት ያቀርብልናል፡፡

ፍርድ፡ በዘመናት በጭቆና ገፈት ውስጥ ያለፉ ሰብዓዊ ወገኖች ትክክለኛውን ፍርድ እንዲያገኙና ፍትሕ እንዲሰፍን ተደጋጋሚ ተማጽኖ ሲቀርብ ኖሮአል፡፡ እንደ እድል ሆኖ እግዚአብሔር በሥቃይ ውስጥ ያሉትን የልቅሶ ድምጾች የሚሰማ አምላክ አድርጎ መጽሐፍ ቅዱስ ይስልልናል፡፡ በመዝሙር መጽሐፍ በተደጋጋሚ እንደተገለጠው ለምሳሌ በደል የደረሰባቸው ፍትሕን እንደ መልካም የምሥራች ይመለከቱታል፡፡

አምልኮ፡ የዕብራውያን ነቢያት የአምልኮን ርዕሰ ጉዳዮች ከመልካም ሥራ ጋር እያስተሳሰሩ በተደጋጋሚ በጽሑፎቻቸው አቅርበዋል--በተለይ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብለው የሚጠሩ በአምልኮአቸው ይፈጽሟቸው የነበሩትንና በዚያው የጸኑባቸውን አጉል ድርጊቶች እያወዳደሩ አቅርበዋል፡፡ ለምሳሌ በኢሳ. 58 እግዚአብሔር አብልጦ የሚሻው አምልኮ ለድኾችና ለችግረኞች በጎነት ማሳየትና ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ መሆኑ በግልጽ ቀርቦአል (ኢሳ. 58፡6-7)፡፡

ፍጥረት፡ ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ከእግዚአብሔር የፍትሕ ጥሪ መሰረታዊ ባህሪያት አንዱ የሰው ልጅ በአንድ የሚጋራው ሰብዓዊ ቤተሰብነት ነው፡፡ እኛ ሁላችን በእርሱ አምሳል የተፈጠርን፣ የተወደድንና በፊቱ የከበረ ዋጋ ያለን እንደ መሆናችን ማንም በኢፍትሐዊው ስግብግብነት ሌላውን ሊበዘበዝ ወይም ሊጨቁን አይገባም፡፡ ይህ ሰፊና እጅግ ብዙ ዐውዶችን ያካተተ የፍጻሜው ጊዜ የወንጌል እወጃ የወደቀው ሰብዓዊ ዘር መዳን፣ መቤዠትና ወደ ቀድሞ ንጽህና መመለስ እንዲያገኝ የቀረበለት አምላካዊ ጥሪ ነው፡፡ የእውነተኛና ሐሰተኛ አምልኮ ጉዳዮች ገንነው በሚወጡባቸውና የክፉው ተግባር አስጨናቂ በሚሆንበት ስደት መሃል (ራእ. 14፡ 8-12) እግዚአብሔር ለእውነት፣ ለአምላካዊው ትእዛዛትና ለየሱስ እምነት የሚቆሙ ሕዝቦች ይኖሩታል፡፡

***በችግር ያሉ ሰብዓዊ ወገኖችን እያገለገልን የሦስቱን መላእክት መልእክት ተስፋዎችና ማስጠንቀቂያዎች ማካፈል የምንችልበትን መንገድ ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?***

## አርብ ጳግሜ 1

ተጨማሪ ሀሳብ፡ *Read Ellen G. White, " 'God With Us,' " pp. 19–26, The Desire of Ages; "Saved to Serve," pp. 95–107, in The Ministry of Healing.*

"እግዚአብሔር ምድር የእርሱ የወይን ቦታ መሆኗን ይናገራል፡፡ ምንም እንኳ ያላግባብ ዙፋኑን በያዘው እጅ ብትወድቅም እርሷ ግን የእግዚአብሔር ናት፡፡ በመፍጠርም ሆነ በመዋጀት እነሆ የእርሱ ናት፡፡ ክርስቶስ ስለ ዓለም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ

ሰጥቶአል--‘እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና’ (ዮሐ. 3፡16)፡፡ በዚያ በአንዱ ስጦታ ሁሉም ሰው ተካፋይ ሆነ፡፡ መላው ዓለም በየዕለቱ ከላይ ከአርያም የሚላከውን በረከት ይቀበላል፡፡ እያንዳንዱን የዝናብ ጠብታም ሆነ የብርሃን ጸዳል ለእኛ ለምስጋና ቢሶቹ ሰብዓዊ ዝርያዎች ይሰዳል፡፡ እያንዳንዱ ለምለም ቅጠል፣ አበባና ፍራፍሬ የእግዚአብሔርን ረጅም ትዕግሥትና ታላቅ ፍቅር ይመሰክራል፡፡”—Ellen G. White, Christ’s Object Lessons, pp. 301, 302.

“በክርስቶስ አይሁድ ወይም ግሪክ ወይም ደግሞ ባሪያና ነጻ ሰው የሚባል የለም፡፡ ሁሉም በከበረ ደሙ ወደ እርሱ መቅረብ ስለቻሉ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናቸው (ገላ. 3፡28፣ ኤፌ. 2፡13)፡፡

“በሰዎች መካከል የቱንም ዓይነት የኃይማኖት ልዩነት ቢኖርም የሰብዓዊው ወገን የድረሱልኝ ድምጽ መሰማቱና ምላሽ ማግኘቱ የግድ ነው. . .

“የእኛ ርኅሩኅ ቃላትና እርዳታ የሚያሻቸው አያሌ ድኾችና ፈተናቸው የበዛ ነፍሳት በዙሪያችን አሉ፡፡ ስሜታቸውን ልንጋራና የእርዳታ እጆቻችንን ልንዘረጋላቸው የሚገቡ ባላቸውን በሞት የተነጠቁ ወይም ያለ ባል አለኝታ አሰቃቂ ኑሮ የሚገፉ ባልቴቶች አሉ፡፡ ክርስቶስ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህጻናትን እንደ እግዚአብሔር አደራ ተቀብለው ያሳድጉ ዘንድ ተከታዮቹን አዞአል፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ አዘውትሮ ችላ ሲባል ይታያል፡፡ ምናልባት እነዚህ ህጻናት ባብዛኛው የተጎሳቆሉ፣ የታረዙና ብዙዎች የሚጠየፏቸው ዓይነት ሊሆኑ ቢችሉም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ንብረቶች ናቸው፡፡ በዋጋ የተገዙና በእርሱ ዐይን የከበሩ ናቸው፡፡ የታላቁ አምላካዊ ቤተሰብ አባላት እንደ መሆናቸው መጋቢ ክርስቲያኖች ኃላፊነት አለባቸው፡፡”—Ellen G. White, Christ’s Object Lessons, pp. 386, 387.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.መልካም ሥራ ለመሥራትና ሌሎችን ለመርዳት ካለን መሻት አኳያ-- ሥራችን የተሻልን ሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት ይበልጥ ሞገስ እንደሚሆነን በማሰብ ሊመጣ የሚችልን ፈተና እንዴት መቋቋም እንችላለን?

2.የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ማኅበረሰብ ልዩነት የማያደርግ በክርስቶስ አንድ የሆነ ምዕመን ነው? አብልጦ ወደዚህ አቅጣጫ መምጣት የሚቻለው እንዴት ነው? ቤተ ክርስቲያንዎ ምን ያህል ሌሎችን አካታች ነው?

3.በችግር ያሉትን እየረዳንና እግረ መንገዳችንን የወንጌልን እውነት እያካፈልን ትክክለኛውን ሚዛን ጠብቀን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው? እነዚህን ሁለት ነገሮች በተጓዳኝ ማድረግ የምንማረው እንዴት ነው? ሁለቱንም ጎን ለጎን ማስኬድ ሁሌም የተሻለ የሆነው ለምንድን ነው?

*ማጠቃለያ፡በደኅንነት እቅድ እንዲሁም በየሱስ መሥዋዕትነትና ህይወት የተገለጸው የእግዚአብሔር ፍቅር--ይቅርታ፣ ህይወትና ተስፋ ይሰጠናል። እንደ ጸጋው ተቀባይነታችን ይህን ለሌሎች ለማካፈል የምንመኘው ለመዳን ብለን ሳይሆን የተፈጠርነውና ዳግም የተወለድነው ይህንን ለማድረግ በመሆኑ ነው። እንዲሁም ወንጌል የግንኙነትን ዐውድ በመቀየር ወደ አገልግሎት ይመራል--በተለይም እርዳታ ወደ ሚፈልጉት።*

# 11ኛ ትምህርት

ከጳግሜ 2 - መስከረም 2

# በዳግም ምጽአቱ ተስፋ መኖር

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 15:1፣ 7:1–3፣ 14:9-10፣ 16:1–12፣ 17:1፣ ዳን. 5፣ ራእ. 16:16፣ 2ተሰ. 2:9–12፡፡

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-““ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ፡፡ ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡58)።**

የእግዚአብሔርን መንግሥት ዛሬ ልንወርሰው የምንችል ተጨባጭ እውነታ አድርጎ የሱስ አስታውቆናል፡፡ ይህንኑ መልእክት እያበሰሩ፣ ወንጌልን እየሰበኩና ሌሎችን እያገለገሉ መንግሥቱን ያውጁ ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ላከ፡፡ ያም ማለት በነጻ አንደ ተቀበሉ በነጻ ይሰጡ ነበር (ማቴ. 10፡5-8)፡፡

የሱስ የእርሱ መንግሥት ከተለመደው የተለየ ስለ መሆኑ “የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም አይደለም” በማለት በግልጽ ተናግሮአል (ዮሐ. 18፡36)--በሙላት ሊመጣ ያለ እንጂ! ሥጋ በመልበሱ፣ በአገልግሎቱ፣ በሞቱና በትንሣኤው እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት ተቋቋመ፡፡ ነገር ግን የእርሱ መንግሥት የዚህን ዓለም መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የሚተካበትንና የእግዚአብሔር ንግሥና ፍጹም ሆኖ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የሚያስተጋባበትን ጊዜ አሻግሮ ይመለከታል፡፡

አድቬንቲስት ወይም የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚጠባበቁ የተሰኘው ስያሜ--ተስፋ የሚያደርጉ ሕዝቦች የሚል ፍቺ አለው፡፡ በእርግጥ ይህ ተስፋ ወደፊት የሚመጣውን አዲስ ዓለም ብቻ ያማከለ አይደለም፡፡ ተስፋ የወደፊቱን አሻግሮ እንደሚመለከት ሁሉ የአሁን ሁኔታንም ይቀይራል፡፡ በዚህ ተስፋ ዛሬን እየኖርን የወደፊቱንም እንጠባበቃለን፡፡ ዓለም አንድ ቀን ምን ሊሆን እንደሚችል ተስፋ ከምናደርገው ጋር የተጣጣመ ለውጥ ለማምጣት አሁን መሥራት እንጀምራለን፡፡

# እሁድ ጳግሜ 3

## “ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ?”

ብዛት ባላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የአምላካዊውን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቁ ከእግዚአብሔር ሕዝቦች የቀረቡ ተደጋጋሚ ጥሪዎች አሉ--በተለይ በባርነት፣ በግዞት፣ በጭቆና፣ በድኽነት ወይም በሌሎች ኢፍትሐዊ ወይም አሳዛኝ ሁኔታዎች ውስጥ ከነበሩ ህዝቦች፡፡ በግብፅ ባርነት እና በባቢሎን ግዞት ስር ወድቀው የነበሩ እስራኤላውያንን ጨምሮ ሌሎች አያሌ ወገኖች እግዚአብሔር ሥቃያቸውን እንዲሰማ፣ እንዲመለከትና የተበላሸውን እንዲያቃና የጩኸት ድምጾቻቸውን አሰምተዋል፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝቦቹን ለማዳንና ወደ ቀድሞው የተሻለ ሁኔታ ለመመለስ፤ እንደውም አንዳንዴ ጨቋኞቻቸውንና ጠላቶቻቸውን እስከ መበቀል የደረሰባቸውን አጋጣሚዎች መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ ያስነብበናል፡፡

ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እነዚህ የመታደግ ሥራዎች ለአጭር ጊዜ ብቻ ዕድሜ ያላቸው እንደመሆናቸው፤ ነቢያት እግዚአብሔር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የክፉው ዘመን አክትሞ የተገፉትን ከፍ ከፍ የሚያደርግበትን ጊዜ አሻግረው መመልከታቸውን ቀጥለዋል፡፡ በተጨማሪ እነዚህ ነቢያት “ጌታ ሆይ እስከ መቼ ነው?” ብለው ማንባታቸውንም አላቆሙም፡፡ ለምሳሌ የእግዚአብሔር መልአክ ስለ እስራኤላውያን የግዞት ዘመን እንዲህ ብሎ ጠይቆአል “እግዚአብሔር ጸባኦት ሆይ... የማትምራቸው እስከ መቼ ነው” (ዘካ. 1፡12)፡፡

መዝሙረ ዳዊት ኃጥአን በግልጽ እየበለጸጉና የመልካም ዕድል ባለቤት እየሆኑ ጻድቃን ግን የጉዳት፣ የብዝበዛና የድኽነት ሰለባ መሆናቸውን እያነሳ ብርቱ የሰቆቃ ድምጽ ያሰማል፡፡ እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ በተደጋጋሚ ጥሪውን እያቀረበና ምድር በእግዚአብሔር በተፈጠረች ጊዜ ዛሬ ያላትን ሁኔታ እንዳልያዘች ወይም እንድትይዝ አምላካዊው ፈቃድ እንዳልነበር እየገለጸ “ጌታ ሆይ እስከ መቼ?” ሲል እርሱም የነቢያቱንና የተጨቆኑትን የልቅሶ ድምጽ ያሰማል (መዝ. 94፡3-7)፡፡

ለሰዎች ሁሉ ፍትሕ የሚመኝ የፍትሕ አምላክ በሚመለክበት እምነት ውስጥ ኢፍትሐዊነትን ተቀብሎ መኖር ይበልጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዓለም በሰፈነው ክፉው ላይ ሁሌም ቢሆን ትዕግሥት አይኖራቸውም፡፡ ደግሞም ብዙም ሳይቆይ ገቢራዊ ሊሆን የሚችለው አምላካዊ ፍርድ--ሌላው ትዕግሥት የለሽ የሚያደርጋቸው ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህ “እግዚአብሔር ሆይ፤ ለእርዳታ እየተጣራሁ አንተ የማትሰማው እስከ መቼ ነው? ‘ግፍ በዛ’ ብዬ እየጮኽሁ፣ አንተ

የማታድነው እስከ መቼ ነው?" (ዕንባ. 1፡2) የሚሉ ጥብቅ ጥያቄዎችን አልፎ አልፎ ነቢያት ይጠይቃሉ፡፡

ፍጥረት ራሱ የሚቃትትበትና እግዚአብሔር እንዲታደገው ተማጽኖ የሚያቀርብበት ተመሳሳይ የልቅሶ ድምጽ በአዲስ ኪዳን ቀርቦአል (ሮሜ 8፡19-22)፡፡ በራእ. 6፡ 10 "ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ?" በሚል የቀረበው የልቅሶ ድምጽ በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት የተነሳ ሰማዕት ስለ ሆኑት ቅዱሳን የቀረበ ነው፡፡ ሆኖም ስለ ተጨቆኑና ስለ ተሰደዱ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነት ከሚማጸን የሰቆቃ ድምጽ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 18፡1-8፡፡ ሕዝቦቹ እግዚአብሔር እንዲደርስላቸው በተደጋጋሚ ያቀርቡ ለነበረው ልቅሶ እና ጸሎት አምላካዊ ምላሽ አስመልክቶ የሱስ ምን እያለ ነው? ይህ ሁኔታ እምነት አስፈላጊ ከመሆኑ ጋር እንዴት ይተሳሰራል?**

## ሰኞ ጳግሜ 4

# የሆነ ዓይነት ተስፋ

ኃይማኖት ዛሬ በዚህ ምድር አማኞች የሚኖሩትን ህይወት ችላ ብለው ከህይወት በኋላ ወዳለ የተሻለ የሚመስል ህይወት የመውሰድ አዝማሚያ አለው የሚል ትችት በተደጋጋሚ ይሰነዘራል፡፡ የሰዎችን ትኩረት ወደ ሌላ ዓይነት ግዛት የሚወስደው የአማኙ የመናኝ ዓይነት የተቀደሰ ህይወት፤ ከምድራዊው ነገርም ሆነ ከማኅበረሰቡ ተጠቃሚ የሚያደርገውን ምላሽ በቅጡ እንዳይሰጥ መንስኤ ይሆናል--የሚል ነው ትችቱ፡፡ አልፎ አልፎ አማኞች ራሳቸውን ለእንዲህ ያለው ትችት ክፍት ሲያደርጉ ሌላ ጊዜ ደግሞ እያለሙ፣ እየሰበኩና እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት እየተለማመዱ ኖረዋል፡፡

የሱስ ዳግም ተገልጦ ሁሉም ነገር ትክክለኛ ገጽታውን እስኪይዝ ደኻውና የተጨቆነው በዚህ ምድር የገጠመውን አሳዛኝ ዕጣ ፈንታ ተቀብሎ እንዲኖር የሚነግሩ በኃላፊነት የተቀመጡ አስደንጋጭ ምሳሌዎች አሉ፡፡

ዓለማችን መውደቋ፣ መፍረሷና አሳዛኝ ስፍራ መሆኗ እርግጥ ከመሆኑ አኳያ እግዚአብሔር ኢፍትሐዊነትን፣ ህመምንና ሐዘንን ወደ ፍጻሜ አምጥቶ የዛሬውን ምስቅልቅል በታላቅ ክብር በተሞላና ጻድቅ መንግሥት ተክቶ የጠፋውንና የተመሰቃቀለውን ወደ ቀድሞው ንጽህና እንዲመልሰው መናፈቅ በራሱ ስህተት የለውም፡፡ ለነገሩ ያ አለኝታ ባይኖረን ኖሮ እንደው ያለ ተስፋ በቀረን ነበር፡፡

የሱስ ስለ ምድር መጨረሻ የተናገረበትን ስብከት (ማቴ. 24 እና 25) የመጀመሪያ ክፍል አጋማሽ ያዋለው በዓለም ላይ ከሚከሰት መከራ ስለ ማምለጥ አስፈላጊነት በመዘርዘር ነው፡፡ እንደውም በቀጥታ ወደ ዋናው ሀሳብ በመግባት "'ቀኖቹ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ ነበር'" (ማቴ. 24፡22) ይላል፡፡ ሆኖም ይህ ስለ አምላካዊው ተስፋ ምንነት የሚሰጠው ማብራሪያ የመግቢያ ክፍል ነው፡፡ የወደፊቱ የክርስቲያኖች ተስፋ "ማምለጥ" በሚለው ቃል ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርግ ወይም ተቀዳሚውን ስፍራ እንዲወስድ ማድረግ፤ የሱስ ያስተማራቸውን አንዳንድ ጥልቀት ያላቸውን ነጥቦች ማጉደል ይሆናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ ማቴ. ምዕ. 24 እና 25፡፡ ከየሱስ የተራራው ስብከት ንባብዎ በእጅጉ አስፈላጊ ያሏቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? ዳግም ምጽአቱን እየተጠባበቅን እንዴት መኖር እንዳለብን አስመልክቶ የሱስ የሰጣቸውን መመሪያዎች እንዴት ጠቅለል አድርገው ያቀርቧቸዋል?

---

---

ስለ ወደፊቱ የሚኖረን እምነት ለዛሬው አኗኗራችን ጠቃሚ አንደምታ አለው፡፡ እግዚአብሔር ለዓለማችን የወደፊት ሁናቴ ባለው አስተሳሰብ ላይ የሚኖር ጤነኛ መተማመን፤ ጥብቅ ለሆነው ቁርጠኝነት ለውጥ የሚያመጣ፣ ለከበረውና ጥልቅ ትርጉም ላለው ህይወት የብርሃን ብልጭታ የሚፈነጥቅና በሌሎች ላይ ልዩነት የሚፈጥር ሊሆን ይገባል፡፡

**የየሱስ ዳግም ምጽአት ተስፋና ኪዳን በተለይ በችግር ውስጥ ያሉትን ከመርዳት አኳያ በዛሬው አኗኗራችን ላይ ተጽእኖ ማምጣት የሚችለው እንዴት ነው?**

## ማክሰኞ ጳግሜ 5

# የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ

ክርስቲያኖች በየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ያላቸው ተስፋ ብሩህ የሆነውን መጻኢ ነገር አሻግሮ በማየት ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ የቀደሙት ክርስቲያኖች የሱስ በአካል ወደ ሰማይ ሲያርግ መመልከታቸው ስለ ዳግም ምጽአቱ ተጨባጭ ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርት ምስክር የሆኑበትን--ሞትን አሸንፎ እስከ ተነሳ ድረስ ኃጢአትንና ውጤቱን አስወግዶ ዓላማውን እስከ መጨረሻው ሊያሳካና ምድርን አዲስ ሊያደርግ እነሆ በእርግጠኝነት ይመጣል (1ቆሮ. 15፡22-23)፡፡

ትንሣኤ ለሐዋርያው ጳውሎስ በቅርብ የሚገለጠው ተስፋ ቁልፍ ነገር ነበር፡፡ እርሱ የስብከቱን ሁሉ ተአማኒነት በዚህ ከሁሉ የላቀ የየሱስ ታሪክ ታምራት ላይ ለማዋል ዝግጁ ነበር፡ "ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ነው" (1ቆሮ. 15፡17)። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አሰብ ያድርጉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 15፡12-19፡፡ የትንሣኤው እውነት ለዳግም ምጽአቱ ወሳኝ ስለ መሆኑ አማኝ ላልሆነ ሰው እንዴት ይገልጹታል?

___

___

___

የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ለየሱስ ትንሣኤ ምስክር መሆን ህይወታቸው እንዲለወጥ አደረገ፡፡ ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲያውጁ ተልከው (ማቴ. 10፡5-8) የነበረ ቢሆንም፤ ነገር ግን የየሱስ ሞት ወኔያቸውን ሰልቦ ተስፋቸውንም አጨልሞ ነበር፡፡ ከሞት በተነሳው የሱስ (ማቴ. 28፡18-20) እና በልዩ ሁኔታ በወረደው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል (ሐዋ. 2፡1-4) እንዲያከናውኑ የተሰጣቸው ቀጣይ ተልዕኮ ዓለምን መለወጥ በሚያስችል ጎዳና ላይ አስቀምጦ የሱስ መስርቶት በነበረው መንግሥት ላይ አጸናቸው፡፡

ከሞት ኃይልና ፍርሃት ነጻ የሆኑት የቀደሙት አማኞች በየሱስ ስም በብርታት እየተመላለሱ ቃሉን ያካፍሉ ነበር (1ቆሮ. 15፡30-31)፡፡ ሞት የሚያስከትለው ክፋው--የሥቃይ፣ የፍትሕ መጓደል፣ የድኽነትና የተለያየ ዓይነት ጭቆና መንስዔም ነው። ሆኖም በየሱስ እና እርሱ በሞት ላይ ባለው አሸናፊነት የተነሳ ይህ ሁሉ አንድ ቀን ያከትማል፡፡ "የሚደመሰሰውም የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው" (1ቆሮ. 15፡26)፡፡

**"ዛሬ የትኛውንም ሰው ብናግዝና ብንረዳ ውሎ አድሮ አንድ ቀን ሞት አይቀርም፡፡ ሌሎች በየሱስ ሞት እና ትንሣኤ ውስጥ የሚገኘውን ተስፋ እንዲያውቁ መርዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ከዚህ ከባድ እውነት ምን እንማራለን?**

## ረቡዕ ጳግሜ 6

# የፍርድ ተስፋ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መክ. 8፡14፡፡ በዚህ ስፍራ የተጻፈውን ጽኑ እና ብርቱ እውነታ በምን ዓይነት መንገድ ይመለከቱታል?

---

---

ሰብዓዊውን ሥቃይ፣ ጭቆና እና አሳዛኝ ክስተት በራሱ ተቋቁሞ መዝለቅ እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም፤ በማናለብኝ የሚፈጸም አካላዊ ጉዳት ወይም ስድብ ደግሞ ጉዳቱ ይበልጥ የከፋ ነው፡፡ በሰብዓዊው ወገን ላይ ሊደርስ የሚችል ቅጥ ያጣ፣ ትርጉም የለሽ ሐዘን ከቀደመው ቀንበር በከፋ ለመቋቋም ከባድ ነው፡፡ ተግባሩ በመዝገብ መስፈር ያልቻለ ወይም በመጨረሻ ፍትሐዊ ብይን የማያገኝ ዓለም ድምዳሜው ጨካኝና ትርጉም ዐልባ ነው፡፡ የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዝግመተ ለውጥ አራማጅ ጸሐፊዎች እነርሱ ያመኑበት ሰብዓዊ ሁኔታ "ዘበት" እንደሆነ በማውሳት ቢያላዝኑ ብዙም አይደንቅም፡፡ ዓለማችን የፍትሕ ተስፋ ከሌላት፣ አንድ ቀን የፍርድ ጸሐይ የማይወጣላትና ነገሮች እንደተመሰቃቀሉ የሚቀሩ ከሆነ፤ በእርግጥም ትርጉም ዐልባ ዘበት ናት፡፡

በመክ. 8፡14 የቀረበው የልቅሶ ድምጽ የታሪኩ መጨረሻ አለመሆኑን ልብ ይሏል። ሰለሞን የተቃውሞ ሀሳብ ካነሳ በኋላ በመጨረሻ ድንገት ይመለሳል፡፡ በእርግጥ ሰለሞን ስለ ከንቱነት ከጠቃቀሳቸው የሰቆቃ ቃላት መሃል *እግዚአብሔር ፍርዱን ስለሚሰጥ ማንኛውም ነገር ትርጉም የለሽ አይደለም፤ በመሆኑም አሁን ማንኛውም ነገርም ሆነ እያንዳንዱ ሰው ትርጉም አለው* የሚል ዐውድ እናገኛለን፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መክ. 12፡13-14፡፡ እያንዳንዱ የምናደርገው ነገር ምን ያህል አጽንኦት እንደሚሰጠው አስመልክቶ ይህ ምን ይነግረናል?

---

---

የፍርድ ተስፋ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ባህሪ፣ ስለ ህይወትና ስለምንኖርባት ዓለም ከሚኖረው እምነት ይመነጫል፡፡ እኛ እየኖርን ያለነው እግዚአብሔር በሚወዳትና በፈጠራት ምድር ውስጥ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አጽንኦት ሰጥቶ ይነግረናል፡፡ ሆኖም ይህች ምድር በተሳሳተ አቅጣጫ መንገዷን ተከትሎ እግዚአብሔር በልጁ

በየሱስ ህይወትና ሞት እነሆ ዳግም ሊፈጥራት እየሠራ ይገኛል፡፡ አምላካዊው ፍርድ ምድራችንን ዳግም ወደ ቀናው ጎዳና የሚመልስበት ቁልፍ ክፍል ነው፡፡ ለተገፉ፣ የጭካኔ ተግባር ለተፈጸመባቸው፣ ለተጨቆኑና ለተበዘበዙ ሁሉ የፍርድ ተስፋ በእርግጥም መልካም የምሥራች ነው፡፡

***አሁን አጥብቀን የምንናፍቀው ፍትሕ በመጨረሻ አንድ ቀን ልንገምት በማንችለው መንገድ መምጣቱ ለእርስዎ ምን ዓይነት ትርጉም አለው? ከዚህ የተስፋ ቃል--ተስፋ መጨበጥ የምንችለው እንዴት ነው?***

## ሐሙስ መስከረም 1

## ከዚህ በኋላ እንባ ወይም ህመም አይኖርም

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 21፡1-5፣ 22፡1-5፡፡ በጥቅሶቹ የተገለጠው ህይወት ምን ሊመስል እንደሚችል በዐይነ ህሊናዎ ለመመልከት ይሞክሩ፡፡ ህይወትን ከኃጢአት፣ ከሞት፣ ከህመምና ከዕንባ ውጪ ለማሰብ የሚከብደው ለምንድን ነው?

---

---

መጽሐፍ ቅዱስ ከኃጢአት በኋላ ስላለው ህይወታችን የሚሰጠው መግለጫ አስገራሚና በክብር የተሞላ ከመሆኑ አኳያ የሚጠብቀንን ነገር ፍንትው አድርጎ ማቅረቡ ብዙም የሚደንቅ አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በእነዚህ ጥቅሶች የቀረቡት መግለጫዎች ራሳቸው የሚዳስሱት በዚያ ያሉትን ሳይሆን የሌሉትን ነው፡፡ እኛ የምናውቀው ይህን ዓለም ብቻ እንደ መሆኑ፤ ህይወትን ከህመም፣ ከሥቃይ፣ ከሞትና ፍርሀት፣ ከኢፍትሐዊነትና ድኽነት ውጪ ለማሰብ ይከብደናል፡፡

ጥቅሱ የሚናገረው ከዚህ በኋላ እነዚህ ነገሮች በዚያ ስፍራ አለመኖራቸውን ብቻ ሳይሆን ግላዊ መነካትንም በማከል "እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል" ይላል (ራእ. 21፡4)፡፡ በዘመናት በሥቃይ ውስጥ ስላለፉት ምስኪኖች--የእግዚአብሔር ርኅራኄ በዚህ አንድ ዐርፍተ ነገር ከፍ ወዳለ ደረጃ ተሸጋግሮ እንመለከታለን፡፡ እርሱ ለሥቃያቸው ፍጻሜ ማምጣት ብቻ ሳይሆን ዕንባቸውንም ያብሳል፡፡

ዓለም በኃጢአት ህይወት፣ በኢፍትሐዊነትና አሳዛኝ ክስተቶች የተጎሳቆለና የተደናገጠ ቢሆንም፤ የኃጢአት ሰለባዎች ለሆንነው ለእኛ ለሁላችን የፈውስ ሂደት ፍንጮችን በተለያዩ መንገዶች ከራእይ መጽሐፍ መመልከት እንችላለን፡፡ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስለሚገኘው የህይወት ዛፍ ዮሐንስ ሲያብራራ "የዛፉም ቅጠሎች

ሕዝቦች የሚፈወሱባቸው ነበሩ" ይላል (ራእ. 22፥2)፡፡ በድጋሚ እግዚአብሔር ሰውን እንደሚያስተውል፣ ለሰው እንደሚራራ፣ ሰው መሆን ያለውን ስሜት፣ ትርጉሙን፣ ተሞክሮውን፣ ምስክርነቱን ከዚያም አልፎ የዓለም ክፋት ተጋሪነቱን እንደሚረዳ ያሳየናል፡፡ ምድራችንን ዳግም የመፍጠር እቅዱ እኛን ወደ ቀድሞው ንጽህና መመለስና መፈወስን ያካትታል፡፡

ምንም እንኳ የእኛን ችሮታ ለሚሹ በዙሪያችን ያሉ ወገኖች የምናበረክተው አገልግሎት በማቅማማት የታጀበና እጅግ አነስተኛ ሊሆን ቢችልም፤ ነገር ግን እስከዚያው የድርሻችንን እያበረከትን በክርስቶስ መሆን የምንችለውን ሁሉ ለመሆን የተቻለንን ጥረት ለማድረግ ምኞታችን ነው፡፡ አገልግሎታችን የቱንም ዓይነት ሊሆን ቢችል ማለትም--በበጎ ቃላት የመንፈስ ልዕልና መፍጠር፣ ለተራበው ማብላት፣ የህክምና እርዳታ መስጠት፣ የታረዘውን ማልበስ ወይም የምክር አገልግሎት መስጠት ሊሆን ቢችል--ሁሉም የሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ወቅት ባሳየን ዓይነት ራስን ዝቅ በማድረግ፣ ራስን በመካድና ራስን ለሌላው መሥዋዕት ባደረገ ፍቅር ሊተገበር ይገባል፡፡

ምንም እንኳ የተቻለንን ጥረት ከማድረግ ባንቦዝንም ዓለም ከመቼውም ይልቅ እየከፋችና ነገሮች እየተባባሱ መሄዳቸው እርግጥ ነው፡፡ ይህ እንደሚሆን ያውቅ የነበረውን የሱስ እውነታው ከማገልገል እንዳልገታው ሁሉ፤ በተመሳሳይ እኛንም ሊገታ አይገባም፡፡

## አርብ                                                    መስከረም 2

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** *Read Ellen G. White, "Called to Reach a Higher Standard," pp. 309–322, in The Acts of the Apostles; "Desolation of the Earth," pp. 653–661, in The Great Controversy.*

"የእግዚአብሔር ድምጽ የሕዝቦቹን ምርኮ ሲመልስ፤ በታላቁ የህይወት ተጋድሎ ሁሉንም አምላካዊ ነገር ያጡ በጣም አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ ይነቃሉ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚፈተኑበት ጊዜ በቀጠለ ቁጥር ዐይኖቻቸው በሰይጣን ማታለያ ተሸብበውና የኃጢአት መንገዳቸውንም አጽንተው ይዘው ነበር፡፡ ሀብታሞች የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሰው በሰበሰቡት ሀብት በድኾች ላይ ታበዩ፡፡ የተራበውን ለማብላት፣ የታረዘውን ለማልበስ፣ በቅንነት ለማስተናገድና ምኅረትን ለመውደድ ችላ አሉ. . . ለምድራዊው ተድላና ፍስሐ ነፍሳቸውን ከመሸጥ ውጪ በእግዚአብሔር ፊት ባለጸጋ ለመሆን አልተመኙም፡፡ በውጤቱ ህይወታቸው በውድቀት፣ ደስታቸው በከባድ ሐዘን፣ ሐብታቸውም በንቅዘት ተበላ፡፡"—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 654.

*“ታላቁ ተጋድሎ ፍጻሜ አግኝቶአል፡፡ የኃጢአትና ኃጢአተኞች ጉዳይ አክትሟል። መላው ጽንፈ ዓለም ወደ ቀደመ ንጽህናው ተመልሶአል፡፡ በመላው ፍጥረት ውስጥ አንድ ዓይነት ስምምነትና ውህደት ሰፍኖአል፡፡ ወሰን በሌለው ግዛት ሁሉን ከፈጠረው ከእርሱ--ህይወት፣ የብርሃን ጸዳልና የደስታ ፍስሐ ይፈሳል፡፡ ኢምንት ከሆነው አቶም እስከ ግዙፉ ዓለም፣ ህይወት ያለው ወይም ግዑዙ--አንዳችም ጥላ ባላጠላበት ውበትና ፍጹም ደስታ እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ያውጃሉ፡፡”*—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 678.

*የመወያያ ጥያቄዎች፡*

***1.በዚህ ሣምንት ባጠናነው መሰረት ምድራዊ ማንነትዎ ያንኛውን ሕይወት እንዴት እንደሚያሳይ ያብራሩ፡፡ እግዚአብሔር ይህን ምድር አጥፍቶ ሁሉም ነገር እንደገና ከአዲስ ስለሚጀምር ስለዚህ ምድርም ሆነ ህይወት መጨነቅ የለብንም ከሚለው እምነት ጋር መልስዎን ያመሳክሩ፡፡ ይህን የአዲስ ፍጥረት ተስፋ እውነት በችግር ያሉትን ችላ ሳንል ጥቅም ላይ ለማዋል ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን እንዴት ነው? ይህን እውነት ሌሎችን ለመበዝበዝ ጥቅም ላይ ላለማዋላችን እርግጠኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?***

***2.የየሱስ ዳግም ምጽአት በተቃረበ ቁጥር የክፉው አሠራር፣ ችግርና ሥቃይ እየጨመረ ይሄዳል ብላ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን--ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት አኳያ የዚህን እውነት ገቢራዊነት ትጠባበቃለች፡፡ እነዚህ ነገሮች እያየሉ በሄዱ ቁጥር በተደጋጋሚ ከምናደርጋቸው ነገሮች አንዱ ማቴ. 24ን ማንበብ ነው፡፡ አሳዛኞቹን ክስተቶች ከማቴ. 25 አኳያ እንዴት እናስተውላቸዋለን?***

***<u>ማጠቃለያ፡</u> ክፉው መጨረሻ ለሌለው ዘመን ተንሰራፍቶ እንዲኖር አምላካችን አይፈቅድም። የሱስ ለክፉው ፍጻሜ፣ ለኢፍትሐዊነት ፈውስ በማምጣት የቀደመ ንጽህናዋን የያዘች አዲስ ምድር ዳግመኛ ሊፈጥር ዳግም ይገለጣል። ይህ ታላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋ ነው። በየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ የተገነባው ይህ ተስፋ ዛሬ እኛን በመለወጥ ዳግም ምጽአቱን እየተጠባበቅን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ለምንሰጠው አገልግሎት ወኔ ይሆነናል።***

# 12ኛ ትምህርት

ከመስከረም 3-9

# ምህረትን መውደድ

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማቴ. 6:25–33፣ ያዕ. 1:5–8፣ 2:15-16፣ ኢሳ. 52:7፣ 1ዮሐ. 3:16–18፣ ኢሳ. 58:1–10፡፡*

**<u>የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-</u> "ለቅን ሰው በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይወጣለታል፡፡ ለጋስና ያለ ማንገራገር የሚያበድር፣ ሥራውንም በትክክል የሚያከናውን ሰው መልካም ይሆንለታል" (መዝ. 112፣ 4-5)፡፡**

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለ ደኻውና የተጨቆነው ምን ያህል እንደሚቆረቆር--ሕዝቡም ስለ እነዚህ ሰብዓዊ ወገኖች እንዲሠራ የቀረቡለትን ጥሪዎች በሚያሳዩ ጥልቅ ስሜት ባላቸው መግለጫዎች የተሞላ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ምንም እንኳ ለእነዚህ ጉዳዮች ትኩረት ሲሰጥና ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አደራ አልፎ አልፎ ፍጻሜ ሲያገኝ ቢስተዋልም፤ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ፍጻሜ የሚያገኘው ከየሱስ ዳግም ምጽአት በኋላ ገቢራዊ በሚሆኑ ታላላቅ ክስተቶች ይሆናል፡፡

እስከዚያው ግን ክፉው ከጨለማው የዲያብሎስና መላእክቱ ተጽእኖ በሚያገኘው ጉልበት እየታገዘ በብዙ ቅርጽና መጠን መታየቱን ይቀጥላል፡፡ ይህ ክፉ አዘውትሮ የሚገለጥባቸው መንገዶች ድኽነት፣ ብጥብጥ፣ ጭቆና፣ ባርነት፣ ብዝበዛ፣ ራስ ወዳድነትና ስስት ናቸው፡፡ የቱንም ያህል ዋጋ ሊያስከፍል ቢችልም--ማኅበረሰባችን፣ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ቤተሰባችን ከእነዚህ የክፉ ተግባራት በተቃራኒ ሊቆሙ ይገባል፡፡ ለእግዚአብሔር ፍቅርና ትእዛዞች በምንሰጠው ምላሽ፣ በየሱስ አገልግሎትና የመሥዋዕትነት ብርሃን በምናደርገው መመላለስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላታችንና ምሪት ማግኘታችን--ፍትሕን እናደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም እንወድድ ዘንድ፣ በአምላካችን ፊት በትህትና መራመድን (ሚልክ. 6፡8) አጥብቀን በመሻት ሩኅሩኅዎች፣ ብልህዎችና ጀግኖች ልንሆን ይገባል፡፡

## እሁድ

## መስከረም 4

# የሰማያዊው መንግሥት ቅድሚያዎች

በየሱስ አስተምህሮና በአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ግልጽ ሆኖ እንደቀረበው የእግዚአብሔር መንግሥት አባል ሆነው ለመኖር የሚመርጡ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች ዓለም ቅድሚያ ከምትሰጣቸው በእጅጉ የተለዩ ናቸው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 6፡25-33፡፡ በጥቅሶቹ የተሰጠን መጽናኛ ምንድን ነው? ይህ መጽናኛ ቅድሚያ በምንሰጣቸው ነገሮች ላይ እንዴት ተጽእኖ ማሳደር ይችላል?

---

---

የሱስ "ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን?" በማለት በማቴ. 6፡ 25 ይናገራል፡፡ የእነዚህ ነገሮች አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ባይገባም፤ በአምላካዊው መንግሥት ብርሃን ልናያቸው ግን የግድ ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ህይወታችንን በተጨባጭ ማስቀደም ይኖርብናል፡፡ ሌሎችን ስንረዳና ስናግዝ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክቶች ለቀረቡት ጥሪዎች እውቅና እንሰጣለን፡፡ የየሱስን ፈለግ ለመከተል ያለንን መሻት ስናሳይ ይህ ጥሪ ቅድሚያ ከምንሰጣቸው ነገሮች መካከል አንዱ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ጥሪ በራሳችን ጉዳዮች ዙሪያ በጥቂቱ--ሌሎች ላይ ግን የላቀ ትኩረት እንድናደርግ ሊረዳን ይገባል፡፡

ይህ ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንዳለብንና እንደሌለብን እገዛ የሚያደርግልን ትክክለኛ አስተሳሰባዊ አወቃቀር ከምድራዊ አለቆቻችንና ከተጨቆኑ ጋር ያለንን ግንኙነት ይቀይራል፡፡ ክርስቲያኖች በተቻላቸው መጠን መንግሥታዊ አካላትን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር ሁሉ (ሮሜ. 13፡ 1-7) "ከሰው ሁሉ ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል" (ሐዋ. 5፡29) ሲል ሐዋርያው ጴጥሮስ የጻፈልንን የምናስተጋባበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም መዘንጋት የለብንም፡፡ አንዳንዶች የሱስን በተንኮል ለማጥመድ በጠየቁት ጊዜ የሰጣቸው መልስ እነዚህን ሁለት መርኅዎች በሚዛናዊነት ያስቀመጠ ነበር "'የቄሳርን ለቄሳር፤ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ'" (ማቴ. 22፡21)፡፡

የመንግሥት ይሁን ወይም ከዚያ ውጪ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች እያስፈራሩ ወይም ኃይል እየተጠቀሙ የበላይነታቸውን ጠብቀው ለማቆየት ሲሞክሩ በተደጋጋሚ

ይስተዋላሉ፡፡ ክፉው ለተጋረጠበት ሁኔታ በታማኝነት ለመመላለስ ሁል ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ታዛዥ መሆን እንደማይጠበቅብን ከየሱስ ህይወት መመልከት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ስለነበረው የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ኤለን ጂ. ኋይት የሚከተለውን ጽፋለች፡ "የሰው ሕጎች ከአምላካዊው ቃል እና ሕግ ጋር ሲጣረሱ ውጤቱ የቱንም ዓይነት ሊሆን ቢችል የአምላክን ቃል መታዘዝ ይኖርብናል፡፡ ባሪያን ለባለቤቱ እንድንሰጥ የሚጠይቀንን የምድራችንን ሕግ የማንታዘዝ ከሆነ ይህን ሕግ በመጣሳችን የሚመጣውን መዘዝ መቀበል የግድ ይሆናል፡፡ ባሪያ የማንም ሰው የግል ንብረት አይደለም፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔር ባለመብት ጌታ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው የባለ-እጁን ንብረት እንደ ራሱ መቁጠር አይችልም፡፡"—Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 201, 202.

***ለባለሥልጣኖች በመታዘዝ እና በጨቋኝ ሥልጣን ሰለባ ሊሆኑ በሚችሉ ወገኖች በመቆም መሀል ያለው ቀጭን መስመር መገኛው የት ላይ ነው?***

## ሰኞ መስከረም 25

## በርኅራኄ መዛል

ስለዚህ ዓለም መጨነቃችንን ተቋቁመን በሥቃይ ውስጥ የሚገኙ ወገኖች ህይወት ላይ ልዩነት ማምጣት የአብዛኞቻችን ፍላጎት ነው፡፡ በችግር ውስጥ ለሚገኙ ሰብዓዊ ወገኖች አዎንታዊ ምላሽ እንድንሰጥ ሊረዱን የሚችሉ በርካታ ባህሪያትና ድርጊቶች አሉ፡፡

ርኅራኄ፡ ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ሁኔታ በቅጡ አጢኖ ችግራቸውን እንደ ራስ ማየት ወደ ድርጊት የሚመራን የመጀመሪያው ቅደም ተከተል ነው፡፡ በሥቃይ ለሚገኙ የምናንጸባርቀውን የመቆርቆር ስሜት ማሳደግና ጠብቀን ማቆየት አለብን፡፡ በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን አሳዛኝ ታሪክ ስንሰማ ከርኅራኄ ብዛት የሚከሰት የልብ መሰበርና ሐዘን ኪሳችንን ከመዳበስ አልፎ ጭንቀት ውስጥ ሊከተን የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ዙሪያውን የከበበውን ክፋትና ሥቃይ በጥንቃቄ ያስተውል የነበረው የሱስ በርኅራኄው እንደ ጸና ሁሉ እኛም የእርሱን ፈለግ መከተል ይጠበቅብናል፡፡

ትምህርት፡ አብዛኞቹ ከፍትሕ መዛባትና ድኽነት ጋር ትስስር ያላቸው ሁናቴዎች ውስብስብ ከመሆናቸው አኳያ አንድን ጉዳይ ከስሩ ማድመጥና ምን ማድረግ እንደምንችል መማር በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ እርዳታ ለማድረግ ከመሞከር ጋር ተያይዞ አስቀድመው በተወጠኑ ተገቢ ያልሆኑ ተግባሮች በሌሎች ህይወት ላይ የተፈጸሙ በምሳሌ የሚጠቀሱ አያሌ መሰሪ ተግባራት አሉ፡፡ ይህ ሌሎችን ላለመርዳት እንደ ሰበብ መቆጠር እንደማይችል ሁሉ በቂ መረጃ ባላቸው የርኅራኄ ተግባራት ለመሳተፍ ፍላጎት ሊኖረን ይገባል፡፡

ጸሎት፡ አንድ የሆነ ችግር ስንመለከት በመጀመሪያ ወደ ልባችን የሚመጣው “በተግባር የሚገለጥ” ድርጊት ነው፡፡ ሆኖም ጸሎት በተግባር የሚገለጥ ድርጊት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ለድኾችና ለተጨቆኑ እንዲሁም ለበላዮቻቸው በመጸለይ በህይወታቸው ላይ ተጨባጭ ልዩነት ማምጣት እንችላለን (1ጢሞቴ. 2፡ 1-2)፡፡ በተጨማሪ ውጤታማ በሆነ አካሄድ ልንረዳቸው የምንችልበትን አምላካዊ ምሪት መሻትም እንዲሁ ከእኛ ይጠበቃል (ምሳ. 2፡7-8)፡፡

ተስፋ ማድረግ፡ በሥቃይ ውስጥ ያሉትን ሰብዓዊ ወገኖች ችግር ለማቃለል የምንሠራበት ሌላው አስፈላጊ ነጥብ ውስብስብ ለሆኑ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ግላዊ ሁናቴዎች ተገቢ ግምት መስጠት ነው፡፡ ሰዎች ሊኖራቸው ያልቻለውን ምርጫና ዕድል መስጠት ተስፋችን ሊሆን ይገባል፡፡ ምንም እንኳ እነዚህን እድሎች የሚያገኙ ሰዎች አንዳንዴ ቅር ሊያሰኙን ቢችሉም እነዚያን ምርጫዎች ማክበራችን ግን የግድ ይሆናል፡፡ በሥቃይ ውስጥ ላሉ ሰዎች በየትኛውም አቅጣጫ ልንሠራ ብንሞክር የምንከተለው መርኅ “ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው” የሚል ነው (ማቴ. 7፡12)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ያዕ. 1፡5-8፡፡ በክርስቲያን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጸሎት ምን ዓይነት ሚና ሊኖረው ይገባል? ለሌሎች የምንጸልየውን ጸሎት ምላሽ በመስጠቱ ረገድ እንዴት ራሳችን አስተዋጾ ሊኖረን እንደሚችል ያዕ. 2፡15-16 ምን ይጠቁመናል?**

**ማክሰኞ** **መስከረም 6**

# ልግስና

“እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል” (2ቆሮ. 9፡7)፡፡ በልግስና መስጠት የክርስትና ህይወት መሰረታዊ ገጽታ ነው፡፡ በመስጠታችንና ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ማስቀደም ስላለብን ነገር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሞግተን መፍቀዳችን እንዳለ ሆኖ፤ ልግስና ገንዘብን ለአንድ ጉዳይ ከመወርወር የላቀ ፋይዳ አለው፡፡

ይልቁንም ልግስና በመዝ. 112 በተደጋጋሚ እንደ ተገለጸው “እግዚአብሔርን የሚፈሩ” አብዛኛው የሕይወታቸው አመለካከትና ቁልፍ መለያ ባህሪ ነው፡፡ “ለጋስና ያለማንገራገር የሚያበድር፣ ሥራውንም በትክክል የሚያከናውን ሰው መልካም ይሆንለታል” (መዝ. 112፡5)፡፡

በችግር ላሉ ልግስና ስለ ማሳየት ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል? ዘሌዋ. 25፡35-37፣ መዝ. 119፡36፣ 2ቆሮ. 8፡12-15፣ 1ዮሐ. 3፡16-18፣ 1ጢሞቴ. 6፡17-19፡፡

ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን መልእክቶቹ የክርስትና ተስፋ ምንጭ የሆነው የሱስ ስለ እኛ የሰጠውን ፍቅሩን በመግለጽ ስለ እግዚአብሔር ልግስና በተደጋጋሚ ጠቅሶአል፡፡ የእርሱ ለእኛ መሞት ስለ ሌሎች ለጋስ ህይወት እንድንኖር አነሳሽ ምክንያታችን ነው፡ “በክርስቶስ ስላለን መልካም ነገር ሁሉ በሚገባ ትረዳ ዘንድ፣ እምነትህን ለሌሎች በማካፈል እንድትተጋ እጸልያለሁ” (ፊልሞ. 1፡6)፡፡

ልግስና ግዝፈት ያለው፣ በድፍረት የተሞላና አቃፊ የህይወት አመለካከት ነው፡ ፡ አብዛኛው ግላዊ፣ ማኅበረሰባዊና ባህላዊ የህይወታችን ክፍል የተቻለንን ያህል በራሳችን ዙሪያ ትኩረት እንድናደርግ ይገፋፉናል፡፡ እውነት እንነጋገር ከተባለ የአብዛኞቻችን ነባራዊ ሁኔታ ሁል ጊዜም እኔ፣ እኔ፣ እኔ--ብቻ ነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እምነታችን እኔነትን ገድሎ ለሌሎች እንድንኖር መንስኤ ይሆነናል፡፡ እምነታችን ዓለምንና ሕዝቦቿን እግዚአብሔር በሚያይበት ዐይን ማየት እንድንችል ይረዳናል፡፡ እርዳታ ለሚያሻቸው አቅማችን እንደ ፈቀደ የበኩላችንን እንድናበረክትም ይገፋፋናል፡፡

ምርጥ የሕይወት ዘይቤ የሆነው ለጋስነት በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዘንድ ከፍ ያለ አድናቆት ይቸረዋል፡፡ እንዲህ ያለው ልግስና በመጠን የሚለካና በቀጥታ

ሥራ ላይ መዋል የሚችል ነው፡፡ ሆኖም ከፍ ያሉ ችሮታዎች የሰጪውን በልግስና የተሞላ ህይወት ላያንጸባርቁ ይችላሉ (ማር. 12፡41-44)፡፡ በልግስና የተሞላ ህይወት ከማንኛውም ችሮታ የላቀና የገዘፈ ነው፡፡ በምናደርጋቸው ነገሮች ለልግስና መንፈስ የተሻለ ዋጋ ልንሰጥና እንዲዳብር መፍቀድ ይጠበቅብናል፡፡ ልግስና ለብዙዎች አብሮአቸው የተፈጠረ ነገር አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ኃጢአተኛውና ራስ ወዳዱ ሰብዓዊ ማንነት ቁልቁል ቢስበንም፤ ይህን ጸጋ በእቅድና በዝግጅት በህይወታችን ገልጠን ልናወጣ ይገባናል፡፡

***በልግስና ገንዘብ ከመስጠት ጎን ለጎን በልግስና የተሞላውን መንፈስ ገልጸን የምናሳይባቸው ሌሎች መንገዶች የትኞቹ ናቸው?***

## ረቡዕ መስከረም 7

# ሰላም ማውረድ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 5፡9፡ እኛ በምንኖርበት በዚህ ዓይነቱ ዓለም የሱስ እየተናገረ ያለውን በሥራ ላይ ማዋል የምንችለው እንዴት ነው? ውሎ አድሮ ስኬታማ መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ማር. 13፡7፡፡

---

---

የከረረ ግጭት ዋንኛ የሥቃይና እንግልት መንስኤ ነው፡፡ በጦርነት ምክንያት በህይወት ላይ በቀጥታ የሚደርሰው ምስቅልቅልና ሥቃይ ውጊያ የሚያስወጣው ከፍተኛ ወጪ ዋንኛ አካል ነው፡፡ ለጦር ተሸከርካሪና መሣሪያ የሚውለው ሀብት ከዘመቻ ተርፎ የተመለሰውን “አሸናፊ” ጨምሮ የሰብዓዊውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማቅለል ቢውል እጅግ የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስፍር ቁጥር የሌለውን ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ህይወት ፍርሃት ውስጥ የሚከቱ በርካታ አነስተኛ ግጭቶች አሉ፡፡ ፍትሕ እንዲሰፍን አጥብቆ የሚሻው ማንነት ሰላም እንዲያወርድ የተጣለበትን ዐደራ ችላ ብሎ ማለፍ አይችልም፡፡

ቸርና ለጋስ የሆነው መሃሪ አምላክ ታላቁ ድርጊት፤ ከኃጢአተኛው ሰብዓዊ ፍጡር ጋር ሰላም ማውረድና ከፈጣሪው ጋር ማስታረቅ ሲሆን ይኸውም የየሱስ ወንጌል አስኳል ነው (2ቆሮ. 5፡18-21)፡፡ ይህ የምንቀበለው እርቅ ለሌሎችም “አምባሳደሮቹ” እንድንሆን ያስችለናል፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ኢሳ. 52፡7 ይህን አባባል ወደ ተግባር የሚቀይሩት እንዴት ነው?

___

___

___

የሰላም ወንጌል ነውጠኛዋ ዓለም ወደ ሰላም እንድንመጣ አነሳሽ፣ ተምሳሌትና በተግባር ላይ መዋል የሚችል ሰነድ ነው፡፡ "ከእግዚአብሔር ጋር ስምሙ የሆነው ልብ የሰማያዊው ሰላም ተካፋይ በመሆኑ የተባረከውን ተጽእኖ በዙሪያው ያሰራጫል፡፡ የሰላም መንፈስ በዓለማዊው ሁከት የተቸገሩ ልቦች ላይ እንደ ጤዛ ያርፋል፡፡"—Ellen G. White, Thoughts From the Mount of Blessing, p. 28.

የሱስ በተረራው ላይ ስብከቱ "ሰላምን የሚያወርዱ ብፁአን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና" (ማቴ. 5፡9) በማለት ተናግሮአል፡፡ የሱስ ይህንን ሀሳብ ወደ ላቀ ደረጃ ሲያሸጋግር አትግደል የሚለውን ትእዛዝ ማጽናት ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው ወንድሙን ያለ አግባብ መቆጣት ወይም ቂም መያዝ (ማቴ. 5፡21-26) እንደሌለበት ተናግሮአል፡፡ እንዲሁም ጠላቶቻችንን ልንወድና ለሚያሳድዱን ልንጸልይ እንደሚገባ (ማቴ. 5፡43-48) ማለትም የእነርሱን መልካም ነገር በመፈለግ ንቁ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚኖርብን ተናግሮአል፡፡ በተለያዩ ግጭት የሚስተዋልባቸው የዓለም ክፍሎች በመጠኑም ቢሆን የእርቅ፣ የሰላምና የፈውስ ጭላንጭል እንዲታይ በማድረግ፣ ግጭቶቹ ያስከተሏቸው መጠነ ሰፊ ሥቃይና እንግልቶች እንዲቀንሱ ያላሰለሰ ሚና የተጫወቱ ልብ የሚነኩ የብዙ ሰዎች ታሪኮች አሉ፡፡

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ በአጥቢያ ደረጃ ሰላም የማውረድ ሚና እንዲኖራት የሚያስችሉ አካሄዶች የትኞቹ ናቸው?**

**ሐሙስ** **መስከረም 8**

# ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ መሆን

ሰለሞን "ለዝምታ ጊዜ አለው፤ ለመናገርም ጊዜ አለው" (መክ. 3፡7) በማለት ጽፏል። ትክክል ነበር፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን ሚዛናዊ ሁኔታ ማግኘት ለማንኛችንም ቢሆን ቀላል አይደለም፡፡ ነገር ግን ለተጨቆኑና ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ በመሆንና ክፉን በመልካም ለማሸነፍ መፈለግ ረገድ እንደ ቤተ ክርስቲያን ድምጻችን ሊሰማ ሲገባው በጣም ዝምታ በሰፈነበት አቅጣጫ መዋላችን ስህተት ይሆን?

ክርስቲያኖች የሱስ ሌሎችን እንድናገለግል ያቀረበልንን ጥሪ በመጥቀስ የየሱስ እጆችና እግሮች ስለ መሆን አዘውትረው ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ነገር ግን ከትንቢታዊ ሚና አኳያ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ቀረበው ከሆነ እግዚአብሔር ለወንዶችና ለሴቶች ያቀረበው የመጀመሪያ ጥሪ የእርሱ ድምጽ ሆነው--እንዲናገሩና እርሱ ሊከላከልላቸው ለሚፈልጋቸውም አንደበት ይሆኑ ዘንድ ነው (መዝ. 146፡6-10)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 58፡1-10፡፡ በዚያ የተወሰነ ጊዜ፣ ቦታ እና ዐውድ የተሰጠው ይህ መልእክት ዛሬ ለእኛ በሌላ ጊዜ፣ ስፍራና ዐውድ ለምንገኝ ምን እያለን ነው? ኢሳይያስ ይህን መልእክት በጻፈበት ጊዜና በዛሬዋ ዓለማችን መሀል ነገሮች ምን ያህል ተለውጠዋል?

ፍትሕ እንዲሰፍን ነቢዩ ያቀረበው ጥሪ ወደ ዝና የሚወስድ ልነበረም፡፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ተልዕኮ በመነሳሳት፣ እርሱ ለፍትሕ የነበረውን ጥልቅ ፍላጎት በማስተዋል፣ የድኾችንና የተጨቆኑትን ሐዘንና መከራ በመካፈልና ምርጥ የሆነውን ለማኅበረሰባቸው በመመኘት--ነቢያቱ ብርቱ ተቃውሞ፣ መጎሳቆልና አደጋ ቢጋረጥባቸውም እነርሱ ግን ለነበሩበት ጊዜና ስፍራ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ለመሆን ደፈሩ (1ጴጥ. 3፡7)፡፡

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ስለ ወንጌል ባለን መረዳትና የሱስን ለዓለም ለማንጸባረቅ በቀረበው ጥሪ--በዓለም ከሰፈነው ክፉ ጋር በሚደረገው ግብ ግብ አያሌ ልናበረክት የምንችላቸው መልካም ነገሮች አሉ፡፡

"ድኽነትንና ተጓዳኝ ኢፍትሐዊነትን ለመቀነስ የሚደረግ እርምጃ የክርስቲያን

ማኅበራዊ ሀላፊነት አስፈላጊ ክፍል ነው ብለው ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ያምናሉ። እግዚአብሔር ለድኾች ያለውን የተለየ ፍላጎት እና የእርሱ ተከታዮች ራሳቸውን መርዳት ላልቻሉት ምላሽ ሲሰጡ ለመመልከት ተስፋ እንደሚያደርግ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ መላው የእግዚአብሔርን አምሳል የያዘ የሰው ዘር የአምላካዊ በረከት ተቀባይ ነው (ሉቃ. 6፡20)፡፡ እኛ ከድኾች ጋር በመሥራት የየሱስን አስተምህሮ ምሳሌ እንከተላለን (ማቴ. 25፡35-36)፡፡ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች እንደ አንድ መንፈሳዊ ማኅበረሰብ 'ስለ ራሳቸው መናገር ለማይችሉ በመናገር' (ምሳ. 31፡8) እና 'የደኻውን መብት የሚገፍፉትን' (ኢሳ. 10፡2) በመቃወም ስለ ድኻው ፍትሕ ይቆማሉ፡፡ 'የደኻውን ፍትሕ ከሚያስጠብቀው' (መዝ. 140፡12) እግዚአብሔር አምላክ ጋር ተሳትፎ እናደርጋለን፡፡" Seventh-day Adventist Official Statement on Global Poverty, June 24, 2010.

## አርብ **መስከረም 9**

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** Read Ellen G. White, "A Higher Experience," pp. 503–516, in The Ministry of Healing; "Duty to the Unfortunate" and "Man's Duty to His Fellow Men," pp. 511–526, in Testimonies for the Church, vol. 3; "Doing for Christ," pp. 24–37, in Testimonies for the Church, vol. 2.

"ሰማይና ምድርን ብንፈትሽ የእኛ ርኅራኄና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በምህረት ሥራዎች ከተገለጠው የላቀ በግዝፈት የተገለጠ እውነት የለም፡፡ ይህ በየሱስ የነበረ እውነት ነው፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች ነን የሚሉ የወርቃማውን ሕግ መርኅዎች በተግባር ላይ ሲያውሉ ለሐዋርያት ወንጌል የወረደው ኃይል በእነርሱም ገቢራዊ ይሆናል"—Ellen G. White, Thoughts From the Mount of Blessing, p. 137.

"የከበረውን ፍቅር ለእግዚአብሔር እንድናሳይና እርስ በርሳችን ደግሞ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ፍቅር እንዲኖረን የሚያስችል ምርጥ ስጦታ የሰማዩ አባታችን ሊሰጠን ይችላል፡፡ ይህ ፍቅር ስሜት ሳይሆን የማይለዋወጥ መለኮታዊ መርኅ ነው። ራሱን ለጌታ ቀድሶ ያልሰጠ ልብ ይህን ፍቅር ከየትም ሊያመጣው አይችልም፡፡ የሱስ በነገሠበት ልብ ውስጥ ብቻ ይገኛል. . . ይህ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ፍቅር ህይወትን ያጣፍጣል፣ በዙሪያችንም አዎንታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 551.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.የሱስ ስለ እኛ መጠነ ሰፊ ተግባራትን እንዳከናወነ እኛም ስለ ሌሎች እንሠራ ዘንድ ወንጌል ምሳሌያችንና መበረታቻ ምክንያታችን ሆኖ መቀጠሉን በዚህ ሣምንት ጥናታችን ተመልክተናል፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውንና ፍቅሩን የገለጸበትን ይህን መልካም የምሥራች ያስተውሉና ያደንቁ ዘንድ አመለካከትዎን ማስፋት የቻለው እንዴት ነው?**

**2.ድምጻቸው ለማይሰማ ድምጻችንን ማሰማታችን፣ ሰላም በማውረድ ተግባር ላይ መሳተፋችንና የሌሎች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች አካል መሆናችን ወደ ሕዝባዊና ፖለቲካዊ መድረኮች እንድንሳብ ሊያደርገን ይችላል፡፡ ሆኖም ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት እና በቤተ ክርስቲያን መካከል መለያየት እንዲኖር አጥብቃ በመሥራት ትታወቃለች፡፡ አግባብ ባልሆነ መንገድ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባትና ድምጽን እያሰሙ ለሰላም በመሥራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

**3.በዚህ ሣምንት ጥናታችን ከተወያየንባቸው ነጥቦች መሃል የትኛውን ለግልዎና ለማኅበረሰብዎ መተግበር ይችላሉ? ይህን እንዴት እውን ማድረግ ይችላሉ?**

**4.ለማኅበረሰብዎ ወይም በዓለማቀፍ ደረጃ ሊጸልዩበት የወሰኑት የከፉው ርዕሰ ጉዳይ እና ጭቆና የትኛው ነው?**

*ማጠቃለያ፡ እግዚአብሔር ስለ ደኻውና ስለ ተገፋው ያለውን ብርቱ መቆርቆር የምንቀላቀልበትን ቅንአት በውስጣችን መፍጠር ጨምሮ፤ የየሱስ ተከታይ መሆን ህይወታችንን በብዙ መንገድ ይለውጠዋል። ይህ እምብዛም ገናና ያልሆነ ነገር ፈጽሞ ቀላል ኃላፊነት አይደለም። ቅድሚያ እንሰጣቸው የነበሩ ነገሮችን ትተን በአካባቢያችን ብሎም በዓለም ዙሪያ የሚገኙትን የተጎዱ ሰብዓዊ ወገኖች ለመፈወስ በሚያስችሉን ቅደም ተከተሎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ይኖረን ዘንድ መነሳሳት ይፈጥርልናል።*

# 13ኛ ትምህርት

**ከመስከረም 10-16**

# “እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ”

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 2:14–16፣ ዘፀ. 32:1–14፣ 1ጴጥ. 2:12፣ ፊልጵ. 2:15፣ ኤፌ. 2:19፣ ዕብ. 10:23–25፡፡*

**የሣምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡ :-**“የተስፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለሆነ፣ አምነን የምንናገርለትን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ፡፡ እርስ በርሳችንም ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ” (ዕብ. 10፡23-24)

ክርስቲያናዊውን ተልዕኮ ከፍጻሜ ለማድረስ ላለን ብርቱ መሻት ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ የተደራጀ አማኝ ማህበረሰብ ያላትን ጉልበት ዝቅ አድርገን ማየት የለብንም፡፡ ከኢፍትሐዊነትና ድኽነት ጋር ለምናደርገው ትግል ሊገጥሙን የሚችሉ ተግዳሮቶችን ቀደም ባለው ጥናታችን ለማየትና ግንዛቤ ለማግኘት ሞክረናል፡፡

እኛ እንደ ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ስንሆን ቤተ ክርስቲያን ዓለምን እንድታገለግል በእግዚአብሔር የተፈጠረች፣ የተሰየመችና ይህን ተከትላ መጓዝ እንዳለባት ትኩረት ከማድረግ እየዘነጋን እንፈተናለን፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን አካልነታችን በዙሪያችን እየተከሰተ ያለውን ሥቃይና ክፉ እያየን እንዳላየ ማለፍ የለብንም፡፡ ክርስቶስ ችላ ካላለው እኛም ችላ ማለት የለብንም፡፡ ወንጌልን እንድንሰብክ ለተሰጠን ኃላፊነት ታማኞች ልንሆን ይገባል፡፡ ለተጨቆኑት፣ ለተራቡት፣ ለታረዙትና ለረዳት አልባዎች መሥራት ወንጌልን ከመስበክ ጋር በተጓዳኝ ይሄዳል፡፡

እንደ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብና ድርጅት እኛ ሁላችን በአንድ ላይ የክርስቶስ አካል ነን (1ቆሮ. 12:12–20)፡፡ ይህን ተከትሎ እንደ አንድ ማኅበረሰብ የሱስ እንደ ተራመደ ልንራመድ፣ ወደ ሰብዓዊው ወገን እንደ ደረሰ ልንደርስ፣ ለዛሬዋ ዓለም የየሱስ እጆች፣ እግሮች፣ ድምጾችና ልቦች ሆነን እንድናገለግልና ወደ ሁሉም እንድናመራ ተጠርተናል፡፡

# እሑድ መስከረም 11

## የለውጥ ሐዋርያዎች

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያን አማኞች በመካከላቸው ለነበሩ ችግረኞች እንክብካቤ በማድረግ፣ በአንድነት ሆነው ከእነርሱ ማኅበረሰብ ውጪ ወደነበሩ ምስኪኖች በመድረስ እና እግዚአብሔር በመካከላቸው ያደርግ የነበረው በጎነት ተካፋይ እንዲሆኑ በመጋበዝ እንዴት በዓይነቱ ልዩ የሆነ ማኅበረሰብ እንደ መሰረቱ ቀደም ባሉት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ተመልክተናል፡፡

የሱስ ስለ ጨው እና ብርሃን በሰጠው ምሳሌ ላይ አንዳንድ ነጥቦችን ያከለው ጳውሎስ፤ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ስላላት ኃላፊነት በርካታ ዘይቤዎችን ተጠቅሞአል። ከእነዚህም መሃል የእግዚአብሔር ተወካይ ሕዝቦች ሆነው የሚመላለሱትን እንደ መሥዋእት (ሮሜ 12፡1)፣ የክርስቶስ አካል (1ቆሮ. 12፡12-20)፣ አምባሳደሮች (2ቆሮ. 5፡18-20)፣ ሽቶ (2ቆሮ. 2፡14-16) አቅርቦአል፡፡ ምድራችን በታላቅ ተቃርኖ እየጠፋች ባለችበት በዚህ ወቅት--እነዚህ እያንዳንዳቸው እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ተወካይነታችን ስላለን ሚና ይናገራሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን የእግዚአብሔር ተወካይ ሕዝቦች ማንነት ይከልሱ፡፡ እርስዎ እግዚአብሔርን ለመወከል የሚመርጡትን መንገድና ለማኅበረሰብዎ ያለውን ዓላማ ጥሩ አድርጎ የሚገልጸው የትኛው ነው? ለምን?

---

---

እነዚህ እያንዳንዳቸው--ከየራሳቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድርጊት አላቸው ይህን የሚያደርጉት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ሳይሆን፤ ነገር ግን በክርስቶስ መሥዋእትነት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳገኙ ሕዝቦች እየተጎዳና እየሞተ ላለው ዓለም የእርሱ ወኪል ሆነው ለአምላካዊው ፍቅርና ጸጋ ምላሽ የሚሰጡ ናቸው፡፡

ሆኖም እነዚህ ወገኖች አሁንም ጥልቀት ባለው ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት አምላካዊው ፍቅርና ጸጋ እንደመሆኑ በዚህ መልኩ ስንንቀሳቀስ፣ በፍቅርና በጸጋ ለሌሎች ስንንጸባረቅ፣ ዛሬም የዚያ ዘላለማዊ መንግሥት ተዋናዮችና ተሳታፊዎች እንሆናለን፡፡

የአንድ አገር ኤምባሲ ምንም እንኳ የሚወክለው አገር ሕዝብና መንግሥት በብዙ ርቀት ሊገኝ ቢችልም፤ ነገር ግን በዓለማቀፍ ሕግ መሰረት አገሩን በአካል ወክሎ እንደተገኘ ይቆጠራል፡፡ በተመሳሳይ እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መመላለስና ዛሬ በዚህ ምድር የዘላለማዊውን ነገር ተጨባጭነት በውልብታ መግለጽ፤ በመጨረሻ ገቢራዊ የሚሆነውን የከፉውን ሽንፈት ከወዲሁ አሻግሮ ለመመልከትና ለማጣጣም

ያስችላል፡፡ ይህን በማድረግ፤ እንደ ክርስቲያን አምባሳደርነታችንና እንደ ክርስቶስ ወኪልነታችን የፍቅሩንና የፍትሕ አምላክነቱን ተጨባጭነት በገዛ ሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያንና ልናገለግል በምንመኛቸው ሰብዓዊ ወገኖች ህይወት መለማመድ እንችላለን፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 2፡16፡፡ በሁለቱ ሽታዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? እኛ የትኛው እንደሆን እንዴት ማወቅ እንችላለን?**

## ሰኞ መስከረም 12

# ትሩፋን አገልጋይ

በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተገልጸው ለሚገኙት ትሩፋን ሕዝቦች የቀረበው ፍቺ በራእ. 12፡17 ይገኛል፡ "እነርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና የኢየሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው" (ራእ. 14፡12)፡፡ እነዚህ ባህሪያት በምድር ታሪክ መዝጊያ ወቅት የሚገኙትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለይተው ያመላክታሉ፡፡ እንዲሁም ስለ እነዚህ ትሩፋን ሕዝቦች ድርጊት፤ በተለይ እነዚህ ሕዝቦች እንዴት ሌሎችን እንደሚያገለግሉ አንዳንድ ምሳሌዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ማግኘት እንችላለን፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 32፡1-14፡፡ በታሪኩ የምንመለከተው የሙሴ ምሳሌ አስፈሪና ተስፋ አስቆራጭ ነው፡፡ የዚህ ታሪክ የሙሴ ሁናቴ በራእ. 12፡17 ከቀረበው የትሩፋን ሁናቴ ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

---

---

እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ በነበረው ብርቱ ቁጣ ከምድር ገጽ ሊያጠፋቸውና--ዘርህ ታላቅ ሕዝብ ይሆናል ሲል ለአብርሃም የገባለትን ኪዳን ወደ ሙሴና ቤተሰቦቹ ለማስተላለፍ ዝቶ ነበር (ዘፀ. 32፡10)፡፡

ሙሴ ግን ይህ እንዲሆን አልፈለገም፡፡ ይልቁንም ሙሴ--ጌታ አደርገዋለሁ ብሎ የዛተው ነገር መልካምነቱን እንደሚያጠፋ በመንገር እግዚአብሔርን ለመሞገት የደፈረ ሰው ነበር (ዘፀ. 32፡11-13)፡፡ ከዚያም ሙሴ አንዳንድ ነጥቦችን ከነካካ በኋላ ራሱን በአምላካዊው ምኅረት ስር በማስገዛት ለእግዚአብሔር ተማጽኖ ያቀርባል፡፡

ሙሴ እነዚህን ሕዝቦች በምድረ በዳ ለመምራት ብርቱ ትግል ውስጥ ነበር፡፡ እነርሱን ወደ ነጻነት መምራት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከማጉረምረምና መጨቃጨቅ ታቅበው አያውቁም፡፡ ታዲያ ይሄ ሁሉ ሆኖ " 'እነርሱን ይቅር ማለት ካልቻልክ ከጻፍኸው መጽሐፍ እኔን ደምስሰኝ'" (ዘፀ. 32፡32) ሲል ለእግዚአብሔር ነግሮት ነበር፡፡ ሙሴ የጉዞው አካል ያደረጋቸውን ሕዝቦች ለማዳን ሲል ዘላለማዊውን ህይወት እስከ መተው ደርሶ ነበር፡፡ ለማይገባቸው ሲባል ራስ መሥዋእት ሆኖ የቀረበበት እንዴት ያለ ብርቱ የምልጃ ምሳሌ

ነው! ለአጠቃላዩ የደኅንነት እቅድ ግዙፍ ምሳሌ ነው!

*“ሙሴ ለእነዚያ በእግዚአብሔር እጅ ለተያዙ ሰዎች ከነበረው ጥልቅ ፍቅርና ፍላጎት አኳያ ስለ እነርሱ ሲማልድ ቁጣና ንዴቱ ጠፍቶ ነበር፡፡ ሙሴ ከራስ ወዳድነት የጸዳውን ጸሎት አቀረበ፤ ጌታም ልመናውን ሰማ፡፡ ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት እንዲሁም ለሳተውና ምስጋና ቢስ ለሆነው ሕዝብ ያለው ፍቅር ተፈተነ፡፡ ሙሴም ባሳየው ላቅ ያለ ሞራላዊ መርኅ ፈተናውን አለፈ፡፡ ሙሴ ለእስራኤል ያለው ብርቱ ፍላጎት ከእራስ ወዳድነት ከጸዳ ተነሳሽነት የመነጨ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ብልጽግና ከግል ክብሩ የላቀና የታላቅ ሕዝብ አባት መሆኑ ከሚሰጠው ዕድል የከበረ ነበር፡፡ በሙሴ ታማኝነት፣ የልብ ንጽህናና ሐቀኝነት ደስ ተሰኝቶ የነበረው እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ተስፋው ምድር የመምራት ኃላፊነት ሰጠው፡፡” የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት፡ ገጽ 361፡፡*

***በዙሪያችን በስህተት ውስጥ ላሉት በተቻለ መጠን ሳንታክት መሥራት እንዳለብን ይህ ምን ይነግረናል?***

## ማክሰኞ                                                          *መስከረም* 13

# *ወደ ነፍሳት መድረስ*

አልፎ አልፎ በቤተ ክርስቲያን ውይይቶች--ትኩረታችንን በማኅበራዊ እንቅስቃሴ ላይ እናድርግ ወይስ በወንጌል *ሥራ*፣ በበጎ አድራጎት ወይስ በምስክርነት፣ በፍትሕ ነክ ወይስ በወንጌል ጉባዔ--የትኛውን መምረጥ እንዳለብን እንቸገራለን፡፡ ነገር ግን እነዚህን እያንዳንዳቸውን ጽንሰ ሀሳቦች በተሻለ ማስተዋል ስንችልና የየሱስን አገልግሎት ስናጤን ልዩነቱ ይጠብና፤ ወንጌልን መስበክና የተቸገሩትን ለመርዳት *መሥራት* በቅርብ የተቆራኙ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

*“ወደ ሕዝቦች ለመድረስ፤ የክርስቶስ ዘዴ ብቻውን እውነተኛ ስኬት ያስገኛል፡፡ አዳኙ የሰዎችን በጎ እንደሚመኝ በሚገልጽ አኳኋን ከሰዎች ጋር ተቀላቀለ፡፡ ርኅራኄ አሳያቸው፣ በሚያስፈልጋቸው አገለገላቸው፣ በዚህም መተማመናቸውን አሸነፈ፡፡ ከዚያም “ተከተሉኝ” ሲል ጥሪ አቀረበላቸው...*

*“ድኾች አንዳች የሚያስታግስ ነገር አገኙ፣ ህመምተኞች ተፈወሱ፣ ያዘኑና የተከዙ መጽናናት አገኙ፣ ትምህርት ያልነበራቸው የዕውቀት ባለቤት ሆኑ፣ ልምድ ያልነበራቸው ምክረ ሀሳብ ተቀበሉ፡፡ ከሚያለቅሱ ጋር እናለቅሳለን፣ ደስ ካላቸውም ጋር ሐሴት እናደርጋለን፡፡”*—Ellen G. White, The Ministry of Healing, p. 143.

የአምላካዊው *መንግሥት* መገለጫዎቹ ፍትሕ እና ወንጌልን መስበክ በቅርብ የቆራኙት በየሱስ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ በሰጣቸው የመጀመሪያ ተልዕኮ ጭምር ነው፡ “ሄዳችሁም ‘*መንግሥተ* ሰማያት ቀርባለች’ ብላችሁ ስበኩ።

በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ፡፡" (ማቴ. 10፡7-8)፡፡ በአጭሩ መልእክታችንን ለሌሎች ለማድረስ ከሚችሉ እጅግ ምርጥ መንገዶች አንዱ በሚያስፈልጋቸው ማገልገል ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ጴጥ. 2፡12፣ ፊልጵ. 2፡15፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚተገበር መልካም ሥራ ስላለው የምስክርነት ኃይል ጴጥሮስና ጳውሎስ ምን ይላሉ?

---

---

የአምላካዊው የምሥራች ሰፋ ባለ የማስተዋል ዐውድ ሲቀርብ፤ ለሰዎች ርኅራኄ የሌለው የወንጌል ሥራ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እንደ 1ዮሐ. 3፡16-18 እና ያዕ. 2፡16 ያሉት ቁጥሮች ወንጌልን ሳንኖርበት መስበክ ስላለው ተቃርኖ አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡ የወንጌል ሥራ የተስፋውን የምስራች ይዞ መምጣት፣ ማዳን፣ ወደ ንስሐ መምራት፣ መለወጥ ሲሆን--የእግዚአብሔር አቃፊ ፍቅር ደግሞ የፍትሕ መገለጫ ነው፡፡

ወንጌልን መስበክ እና ለፍትሕ የሚኖር ቅንአት እግዚአብሔር ለጠፉ፣ ለተቸገሩና ለተጎዱ ያለውን ፍቅር ከመገንዘብ ይመነጫል፡፡ ይህ ፍቅር እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ በሚኖረው ተጽእኖ በልባችን የሚያድግና የሚጎለብት ነው። አንዱን ከሌላው ሳናበላልጥ እግዚአብሔር የሰጠንን ማንኛውንም ስጦታ ጥቅም ላይ እያዋልን፤ የሰዎችን እውነተኛ ፍላጎት ለማሟላት ከእግዚአብሔር ጋር ለእነርሱ እንሠራለን፡፡

***ለሌሎች መልካም ሥራ ስንሠራ በተጓዳኝ የደኅንነት መልካም የምሥራች የሆነውን ወንጌል መስበክ ችላ ላለማለታችን እርግጠኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?***

## ረቡዕ — መስከረም 14

# ጸጋ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

በኢዮብ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ኢዮብ ታማኝ ስለመሆኑ፣ የአምላካዊውን መንገድ የሚከተልና እግዚአብሔር ከወደቀው ሰብዓዊ ፍጡር ጋር ባለው መስተጋብር ቅንነቱን በማሳየት ምስክርነት ሲሰጥለት ይታየል (ኢዮ. 1፡8)፡፡ አምላካዊው መልካም ስምና ዝና በምድር ላይ በሚኖሩ ሕዝቦቹ ሕይወት እንዲገለጥ ጌታ መፍቀዱ እጅግ

አስደናቂ ነው፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ይህን እግዚአብሔር በአንዳንድ “ቅዱስ” ሰዎች ያለውን እምነት የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብን በማካተት አስፋፍቶታል፡ “አሳቡም በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው” (ኤፌ. 3፡10)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 2፡19፡፡ ቤተ ክርስቲያናዊው ማኅበረሰብ እንደ እግዚአብሔር “ቤተሰብ” በተገለጸበት ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ ምን የተካተተ ይመስሎታል? በመዋቅር የተደራጀው ቤተ ክርስቲያን እንዴት መሥራት እንዳለበት አስመልክቶ ይህ አገላለጽ ምን ዓይነት ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል?

---

---

ማንኛውም ማኅበረሰብ ወይም ድርጅት ከአባላቶቹ ጋር የሚኖረው አግባብ የቡድኑን መሰረታዊ እሴት ያንጸባርቃል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ፤ የክርስቶስ አካል እና የመንፈስ ቅዱስ ማኅበረሰብነቷ--እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አለመሆኑን የማሳየት ከፍ ያለ ኃላፊነት አለባት (1ቆሮ. 14፡ 33)፡፡

በአምላካዊው ፍትሕ፣ ጸጋና ፍቅር እንደታየው--የፍትሕ፣ የጸጋና የፍቅር እሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱትን ነገሮች በሙሉ መግዛት አለባቸው። እነዚህ መርኅዎች ከአጥቢያ የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ እስከ ዓለማቀፉ የቤተ ክርሰቲያን መዋቅር፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለሚሰጡት ምሪት፣ ውሳኔ እና “ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት” ለአንዱ ጥንቃቄ የማድረግ አቅጣጫ ሊያሳዩ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአባላት መካከል የሚነሱ ቅራኔዎችን እንዴት መፍታት እንደሚኖርባቸውም ምሪት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመካከላችን ያሉትን በቅንነትና በአክብሮት ማስተናገድ ሳይሆንልን ከውጪ ያሉትን እንደምን ልናስተናግድ እንችላለን?

የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ሰዎችን ለአገልግሎት ሲመድብ ሁሉንም በእኩል የማየትና ከማንኛውም አድሎ የተጠበቀውን ተግባር በደግነት ሊያከናውን ይገባል። ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉም አባላት ለጉዳት ተጋላጮችን በመከላከል የተቻላቸውን የሚያደርጉበት ደኅንነታቸው የተጠበቀ ስፍራ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እንደ ተመለከትነው አባላት በተለይ የቤተ ክርስቲያን “ቤተሰብ” ለነበሩ ችግረኞች ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁዎች ነበሩ፡፡

የሱስ የሚከተለውን እንደ ትእዛዝ ሲሰጥ--ለውጥ የሚያመጣው በአማኝ ማኅበረሰቡ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም ፊት እምነታቸውን በተጨባጭ ስለሚያሳይ

ነበር “ ‘አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ’” (ዮሐ. 13፡34-35)፡፡

## ሐሙስ መስከረም 15

# ለመልካም ሥራ እርስ በርስ መበረታታት

ምርጥ በሆኑ መነሳሳቶች፣ ውጥኖችና እምነት በእግዚአብሔር እንዲሁም መልካም በሆነው ነገር በኩል ቆመናል እያልን እንኳ ለጌታ መሥራት አስቸጋሪና ተስፋ አስቆራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ዓለማችን በአስከፊና ህመም ባለው ሁኔታ ውስጥ መውደቋ የማይታበል ሐቅ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም ይሄው ነው፡፡ የሱስ እንዲህ ያለውን ድጋፍ ሰጭ ሕብረተሰብ በደቀ መዛሙርቱ ምሳሌ አሳይቶአል፡፡ እርሱ ሰዎችን በግል የላከባቸው አጋጣሚዎች እምብዛም ባይኖሩም ነገሩ ቢሆን እንኳ ምንም ያህል ጊዜ ሳይወስዱ እንደገና ታሪካቸውን ለመናገር፣ ጉልበታቸውንና ድፍረታቸውን ለማደስ በአንድነት ይገናኛሉ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 10፡23-25፡፡ ዕብ. 10፡25 ከሁሉም በላቀ የሚታወቅ ጥቅስ እንደመሆኑ ቀደም ያሉት ሁለት ጥቅሶች ለዚህ በስፋት የሚታወቅ ጥቅስ ምን ያክላሉ? “ለፍቅርና ለመልካም ሥራ” እርስ በርሳችን ከምንበረታታባቸው መንገዶች አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

በማንኛውም ዓይነት ሥራ ወይም ፕሮጀክት በቡድን ሆነው የሚሠሩ፤ ሁሉም በተናጥል ቢሆኑ ሊሠሩት ከሚችሉት የላቀ ውጤት ያስመዘግባሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል ያላትን ምስል በመስጠት እኛ ሁላችን የተለያየ ግን የተሟላ ሚና እንደምንጫወት ያስታውሰናል (ሮሜ 12፡3-6)፡፡ እያንዳንዳችን በተሻለ መሥራት የምንችለውን ነገር ስንሠራና የመሥራት ክህሎታችን አብሮ ለመሥራት በሚፈቅደው መንገድ ስንሠራ፤ ህይወታችንና ሥራችን ዘላለማዊ ልዩነት ማምጣት የሚችል ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል መገመት እንችላለን፡፡

ትክክል የሆነውን ነገር ለመሥራት ፍላጎት የሚኖረውን ያህል ከሰዎችና ከሰዎች ህይወት ጋር ተያያዥነት ያለው ውጤትም እንዲሁ በእጅጉ አስፈላጊ ከመሆኑ

እኢያ--ሊገኝ የሚችለው ውጤት ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሔር ላይ መታመን ይኖርብናል፡፡ የድኽነትን ሥቃይ ለማስታገስ፣ ለጥቃት ተጋላጩን ለመከላከል፣ የተጨቆነውን ቀንበር ለመስበርና ድምጹ ለማይሰማው ለመናገር በምናደርገው እንቅስቃሴ አልፎ አልፎ አነስተኛ መሻሻሎችን እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን በበለጠና በተሳካ ሁኔታ በድል አድራጊነት ለመስራት ተስፋ አለን “በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ካልቆረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን፡፡ ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም እናድርግ፡፡” (ዕብ. 6፡9-10)፡፡

አንዱ ሌላውን እንዲያበረታታ የተጠራንበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡ በታማኝነት መኖር አስደሳችም አስቸጋሪም ነው፡፡ የፍትሕ አምላካችን እና ፍትሐዊ ማኅበረሰባችን ሌሎችም እንዲቀላቀሉን ግብዣችንን እንድናቀርብ የሚያደፋፍሩን አጋዦቻችን ናቸው፡፡

***የሌሎችን ሥቃይና እንግልት ለማስታገስ በመደበኛ ከሚሠራ ሰው ማንን ያውቃሉ? ይህ ግለሰብ ወይም ቡድን ለሚሠራው መልካም ሥራ የሚሰጡት ማበረታታት ምን ይመስላል?***

## አርብ መስከረም 16

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** *Read Ellen G. White, “A Faithful Witness,” pp. 546–556, in The Acts of the Apostles; “Kindness the Key to Hearts,” pp. 81–86, in Welfare Ministry.*

“ደቀ መዛሙርቱ የሠሩትን ሥራ እኛም እንዲሁ መሥራት ይኖርብናል፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን ወንጌላዊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ በችግር ውስጥ የሚገኙትን ሰብዓዊ ወገኖች ከራስ ወዳድነት ርቀን የሐዘናቸው ተካፋይ በመሆን በጽኑ ርኅራኄ እናገልግላቸው...

“የተራቡትን እንመግብ፣ የታረዙትን እናልብስ በሥቃይና በጉዳት ያሉትንም እናጽናና፡፡ ተስፋ የቆረጡትን እያገለገልን ተስፋቸውን እናለምልም፡፡

“ከራስ ወዳድነት ፍጹም ነጻ በሆነ አገልግሎት የተገለጸው የክርስቶስ ፍቅር ከሰይፍ ወይም ከፍርድቤት ፍትሕ የበለጠ ውጤታማ ተሐድሶ በክፉ አድራጊው ላይ ማምጣት ይችላል. . . በዘለፋና ግሳጼ የደነደነ ልብ በክርስቶስ ፍቅር ስር ሲውል ይቀልጣል”—Ellen G. White, The Ministry of Healing, pages 104, 106.

"ባርነት፣ መድልዎአዊ ሥርዓት፣ ኢፍትሐዊ የዘር ጭፍን ጥላቻ፣ የድኻው ጭቆና፣ ረዳት የሌላቸውን ችላ ማለት--ክርስቲያናዊ ያልሆኑና ለሰብዓዊው ዘር ደህንነት አስጊ ጠንቆች በመሆናቸው እነዚህን የከፉ ተግባራት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አሽቀንጥራ እንድትጥል በጌታዋ ሥልጣን ተሰጥቷታል፡፡"—General Conference president A. G. Daniells, speaking of the work of Ellen G. White at her funeral, Life Sketches of Ellen G. White, p. 473.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

**1.በዓለም ውስጥ የሚስተዋለውን እጦት ለማስታገስ የሚሠሩ በጣም ብዙ ሰዎች፣ ቡድኖችና ድርጅቶች አሉ፡፡ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ለእዚህ ኃላፊነት ምን ዓይነት ልዩ ጉልበት፣ ራእይና ሐብት ማጋራት ትችላለች?**

**2.ከቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብዎ መበረታታትና ድጋፍ ያገኙበትን ጊዜ ያስታውሳሉ? ከዚያ ተሞክሮ በመማር እርስዎም ለሌሎች ተመሳሳይ ማበረታቻ ማበርከት የሚችሉት እንዴት ነው?**

3.*መልካም በማድረግ መዛል* **እንዳይገጥሞት የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብን ድጋፍ ጨምሮ ሌሎች ምን ዓይነት ሊረዱ የሚችሉ ነገሮች ይኖራሉ?**

**4.ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ድጋፍ ከምትሰጣቸው አንዳንድ የፍትሕና የድኽነት ቅነሳ ወይም ልማት መርኀ ግብሮች እርሶ የሚያውቋቸው የትኞቹን ነው? ለዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱ አንደኛው ተግባር ድጋፍዎን ማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው**

***ማጠቃለያ፡ አዎ--እንደ ክርስቲያን በተለይ በጉዳት፣ በሥቃይና በጭቆና ቀንበር ስር ያሉትን እንድናገለግል ተጠርተናል። ምንም እንኳ በዚህ ዙሪያ የግል ኃላፊነት ቢኖርብንም፤ ሌሎችን ለማገልገል ትኩረት ባደረገ እንደ ማኅበረሰብ፤ ማለትም እንደ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ይበልጥ ውጤታማ ሥራ መሥራት እንችላለን።***